# አዲስ ዘመን

ኢፕድ

ሐሙስ

82ኛ ዓመት ቁጥር 040 ጥቅምት 10 ቀን 2015 ዓ.ም ዋጋ 10:00

ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!







# መንግሥት የሰሜኑን ጦርነት በዘላቂነት ለመፍታት የሰላም በሮችን ክፍት አድርጎ እየጠበቀ ነው

በጋዜጣው ሪፖርተር

አዲስ አበባ፡- ከሰሜኑ ጦርነት ጋር በተያያዘ ያለውን ችግር በዘላቂነት ለመፍታት መንግሥት የሰላም በሮችን ክፍት አድርጎ እየጠበቀ መሆኑንም የብልጽግና ፓርቲ ምክትል ፕሬዚዳንት አደም ፋራህ ገለጹ።

የብልጽግና ፓርቲ ምክትል ፕሬዚዳንት አደም ፋራህ ከኢዜአ ጋር ባደረጉት ቆይታ እንዳሉት፤ የኢትዮጵያን ውስጣዊ ችግሮች ለመፍታት የዜጎቿ ትብብር፣ የሁሉም አካላት የሰላም ቁርጠኝነትና ለምክክር ዝግጁ መሆን አስፈላጊ ነው።

በመሆኑም ከሰሜኑ ጦርነት ጋር በተያያዘ ያለውን ችግር በዘላቂነት ለመፍታት መንግሥት የሰላም በሮችን ክፍት አድርጎ እየጠበቀ ነው ብለዋል።

በኢትዮጵያ የሚስተዋሉ ችግሮችን በዘላቂነት ለመፍታት የመንግሥት የሰላም እጆች መቼም ቢሆን አይታጠፉም ያሉት ምክትል ፕሬዚዳንቱ፤ በተለይም ከሰሜኑ ጦርነት ጋር ተያይዞ ያለውን ችግር በሰላማዊ ውይይት ለመፍታት የመንግሥት ቁርጠኝነት እንዳለ ቢሆንም በጥፋት መቀጠል ከፈለጉት አካላት ግን ተቃራኒ ሃሳቦች መኖራቸውን ገልጸዋል።

ለአፍሪካዊ ችግሮች አፍሪካዊ መፍትሄ በሚል

መንግሥት የሰሜኑን ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል



የብልጽግና ፓርቲ ምክትል ፕሬዚዳንት አደም ፋራህ








ፎቶ ፡- ሳሙኤል ተስፋዬ

አቶ ሽመልስ አብዲሳ

# በኦሮሚያ ክልል አንድ ሚሊዮን ሄክታር መሬት የበጋ ስንዴ ለማልማት ታቅዷል

ጌትነት ምህረቴ

አዲስ አበባ፡- በኦሮሚያ ክልል አንድ ሚሊዮን ሄክታር መሬት የበጋ ስንዴ ልማት ለማካሄድ ታቅዶ ወደ ተግባር መግባቱን የክልሉ ርዕሰ መስተዳድር አቶ ሽመልስ አብዲሳ ገለጹ።

ርዕሰ መስተዳድር አቶ ሽመልስ አብዲሳ በክልሉ የሚካሄደውን የበጋ ስንዴ ልማት በተመለከተ እንደገለጹት፤ በኦሮሚያ ክልል የስንዴ ምርትና ምርታማነትን በማሳደግ በምግብ ራስን ለመቻል፣ ከውጭ የሚገባውን ምርት በሀገር ውስጥ ሙሉ ለሙሉ በመተካትና ወደ ውጭ በመላክ የውጭ ምንዛሬን ለማግኘት ታሳቢ ያደረገ እቅድ ታቅዶ ወደ ሥራ ተገብቷል። ክልሉ አንድ ሚሊዮን ሄክታር መሬት የበጋ ስንዴ ልማት ለማካሄድ ታቅዶ ወደ ተግባር ተገብቷል። በአሁኑ ጊዜም ከ20ሺህ በላይ ሄክታር መሬት በበጋ ስንዴ በዘር መሸፈን ተችሏል።

ባለፈው ዓመት በክልሉ 600ሺህ ሄክታር መሬት በበጋ ስንዴ ማልማት መቻሉን ያወሱት አቶ ሽመልስ፤ ዘንድሮ በበጋ ስንዴ የሚለማውን መሬት ወደ አንድ ሚሊዮን ሄክታር በማሳደግ ሙሉ ለሙሉ የአገርን የስንዴ ፍጆታ ለመሸፈንና የውጭ ገበያን ታሳቢ ያደረገ የስንዴ ምርት ለማግኘት ታቅዶ እየተሰራ መሆኑን ገልጸዋል።

በኦሮሚያ ክልል የበጋ ስንዴ ልማት የተጀመረው መስከረም 5 ቀን 2015 ዓ.ም መሆኑን አመልክተው፤እስካሁን ድረስም በምዕራብና ምስራቅ ወለጋ፤በቄሌም ወለጋ፣ በጅማና ኢሉባቡር አካባቢዎች ከ20ሺ ሄክታር በላይ መሬት በበጋ ስንዴ በዘር መሸፈኑን አመልክተዋል።

በኦሮሚያ ክልል ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል



ረዳት ፕሮሰፌር ያየሁ ገነት

# ኢትዮጵያ የዲፕሎማሲ መርሆዎችን በመከተል በቀጣናው የሚታየውን የውጭ ኃይሎች ፍላጎት ልታከሽፍ ይገባል

ውብሸት ሰንደቁ

አዲስ አበባ፡- ኢትዮጵያ የዲፕሎማሲ መርሆዎችን በመከተል እና ሉአላዊነቷን በማስከበር በአፍሪካ ቀንድ ጥቅማቸውን ለማስከበር የሚታየውን የውጭ ኃይሎች ፍላጎት ልታከሽፍ እንደሚገባ ተጠቆመ።

በባህርዳር ዩኒቨርሲቲ የፖለቲካል ሳይንስና ዓለም አቀፍ ጥናት ትምህርት ክፍል መምህርና ተመራማሪ ረዳት ፕሮሰፌር ያየሁ ገነት ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለፁት፤ ዓለም አቀፍ ድርጅቶችም ሆነ ድንጋጌዎች የውጭ ኃይሎች የበላይነት ማስጠበቂያ መንገዶች ናቸው። ምዕራባዊያን ዓለም አቀፍ ድንጋጌዎችንና ተቋማትን መሣሪያ በማድረግ በአፍሪካ ቀንድ ያላቸውን ጥቅም ለማስጠበቅ እየሠሩ ነው የሚገኙት።

በመሆኑም ኢትዮጵያ የዲፕሎማሲ መርሆዎችን በመከተል እና ሉአላዊነቷን በማስከበር በአፍሪካ ቀንድ

ኢትዮጵያ የዲፕሎማሲ ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል








## ሕገ-ወጥ የውጭ ምንዛሬና የወርቅ ንግድን በመጠቆም ወሮታ የሚከፈልበት አሰራር ተግባራዊ ሆነ

ገጽ 3

National ID
ብሔራዊ መታወቂያ

# ብሔራዊ መታወቂያው በፍትሕ ስርዓቱ ላይ የሚፈጠሩ ችግሮችን ይቀርፋል

**ሙሳ ሙሐመድ**

አዲስ አበባ፡- በኢትዮጵያ አዲስ የተጀመረው የዲጅታል ብሔራዊ መታወቂያ ወንጀለኞች በፍትሕ ስርዓቱ ላይ የሚፈጥሩትን ክፍተት የሚቀርፍ መሆኑን የብሔራዊ መታወቂያ ፕሮጀክት ጽህፈት ቤት አስታወቀ።

የብሔራዊ መታወቂያ ፕሮጀክት ጽህፈት ቤት የብሔራዊ መታወቂያ የፖሊሲ እና ሕግ አማካሪ አቶ በላይሁን ይርጋ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደተናገሩት፤ በሁሉም ዘርፍ ወንጀል እየሰሩ ያሉ ወንጀለኞች የተለያየ ማንነት ይዘው የፍትህ ስርዓቱ ላይ ክፍተት እየፈጠሩ ይገኛሉ።

አሁን ላይ በኢትዮጵያ አዲስ እየተሰጠ ያለው የዲጂታል ብሔራዊ መታወቂያ የወንጀለኞችን የተለያየ ማንነት በማጋለጥ በፍትሕ ስርዓቱ ላይ የሚፈጥሩትን ክፍተት እንደሚቀርፍም አቶ በላይሁን ተናግረዋል።

የብሔራዊ ዲጂታል መታወቂያ የአገልግሎት አሰጣጡ "አንድ ሰው አንድ ነው" የሚለውን መርህ ያረጋግጣል ያሉት አቶ በላይሁን፣ ጽህፈት ቤቱ ዲጅታል መታወቂያን ተግባራዊ ማድረጉ በሀገሪቱ አጠቃላይ ከፍትህ፣ ከጤና፣ ከግብርና፣ ከኢኮኖሚ ብሎም ከፖለቲካ ስርዓቱ ጋር የተያያዘ በመሆኑ ጠቀሜታው እንደ ሀገር የጎላ መሆኑንም ገልጸዋል።

አገልግሎቱ ከመንግስታዊ ጥቅም ባለፈ አንድ ሰው በአንዲት ሀገር እንደ ዜጋ የመታወቅ መብቱን ለማስጠበቅም የሚያስችል መሆኑን አቶ በላይሁን አክለው ተናግረዋል።

እንደ አቶ በላይሁን ገለጻ፣ የመታወቂያ ስርዓቱ የልደት ቀን እና የትውልድ ስፍራን የሚያካትት ቢሆንም መረጃዎቹ ግልጽ የሚደረጉት በባለቤቱ ፈቃድ ብቻ መሆኑን ተናግረዋል።

አቶ በላይሁን አክለውም፣ አገልግሎቱን በህግ ለመደንገግ የብሔራዊ ዲጅታል መታወቂያ አዋጅ በሚኒስትሮች ምክር ቤት ቀርቦ የጸደቀ ቢሆንም፣ ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት እስካሁን አለመቅረቡን ጠቁመዋል።

አገልግሎት ጽህፈት ቤቱ የዜጎች ምዝገባን እያካሄደ ያለ ቢሆንም በህዳር ወር በሀገር አቀፍ ደረጃ ምዝገባ ለመጀመር ማቀዱን አስታውቀዋል።

የዲጅታል መታወቂያው የመረጃ ፍሰትን ከተቋማት ጋር በቅንጅት የሚሰራ በመሆኑ አገልግሎቱ ዲጅታል ኢትዮጵያን እውን ለማድረግ ያግዛል ሲሉም ተናግረዋል።

የመታወቂያ አገልግሎቱ በኢትዮጵያ ውስጥ ለሚኖር የትኛውም ዜጋ የሚሰጥ መሆኑንም አቶ በላይሁን አመላክተዋል።




ፎቶ ፡- ገበዮ ገብሬ

# ባለሥልጣኑ አገልግሎቱን ለማዘመን እየሰራ መሆኑን አስታወቀ

**አዲሱ ገረመው**

አዲስ አበባ፡- የመንግስት ግዥና ንብረት ባለስልጣን አገልግሎቱን ለማዘመን እየሰራ መሆኑ አስታውቋል። ከመንግሥት በጀት 65 በመቶ የሚሆነው ለመንግስት ግዥና ንብረት እንደሚውልም ባለስልጣኑ ገልጿል።

የፌደራል የመንግስት ግዥና ንብረት ባለስልጣን ከአለም ባንክ የኢትዮጵያ ቅርንጫፍ ጋር በመተባበር የግሉ ዘርፍ የቢዝነስ ስራ ላይ ያተኮረ አውደ ጥናትና ምክክር ከባለ ድርሻ አካላት ጋር አካሂዷል። በመድረኩ የመንግስት ግዥና ንብረት ባለስልጣን ዋና ዳይሬክተር አቶ ሀጂ ኢብሳ፤ የመንግስት ግዥና ንብረት ባለስልጣን የዘርፉን አገልግሎት ለማዘመን እየሰራ መሆኑን አስታውቀዋል። ከመንግስት በጀት 65 በመቶ የሚሆነው ለመንግስት ግዥና ንብረት እየዋለ ነው።

እንደ አቶ ሀጂ ገለጻ፤ በግዥ የሚያጋጥሙ ተግዳሮቶችን ለመፍታት የመንግስት ግዥና ንብረት ባለስልጣን ህግና መመሪያ ማሻሻል መጀመሩንና የመንግስት የኤሌክትሮኒክስ ግዥዎችን ማዘጋጀቱን ተናግረዋል። በግዥ ስርአትና አገልግሎቶች ላይ በሚውለው የመንግስት በጀት ግልጸኝነትንና ተጠያቂነትን እንዲሁም መልካም አስተዳደርን ለማስፈን፤ በሚያጋጥሙ ተግዳሮቶች ላይ የግሉ ዘርፍ ንቁ ተሳትፎ ማድረግ አለበት ብለዋል። የፋይናንስ ሥርዓቱን በማዘመን ቀልጣፋና ግልፅ አሰራር እንዲኖር ከዓለም ባንክና ሌሎች አጋር ድርጅቶች ጋር በትብብር እንደሚሰራም ተናግረዋል።

በኢትዮጵያ ከመንግስት በጀት 65 በመቶው የሚሆነው ለመንግስት ግዥና ንብረት እንደሚውል የጠቆሙት አቶ ሀጂ ኢብሳ፤ የግዥ እቃዎችና አገልግሎቶች ላይ የዋለውን ከፍተኛ የመንግስት በጀት ግልፅነትን፣ የገንዘብ ተጠያቂነትንና መልካም አስተዳደርን ለማስፈን በሚያስችል መልኩ እየተሰራ እንዳለም ጠቁመዋል። ባለስልጣኑ የኤሌክትሮኒክስ ግዥ በማዘጋጀት በተለያዩ የመንግስት አካላት የሙከራ ስራ መተግበሩን አንስተዋል። የግሉ ሴክተር ባለድርሻ አካል በሚፈለገው መጠን የመንግስት የኤሌክትሮኒክስ ግዥዎችን መሳተፍ እንዳለበትም አስገንዝበዋል።

የአለም ባንክ "ኦፕሬሽን ማናጀር" ዶይና ፔትሬስኩ በበኩላቸው፣ አለም ባንክ ከኢትዮጵያ ጋር የቆየ ጠንካራ ግንኙነት እንዳለው ጠቅሰዋል። በጋራ ለመስራት በተቀመጡ ስትራቴጂዎች መሰረት ድጋፎች እንደሚደረጉና በተለይም የመልካም አስተዳደርና ኢኮኖሚያዊ ጉዳዮች ላይ ትኩረት ባደረጉ ስራዎች ላይ ስምምነቶች እንደሚኖሩ ገልጸዋል። የፋይናንስ ሥርዓቱን በማዘመን ቀልጣፋና ግልፅ አሰራር እንዲኖር ዓለም ባንክ ተባባሪ ተቋም እንደሆነም ተናግረዋል።

የዓለም ባንክ ለአገሪቱ ጠቃሚ የሆኑ ፕሮጀክቶችን በመደገፍ በኩል በትብብር እየሰራ ነው ያሉት ማናጀሯ፤ በግዥ በኩል ጠንካራ ስርዓት እንዲኖር ሴክተሮችን የመደገፍ ሥራው ቀጣይነት ያለው እንደሆነም ገልጸዋል።

በአውደ ጥናቱ የዓለም ባንክ የግዥ ማዕቀፍን በተመለከተ፣ የቢዝነስ እድሎች እና የንግድ ሥራዎች፣ ምርቶች እና አገልግሎቶች፣ ስለ ሴክተር ደረጃ ምዘና እንዲሁም ከግሉ ዘርፍ የኢትዮጵያ የመንግስት ግዥ ህግ ማግኘት በሚችልባቸው አጀንዳዎች ዙሪያ ምክክር ተደርጓል።


# በኦሮሚያ ከ14 ሺህ በላይ ትምህርት ቤቶች የምገባ ስርዓት ተጠቃሚ ይሆናሉ

**ዳግማዊት ግርማ**

አዲስ አበባ፡- በኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ከ14 ሺህ በላይ የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የምገባ ስርዓት ተጠቃሚ እንደሚሆኑ የክልሉ ትምህርት ቢሮ አስታወቀ። በክልሉ በሁሉም ዞኖች በሚገኙ ትምህርት ቤቶች ምገባ መጀመሩም ተመላክቷል።

የኦሮሚያ ትምህርት ቢሮ ምክትል ኃላፊ አቶ ኤፍሬም ተሰማ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለፁት፤ ክልሉ በተጀመረው በጀት ዓመት በትምህርት ዘርፍ ላይ ልዩ ልዩ ተግባራት በመከወን አመርቂ ውጤት ማስመዝገብ የቻለ ሲሆን በምገባ ስርዓቱም ከ14 ሺህ በላይ ትምህርት ቤቶች ተጠቃሚ ይሆናሉ።

ትውልድን በተሻለ መንገድ ለመቅረፅ ትምህርት ላይ ትኩረት አድርጎ መንቀሳቀስ እንደሚያሻ የገለፁት አቶ ኤፍሬም፤ በትምህርት ተቋማቱ ላይ የሚሰራውን የምገባ ስርዓትም ልጆች ሀሳባቸው ሳይበታተን ትምህርታቸውን እንዲከታተሉ ማድረግ እንደሚያስችላቸውም ነው የገለፁት።



አቶ ኤፍሬም ተሰማ

በክልሉ በትምህርት ቤት ምገባው ተጠቃሚ ከሚሆኑት ከ14 ሺህ ትምህርት ቤቶች ውስጥ አብዛኞቹ ምገባውን መጀመራቸውን የገለፁት አቶ ኤፍሬም፤ የአጀማመር ወጣገባነትና በየስፍራው መለያየት ቢኖርም በክልሉ በሁሉም ዞኖች በሚገኙ ትምህርት ቤቶች ምገባ መጀመሩን ተናግረዋል።

ክልሉ ባሳለፍነው ዓመት 735 ሺህ የሚሆኑ በቆላማና ዝናብ አጠር በሆኑ ስፍራዎች ለሚገኙ ልጆች የምግብ ድጋፍ ማድረጉን ያወሱት አቶ ኤፍሬም፤ ዘንድሮም በክልሉ በሚገኙ 18 ሺህ በላይ ትምህርት ቤቶች ውስጥ ከሰባት ነጥብ አምስት ሚሊዮን በላይ ተማሪዎች የምገባው ተጠቃሚ እንደሚሆኑ ገልፀዋል።

የኦሮሚያ ትምህርት ቢሮ በክልሉ ዞኖች፣ ከተሞችና ወረዳዎች በማደራጀት የምገባ መርሀ ግብር ብቻ ሳይሆን ሌሎችም መልካም ተግባራትን መከወኑን የገለፁት የቢሮው ምክትል ኃላፊ፤ የተሳካና አይቻልም የተባለውን ያስቻለ ስራ መሰራቱንም ገልፀዋል።

ከአንደኛ እስከ አራተኛ ክፍል ባሉ የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ላይ ተግባራዊ የተደረገው የምገባ መርሀ ግብሩ በህብረተሰቡ ተሳትፎ እንደሚከወን የተናገሩት ምክትል ቢሮ ኃላፊው፤ በተለያዩ ጉዳዮች ላይ ተሳታፊ የሆኑ የክልሉ ባለሀብቶችና ቀና አሳቢዎችንም አመስግነዋል።

በውጪ ሀገርም ሆነ በሀገር ውስጥ የሚገኙና በክልሉ የሚኖሩ ልጆች ያላቸውም ሆኑ የሌላቸው ዜጎች ድጋፉን በማድረግ ላይ መሆናቸውን የጠቀሱት አቶ ኤፍሬም፤ የዜግነት አገልግሎት ግዳጃቸውን በመወጣታቸውም ምስጋናቸውን አቅርበዋል።



# «በኢትዮጵያ ምቹ የኢንቨስትመንት አማራጭ አለ»

**- ሳልፋሬዝ አንሳሪ**
**የካሊማ ፋርም ቴክኖሎጂ ኢንጂነሪንግ ዳይሬክተር**

**ሞገስ ተስፋ**

አዲስ አበባ፡- በኢትዮጵያ ምቹ የኢንቨስትመንት አመራጭ እንዳለ የህንዱ ካሊማ ፋርም ቴክኖሎጂ ኢንጂነሪነግ ዳይሬክተር ሳልፋሬዝ አንሳሬ ገለጹ።

ሳልፋሬዝ አንሳሬ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ በኢትዮጵያ ኢንቨስት ለማድረግ ተስማሚ የአየር ንብረት፣ አምራች የሆነ የሰው ኃይል የሚገኝባት ናት። ለዚህም በህንድ ሙንባይ ከተማ የሚገኘው ካሊማ ፋርም ኢንጂነርንግ በኢትዮጵያ ሰፊ ኢንቨስትመንት እያካሄደ ነው።

ለንጽህና መጠበቂያ ማለትም ለፋርማሲ ፣ ለጤና አጠባበቅ ፣ ባዮቴክ ፣ የኤሌክትሮኒክስ ኢንዱስትሪዎች ምርት ላይ የካበተ ልምድ መኖሩን የገለጹት ዳይሬክተሩ፤ የሚመረቱ ምርቶች የሚሸጡበት የገብያ ስርዓትና ሰፊ የመሬት አማራጭ መኖሩን ጠቁመዋል።

በምስራቅ አፍሪካ ፕሮጀክቶች አሉን ያሉት ዳይሬክተሩ፤ ከእነዚህም የኢትዮጵያ ቀዳሚ ፕሮጀክታችን ሲሆን፤ በኢትዮጵያ ለሚገነቡ የፋርማስቲካል ፕሮጀክት የማማከርና ግብዓት የማቅረብ ስራ ይሰራል። በኢትዮጵያ ለፋርማስቲካል ቴክኖሎጂ እድገት የሚሰራ ሲሆን በደብረ ብርሃን መሬት ወስዶ ግንባታ እያካሄደ ነው። በተጨማሪም በቂሊንጦ ኢንዱስትሪ ፓርክ ግንባታ ለማከናወን መሬት በሊዝ ወስዶ ጥናት በማካሄድ ግንባታ ለመጀመር እየተዘጋጀ መሆኑን ገልጸዋል።

በኢትዮጵያ የካሊማ ቴክኖሎጂ ኢንጂነሪንግ ፕሮጀክት አማካሪ የሆኑት አቶ አባይነህ ጥላዬ በበኩላቸው እንደገለጹት፤ በደብረ ብርሃን እየተገነባ ያለው ፕሮጀክት ሶስት ሺ ሁለት መቶ ካሬ ሜትር የሚሸፍን ቦታ ላይ እየተገነባ ሲሆን የጥናትና ለውጥ ፕሮጀክቶችን ያካተተ ነው። በኢንዱስትሪ ፓርኮች ላይ የሚስተዋሉ ችግሮችን ለመቅረፍ የሚደረግ ጥናት በውስጡ መያዙንም ገልጸዋል።

ከደብረ ብርሃን በተጨማሪ ለጤና አጠባበቅ የሚረዱ ምርቶችን ለማምረት በሂደት ላይ መሆኑን የገለጹት አማካሪው፤ በቂሊንጦ የሚገነባው ይህ ፕሮጀክት በ105 ሚሊየን ብር የተከፈለ መነሻ ካፒታል ነው። አጠቃላይ ፕሮጀክቱ የሚወስደው 108 ቢሊየን ብር መሆኑን የገለጹት አቶ አባይነህ፤ ፕሮጀክቱ የሚገነባው ከኢትዮጵያ ልማት ባንክ በሚገኝ ብድር መሆኑንም አስታውቀዋል።

ደብረ ብርሃን የሚገኘው ፕሮጀክት ተጠናቆ ስራ ሲጀምር ለአንድ ሺ 300 ስራ ፈላጊዎች የስራ እድል እንደሚፈጥር የገለጹት አማካሪው፤ በተመሳሳይ የቂሊንጦው ግንባታ ሲጀምር በፈረቃ በትንሹ ለ200 ስራ ፈላጊዎች የስራ ዕድል ይፈጠራል ብለዋል። ፕሮጀክቱ ተጠናቆ ወደ ስራ ሲገባ 30 በመቶ የሚሆነው ምርቱን ለጎረቤት አገራት እንደሚያቀርብም ይጠበቃል።

በህንድ ሙባይ የሚገኘው ካሊማ ፋርማ ኢንጂነሪንግ የኢንዱስትሪ ማሽነሪዎችን የሚያመርት ሲሆን፤ በተጨማሪም ለንጽህና መጠበቂያና ለፋርማስቲካል ኢንዱስትሪዎች ግብዓቶችን በማምረት ይታወቃል።

# ሕገ-ወጥ የውጭ ምንዛሬና የወርቅ ንግድን በመጠቀም ወሮታ የሚከፈልበት አሰራር ተግባራዊ ሆነ

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

አዲስ አበባ፡- ሕገ-ወጥ የውጭ ምንዛሬና የወርቅ ንግድ ላይ የተሰማሩ አካላትን ለመጠቆም የሚያስችልና ወሮታ የሚከፈልበት የአሰራር ሥርዓት መዘርጋቱን የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ አስታወቀ።

የብሔራዊ ባንክ ሥራ ኃላፊዎች በተዘጋጀው መመሪያ ዙሪያ ትናንት ማብራሪያ ሲሰጡ፤ የባንኩ የሕግ አገልግሎት ዳይሬክተር መስፍን ጌታቸው እንዳሉት፤ የብር ኖት በሕገ-ወጥ መልኩ ከፋይናንስ ተቋማት ውጭ ማከማቸትና ማዘዋወር፣ በሕገ- ወጥ የወርቅ ግብይትና ዝውውር ላይ መሰማራት፣ በሕገ-ወጥ የውጭ ምንዛሬና ግብይት ላይ መሰማራት በአዋጁ መሰረት የተከለከሉ ናቸው።



ሐሰተኛ የገንዘብ ኖት ሕትመትና ዝውውርም በወንጀል የሚያስጠይቅ መሆኑን ጠቅሰው፤ በእነዚህና መሰል የወንጀል ተግባራት የተሰማሩ አካላትን በተመለከተ በአካል፣ በስልክ፣ በኢ-ሜይል፣ በፋክስና በሌሎችም መረጃ የሚተላለፍባቸው መንገዶች ጥቆማ መስጠት የሚያስችል አሰራር መዘርጋቱን ተናግረዋል።

በመሆኑም በወንጀሉ ዙሪያ ለመጠቆም የሚያስችልና ወሮታ የሚከፈልበት የአሰራር ሥርዓት መዘርጋቱን አብራርተዋል።

በዚህ ሂደት የጠቋሚዎቹን ደኅንነት ለመጠበቅ የመረጃ ሰጪዎች ሁኔታ በምስጢር እንደሚያዝ ገልጸው፤ ጠቋሚዎችን ከስጋት ነጻ የሚያደርግ አሰራር መሆኑን ተናግረዋል።

በጥቆማው መሰረት መረጃውን አጣርቶ ሕጋዊ እርምጃ ለመውሰድ ብሔራዊ ባንክ ከፍትህ ሚኒስቴር፣ ከፌዴራል ፖሊስ፣ ከብሔራዊ መረጃና ደኅንነት አገልግሎት እንዲሁም ከፋይናንስ ደኅንነት አገልግሎት የተውጣጣ ግብር ኃይል በጋራ ይሰራል ብለዋል።

ለጠቋሚዎች የወሮታ ክፍያ አሰራር ተግባራዊ መደረጉን ጠቅሰው፤ ለዚህም ጠቋሚዎች በቅድሚያ በኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ የተዘጋጀውን ቅጽ መሙላት የሚጠበቅባቸው መሆኑን አስረድተዋል።

በሕገ-ወጥ ድርጊት ምክንያት የተያዘው ጥሬ ብር፣ የውጭ አገር ገንዘብ ወይም ወርቅ ከሆነ ለጠቋሚው ከተያዘው 15 በመቶ የሚከፈለው ይሆናልም ነው የተባለው።

ለግለሰቦች በቀን ከ100 ሺህ ብር በላይ መያዝ፣ ለተቋማትም በቀን ከ200 ሺህ ብር በላይ መያዝ የተከለከለ ነው ተብሏል።

ይህን መመሪያ የተላለፈን ግለሰብ ወይም ተቋም ለጠቆመ ምስጢራዊነቱ በተጠበቀ መልኩ ወሮታው ተፈጻሚ እንደሚሆን ተገልጿል።

ጥፋተኛ ሆኖ የተገኘ ግለሰብም በከባድ የኢኮኖሚ ወንጀል እስከ 15 ዓመት ጽኑ እስራት እንደሚቀጣ ነው የተመላከተው።

ከሐሰተኛ ገንዘብ ኖት ሕትመትና ዝውውር ጋር በተያያዘ ደግሞ እንደተያዘው ገንዘብ ዓይነትና መጠን ከ20 ሺህ እስከ 200 ሺህ ብር ወሮታ ክፍያ ይፈጸማል መባሉን ኢዜአ ዘግቧል።

በኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ የለውጥ ማኔጅመንት ዕቅድና ኮሙዩኒኬሽን ዳይሬክተር አባተ ምትኩ በዘርፉ የሚስተዋለው ሕገ-ወጥ እንቅስቃሴ እየተባባሰ በመምጣቱ የክትትልና ቁጥጥር ሂደቱ መጠናከር ያለበት መሆኑን ተናግረዋል።

በዚህ ዙሪያ በተለይም መገናኛ ብዙኃን የሕብተረሰቡን ግንዛቤ ማሳደግ፣ መረጃ መስጠትና የወንጀሉን አስከፊነት ለማስገንዘብ በትኩረት መሥራት አለባቸው ብለዋል።



# አገራዊ ምክክሩ ለዘመናት ሲንከባለሉ የመጡ ችግሮችን በመፍታት የተረጋጋች አገር ለመፍጠር ያስችላል

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

አዲስ አበባ፡- አገራዊ ምክክሩ ለዘመናት ሲንከባለሉ የመጡ ችግሮችን በመፍታት የተረጋጋች አገር ለመፍጠር የላቀ ድርሻ እንዳለው የኢትዮጵያ አገራዊ ምክክር ኮሚሽን አስታወቀ።

የኮሚሽኑ ምክትል ዋና ኮሚሽነር ወይዘሮ ሂሩት ገብረስላሴ በረቂቅ የተሳታፊዎችና አጀንዳ ማሰባሰብ አሰራር ዙሪያ ኮሚሽኑ በአርባምንጭ ከተማ ትናንት ባካሄደው ውይይት ላይ እንደገለጹት፤ በአገሪቱ ወሳኝ በሆኑና የአገሪቱን ሠላምና መረጋጋት ላይ አወንታዊ አስተዋፅኦ የሚያበረክቱ፣ በህብረተሰቡና በፖለቲካ ልሂቃን መካከል ያሉ ልዩነቶችን ለማጥበብ የሚያስችሉ ተግባራት ተጀምረዋል። ከእነዚህም መካከል ተስፋ የተጣለበት አገራዊ ምክክር ለዘመናት ሲንከባለሉ የመጡ ችግሮችን በመፍታት የተረጋጋች አገር ለመፍጠር የላቀ ድርሻ ይኖረዋል ብለዋል።

የካቲት 2014 በይፋ የተቋቋመው አገራዊ የምክክር ኮሚሽን ሥራዎቹን በአራት ምዕራፍ ከፋፍሎ እየተገበረ መቆየቱን አስታውሰው፤ ስለ ኮሚሽኑ ማቋቋሚያ አዋጅና ተያያዥ ርዕሰ ጉዳዮች ዙሪያ ግንዛቤ ሲያስጨብጥ መቆየቱን ጠቁመዋል።

ኮሚሽኑ በአሁኑ ወቅት ለሚካሄዱ ውይይቶችና ምክክሮች በብቃትና በገለልተኝነት የሚያመቻች መሆኑን የተናገሩት ወይዘሮ ሂሩት፤ ለዚህም ሰብሳቢዎችና አወያዮች የሚመረጡበት ስርዓትና መመዘኛ ነጥቦች መዘጋጀታቸውን ጨምረው ገልጸዋል። ውይይቱ ለሁለት ቀናት እንደሚቆይም ተጠቁሟል።

ዜና



# ምርጫ ቦርድ እና የኢትዮጵያ የፖለቲካ ፓርቲዎች የጋራ ምክር ቤት ስምምነት ተፈራረሙ

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

አዲስ አበባ፡- በኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ እና በኢትዮጵያ የፖለቲካ ፓርቲዎች የጋራ ምክር ቤት መካከል የጋራ ስምምነት ሠነድ ተፈረመ።

ስምምነቱ በኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ዋና ሰብሳቢ ብርቱካን ሚደቅሳ እና በጋራ ምክር ቤቱ ዋና ሰብሳቢ መብራቱ አለሙ (ዶ/ር) አማካኝነት ትናንት ጥቅምት 9 ቀን 2015 ተፈርሟል።

የመግባቢያ ስምምነት ሠነዱ ምክር ቤቱ መጋቢት 2011 ዓ.ም በፓርቲዎች መካከል የተፈረመውን የቃል ኪዳን ሠነድ አላማ ለማሳካት ለሚያደርጋቸው እንቅስቃሴዎች ቦርዱ ድጋፍ ለማድረግ ይችል ዘንድ፤ እንዲሁም ምክር ቤቱም የሚሰጠውን ድጋፍ በመግባቢያ ሠነዱ ውስጥ በተጣለበት ኃላፊነት መሠረት ለታለመለት ዓላማ ማዋሉን ለማረጋገጥ መሆኑን ቦርዱ አስታውቋል።

በዚህ የመግባቢያ ስምምነት መሠረት ቦርዱ ለምክር ቤቱ ድጋፍ ከሚያደርግባቸውና ከምክር ቤቱ ጋር የጋራ መግባባት ከተደረሰባቸው መካከል የምክር ቤቱ ገጽታ ግንባታ ስራዎች (ለመጽሔት ዝግጅት፤ ለማስታወቂያና ተዛማጅ ስራዎች )፣ፕሬስ ኮንፈረንስ ማዘጋጀት፣ ለአስተዳደራዊ ወጪዎች፤ ማለትም ለሥራ ፈጻሚዎች የሚውሉ የተለያዩ ወጪዎች ተግባራትን ለማከናወን የሚሆን፤ ምክር ቤቱ ወደ ክልል የጋራ ምክር ቤቶች ድጋፍና ክትትል ለሚያደርጋቸው እንቅስቃሴዎች የሚደረግ ወጪን መሸፈን ይጠቀሳሉ።

ቦርዱ ቀደም ሲል በሕግ የተሰጠውን ሥልጣንና ኃላፊነት ማለትም የፖለቲካ ፓርቲዎችን የመከታተል እና የመደገፍ ኃላፊነት ያለበት እንደመሆኑ፤ ለእያንዳንዱ የፖለቲካ ፓርቲ ከሚያደርገው ድጋፍ በተጨማሪ የፖለቲካ ፓርቲዎች ስብስብ የሆነውን ምክር ቤት በመደገፍ የበለጠ ተደራሽ እና ፓርቲዎች በዴሞክራሲ ግንባታ፣ የሕግ የበላይነት መስፈን እና በሰላም መረጋገጥ ላይ ያላቸውን ሚና የበለጠ ለማጎልበት በማሰብ ለጋራ ምክር ቤቱ ቢሮና አስፈላጊ የቢሮ ቁሳቁሶችን፤ እንዲሁም ለሥራ እንቅስቃሴ የሚረዳ የተሽከርካሪ ድጋፍ ማድረጉ ይታወቃል ብሏል።

# መንግሥት የሰሜኑን...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

መርህ ከምንጊዜውም በላይ መንግሥት ለሰላም ቅድሚያ በመስጠት እየሰራ መሆኑን የጠቀሱት አቶ አደም፤ በኢትዮጵያ የሚስተዋሉ ችግሮችን በዘላቂነት ለመፍታት የመንግሥት የሰላም እጆች አይታጠፉም ነው ያሉት።

በአንጻሩ መርህን ባልተከተለ አካሄድ በኢትዮጵያ የውስጥ ጉዳይ ጣልቃ የሚገቡ የውጭ ኃይሎች እንዳሉ ጠቅሰው፤ በውስጥ ያሉ የሽብር ቡድኖችም በጥፋት እንቅስቃሴያቸው ቀጥለውበታል ብለዋል።

በመሆኑም የኢትዮጵያን ሉዓላዊነትና የግዛት አንድነት የሚጋፋ ማንኛውንም እኩይ ዓላማን ይዞ ለሚንቀሳቀስ ኃይል መንግሥት ሕግ የማስከበር ኃላፊነት እንዳለበት ነው የገለጹት።

ለኢትዮጵያ ዘላቂ ሰላም የራስን ችግር በራስ የመፍታት ካልሆነም የአፍሪካን ችግር በአፍሪካ ለመፍታት የሚደረገውን ጥረት ማገዝ እንጂ ማደናቀፍ ተገቢ እንዳልሆነ ገልጸዋል።

አሸባሪው ትሕነግ ከኢትዮጵያ ታሪካዊ ጠላቶች አጀንዳ አንግቦ አገር ለማፍረስ የቻለውን ሁሉ ጥረት ቢያደርግም በመንግሥትና በሕዝቡ የጋራ ጥረት እየከሸፈ ነው ሲሉም ተናግረዋል።

# በኦሮሚያ ክልል...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

ባለፉት ዓመታት ከውጭ የሚገባውን የስንዴ ምርት ሙሉ ለሙሉ እንተካለን ስንል እንደህልም ቢታይም እንደ አገር አሁን ማሳካት ችለናል ያሉት ርዕሰ መስተዳድሩ፤በዚህም አንድ ቢሊዮን ዶላር ማዳን ተችሏል። ይህ ትልቅ ስኬት ነው። ዘንድሮም ለውጪ ገበያ የሚቀርበውን የስንዴ ምርት እናሳካዋለን ብለዋል።

በመኸርና የበጋ ስንዴ ልማት የሚሸፈነውን መሬት በማስፋፋትና ቴክኖሎጂን በመጠቀም እንደ አገር ምርትና ምርታማነትን ለማሳደግ በተሰራው ስራም ከፍተኛ ውጤት መገኘቱን ገልጸው፤በኦሮሚያ የዛሬ ሶስት ዓመት በመኸር የምርት ዘመን በስንዴ የሚለማው መሬት 800ሺህ ሄክታር ነበር። ካቻምና አንድ ነጥብ ሁለት ሚሊዮን ሄክታር መሬት በስንዴ እንዲለማ አድርገናል። ዘንድሮ አንድ ነጥብ ሰባት ሚሊዮን ሄክታር መሬት በመኸር ምርት ዘመን የለማ ስንዴ በመሰብሰብ ላይ እንገኛለን ብለዋል።

በኢትዮጵያ በስንዴ ልማት ብዙ ተስፋና ስኬት የተገኘበት መሆኑን አመልክተው፤ይህን ስኬት በሌሎች ዘርፎች ለመድገም ርብርብ ማድረግ እንደሚያስፈልግም ጠቁመዋል።

የኢትዮጵያን ገጽታ የስንዴ ምርትን በተመለከተ ያለውን እይታ ለመቀየር የሚያስችሉ ውጤታማ ስራዎች እየተሰሩ እንደሚገኙም አመልክተዋል።

የውሃ መሳቢያ ሞተር ፤ትራክተር፤ ኮምባይነር፤ ምርጥ ዘርና ሌሎች የቴክኖሎጂ ውጤቶችን በመጠቀም ምርትና ምርታማነቱ እንዲጨምር ይደርጋል ያሉት አቶ ሽመልስ፤የግብርና ዘርፉን ለማዘመንና ውጤታማነቱን ለማሳደግ አዳዲስ የቴክኖሎጂ አማራጮችን ለክልላችን አርሶ አደሮች ለማቅረብ የምናደርገውን ጥረት አጠናክረን እንቀጥላለን ሲሉ ገልጸዋል።

በአገር አቀፍ ደረጃ ዘንድሮ በበጋ ስንዴ አንድ ነጥብ ሶስት ሚሊዮን ሄክታር መሬት በማልማት 52 ሚሊዮን ኩንታል ስንዴ ለማግኘት ዕቅድ ተይዟል። ክልሎች ከአላቸው የበጋ ስንዴ የማልማት አቅም አንጻርም ኦሮሚያ ክልል ድርሻ 74 ነጥብ አንድ መሆኑን የግብርና ሚኒስቴር መረጃ ያመለክታል።

# ኢትዮጵያ የዲፕሎማሲ...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

ጥቅማቸውን ለማስከበር የሚታየውን የምዕራባውያን ፍላጎት ልታከሽፍ ይገባል።

ዓለም አቀፍ ድርጅቶች እና ዓለም አቀፍ ድንጋጌዎች የውጭ ኃይሎቹ የራሳቸውን እሳቤ የሚያስፋፉባቸው መንገዶች እንደሆኑ የጠቆሙት ረዳት ፕሮፌሰሩ፤ በሌላ በኩል እነዚህ ድንጋጌዎች እና ተቋማት የሰብዓዊ ተቆርቋሪዎች መስለው እንደሚታዩ ጠቁመዋል።

በመሆኑም ኢትዮጵያ የዲፕሎማሲ መርሆዎቿን በመጠቀም የራሷን ጥቅም ባስከበረ መልኩ ከየሀገራቱ ጋር የተግባቦት ሥራዎችን በመሥራት ምዕራባዊያን በቀንዱ ሀገራት ላይ ያላቸውን ጥቅም የማስከበር ሩጫ ለማክሸፍ መሥራት ይኖርባታል ሲሉ ጠቅሰዋል።

በተመሳሳይ የተባበሩት መንግሥታት ድርጅትን ጨምሮ የምዕራባዊያንን የበላይነት ማስጠበቂያ መሣሪያዎች ሆነው የሚያገለግሉት ዓለም አቀፍ ተቋማትና ድንጋጌዎች ገለልተኝነታቸው አጠያያቂ ነው ያሉት ረዳት ፕሮፌሰሩ፤ ለአብነት የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት በተደጋጋሚ ጊዜ በተለይም ኢትዮጵያ ላይ ሰብዓዊ መብትን እንደ ፖለቲካ ጣልቃ ገብነት ማስፈፀሚያ ሲጠቀምበት መታየቱን አንስተዋል።

በሌላ በኩል እነዚህ የውጭ ኃይሎች ዓለም አቀፍ ድንጋጌዎችንና ተቋማትን በመጠቀም የአፍሪካ ቀንድ ጥቅማቸውን ከማስከበር አልፈው በኢትዮጵያ የውስጥ ጉዳይ ጣልቃ ለመግባት እንደሚጠቀሙባቸውም ረዳት ፕሮፌሰሩ አብራርተዋል።

ኃያላን ሀገራት በኢትዮጵያ ላይ ከድሮ ለየት ያለ አቋማቸውን ባላቸው ዲፕሎማሲ እና በዓለም አቀፍ መድረኮች ላይ ማሳየት ጀምረዋል ያሉት ረዳት ፕሮፌሰር ያየሁ፤ በተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ባሉ የተለያዩ የሥራ ክፍሎች አማካኝነት በኢትዮጵያ ላይ ጫና ሲያደርጉ መታየታቸውም ጥቅማቸውን ለማስከበር የሚያደርጉት ሩጫ ማሳያ መሆኑን ነው የተናገሩት።

የተባበሩት መንግሥታት ድርጅትም ይሁን የፀጥታው ምክር ቤት ኢትዮጵያን አጀንዳ በማድረግ እስከ 20 የሚደርሱ ጉባዔዎችን ማካሄዳቸውን ተናግረው፤ ኢትዮጵያም አቋሟን ስታሳውቅ የዲፕሎማሲ መርሆዎችን መሰረት በማድረግ እና ከምንም በላይ ብሔራዊ ጥቅሟን መሰረት ባደረገ እንዲሁም አንድነቷን ለማስጠበቅ በሚደረግ ጥረት ነው ብለዋል።

ምዕራባዊያን ዓለም አቀፍ ድንጋጌዎችን የአንድን ሉአላዊ ሀገር ጣልቃ መግቢያነት የሚጠቀሙት የሉአላዊነት አንዱ መገለጫ የሆነውን በአንድ ሀገር ውስጥ ከምንም በላይ የፖሊሲም ይሁን ሌሎች ፍላጎቶችን ከመንግሥት ባፈነገጠ መልኩ ጫና ማድረግም ሆነ ጣልቃ መግባት እንደማይቻል ግንዛቤው እያላቸው ነው ሲሉም ገልፀዋል።

በአንድ ሉአላዊ ሀገር ጣልቃ መግባት የሚፈቀደውም ሉአላዊ ከሆነው ሀገር ጋር ትብብር በመጠየቅ ነው ሲሉም አክለዋል።

ከሉአላዊ ሀገር ጋር በሚደረግ ስምምነት የሚደረገው የጣልቃ ገብነት ቢሆን ሌሎች የገለልተኝነት መርሆዎች መሟላት እንደሚገባቸው ረዳት ፕሮፌሰሩ ተናግረዋል።

በኢትዮጵያ ውስጥ የትኛውም አይነት የሰብዓዊ እርዳታም ይሁን የጦር ወንጀል ሪፖርት ግኝት ቢኖርም እንኳን በሉአላዊ ሀገሩ የትብብር ጥያቄ የሚገባው ዓለም አቀፍ ድርጅት ገለልተኛ መሆን ሲችል ብቻ ነው ሲሉም ጠቅሰዋል። በተጨማሪም ጣልቃ የሚገባው ዓለም አቀፍ ድርጅት በእኩልነት መርህ መቆም መቻል ይኖርበታል ብለዋል።

# ርዕሰ አንቀፅ

## የትግራይ ህዝብ በብዙ መስዋእትነት እየተገኘ ያለውን ነጻነቱን የማጽናት ኃላፊነት አለበት !

የትግራይ ህዝብ ከሀምሳ አመታት በላይ በአሸባሪው ትህነግ የሽብር አገዛዝ ቀንበር ውስጥ አሳልፏል። በእነዚህ አመታት ክልሉ የጦርነት አውድማ ከመሆን ባለፈ አስከፊ የረሀብ ወቅቶችም ተመላልሰውበታል። ሕዝቡ እንደ ህዝብ ፍጹም ነጻነቱን ተገፎ የቡድኑ የግል ንብረት እስኪመስል ድረስ ሰብአዊ መብቶቹን በአደባባይ ተነፍጎ ለመኖር ተገድዷል።

ቡድኑ በአንድ በኩል ገና ሲፈጠር አንስቶ በተጠናወተው የዘረኝነት እርግማን የተለያዩ የጥፋት ትርክቶችን በመፍጠር፣ በሌላ በኩል እጅግ ጠንካራ ማህበራዊ፣ ፖለቲካዊ እና ሚስጥራዊ የአፈና መዋቅሮችን በማደራጀት ሕዝቡ የራሱን እድል በራሱ እንዳይወስን አድርጎታል። በየትኛውም መንገድ አማራጭ አልባ ህይወት እንዲኖር አስገድዶታል ።

የደርግን ስርአት ለማስወገድ በነጻነት ስም የትግራይን ህዝብ ከጎኑ በማሰለፍ በአስር ሺዎች የሚቆጠሩ የትግራይ ልጆችን ለህልፈት፣ በመቶ ሺዎች የሚቆጠሩትን ለአካል ጉዳት ዳርጎ ወደ ስልጣን ከመጣ በኋላም የአገዛዝ ቀንበሩን በማጥበቅ ሕዝቡ ለገዛ ህይወቱ ባይተዋር እንዲሆን አድርጎታል።

ቡድኑ በበረሀ ትግሉ የተለየ አመለካከት፣ ለትግራይ ህዝብ የተሻለ መጪ ተስፋ ያላቸውን ታጋዮች ሳይቀር በመግደል፤ በማስገደልና በማሳደድ የቆሸሸ ታሪክ ያለው ነው። ለቡድኑ ሀሳብ ያልተገዙ ግለሰቦችን የቤተሰብ መሰረት ከማናጋት ጀምሮ ከፍ ያሉ ስነልቦናዊ ጫናዎችን በመፍጠር የራሳቸውን የሕይወት ምርጫ እንዳይኖራቸው በማድረግ እኩይ ተግባርም ይታወቃል።

የበረሀ ትግሉ በትግራይ ሕዝብ መስዋእትነት በድል ከተጠናቀቀ ማግስት ጀምሮም በትግሉ ከፍ ያለ ዋጋ የከፈሉ ታጋዮችን ጨምሮ የቡድኑን ከፍተኛ አመራሮች በሴራ አስወግዶ የትግሉ የመስዋእትነት ፍጻሜም የጥቂት ግለሰቦች /የአንድ ቤተሰብ/ ገፀ መደብ በመፍጠር ተጠናቋል።

ቡድኑ በቀጣይም የሄደበት መንገድ የዚህን ቡድን ሕልውና በማስቀጠል ላይ ያተኮረ ሲሆን፣ ለዚህም የትግራይን ህዝብ እንደ ህዝብ መያዧ አድርጎ ሲጠቀምበት ቆይቷል። የዘመናት ታሪክ ያለውን ይህንን ህዝብ በመንደር አስተሳሰብ ከመበከል ጀምሮ የግድ የአስተሳሰቡ ባሪያ እንዲሆን ለማድረግ ብዙ ርቀት ተጉዟል።

በስልጣን ላይ በቆየባቸው 27 አመታት የትግራይ ህዝብ በምንም አይነት መልኩ ለአማራጭ አስተሳሰቦች እድል ፋንታ እንዳይኖረው ከማድረግ ጀምሮ፤ ስለ ህዝቡ አማራጭ አስተሳሰብ ያላቸውን በማሳደድ፤ በማሰርና በመግደል ጭምሮ የቡድኑ እኩይ አስተሳሰብ ሳይፈልግ በግድ ባሪያ እንዲሆን አድርጎታል።

በህዝባዊ እንቢተኛነት ከስልጣን ከተወገደ ማግስት ጀምሮም ቀደም ሲል በፈጠራቸው ጠንካራ ማህበራዊ፣ ፖለቲካዊ እና ሚስጥራዊ የአፈና መዋቅሮች በመጠቀም እድሜውን ለማራዘም ከተቻለም ወደ ስልጣን ለመመለስ የትግራይን ህዝብ ላልተፈለገ ጦርነት አሳልፎ ሰጥቶታል።

የትግራይ ወጣት እንደ ሰው የራሱ እጣፈንታ የሌለው፣ ተምጦ የሚወለደው ቡድኑ ለሚፈጥራቸው ጦርነቶች ጥይት ማብረጃ ይመስል፣ ወጣቱን ቆሞ ቀር በሆነው አስተሳሰቡና በዘረኝነት መርዙ በታሸው ፕሮፓጋንዳው፣ በዘፈንና በፉከራ በማነሳሳት ለእልቂት ዳርጎታል።

ይህን ቡድኑ ከውልደቱ ጀምሮ የተጠናወተው የእልቂት እኩይ ተግባር ባለፉት ሁለት አመታት የቱን ያህል የትግራይን ህዝብ ዋጋ እንዳስከፈለው ከትግራይ ህዝብ በላይ፣ እልቂቱ የፈጠረውን መከራና ስቃይ ከትግራይ እናቶች በላይ ሊመሰከር የሚችል አይኖርም ።

የትግራይ ህዝብ በለውጡ የነበረውን ተስፋ ቡድኑ ጦር ሰብቆ ወደ ቅዥትነት በመለወጥ፣ በብዙ ፈተና ውስጥ ሆኖ አምጦ የወለዳቸውንና ለተሻለ ተስፋ ያጫቸውን ልጆቹን እየነጠቀ ለእልቂት ዳርጓል፤ እየዳረገም ነው። “ኢትዮጵያን ለማፍረስ እስከ ሲኦል እንወርዳለን“ በሚለው ፍጹም የሆነ የጥፋት ተልእኮው የትግራይን ህዝብ ሁለንተናዊ ለሆነ ቀውስ ዳርጓል። ለህዝቡ የሚመጣውን የእርዳታ እህል ሳይቀር ከህዝቡ ጉሮሮ በመንጠቅ ህዝቡ በረሀብ ጠኔ እንዲሰቃይ በማድረግ በዚህም የፖለቲካ ቁማር ተጫውቷል።

ቡድኑ በትግራይ ህዝብ ላይ ከአምስት አስርት አመታት በላይ እያደረሰ ያለውን ግፍ ለማስቆም መላው የኢትዮጵያ ህዝብ አንድ ሆኖ መንቀሳቀስ ከጀመረ ውሎ አድሯል። በቡድኑ ላይ እያስመዘገበ ያለው ድልም በየእለቱ እየጎለበተ፣ የትግራይ ሕዝብ የነጻነት አየር የሚተነፍስበትን ጊዜም ከመቼውም ጊዜ በላይ እያቀረበው ይገኛል።

አሁን ሁሉም ነገር መልኩን እየቀየረ ነው። ጥምር ጦሩ የቡድኑን ግልፅ ጦርነቶች እና የተለያዩ ትንኮሳዎች በመቋቋም የትግራይን ሕዝብ ከዚህ አሸባሪ ቡድን ባርነት ለመታደግ ከፍተኛ መስዋእትነት በመክፈል የህዝቡን ነጻነት ማብሰሪያውን ጊዜ እያቀረበው ነው። በአንዳንድ ቦታዎችም የብስራት ዜናው ተሰምቷል።

የትግራይ ህዝብ ከሁሉም በላይ ይህን በብዙ መስዋእትነት እየተገኘ ያለ ነጻነት በማጽናት፣ የራሱን እድል በራሱ የሚወስንበትን እድል በእጁ ለማስገባት ከጥምር ጦሩ ጋር መቆም ይጠበቅበታል። ይህ ለእውነተኛ ነጻነት ሊከፍለው የሚገባው ትንሹ ዋጋ ነው። ይህንን ለማድረግ ደግሞ የትግራይ ህዝብ በቡድኑ የደረሰበት ግፍና በደል በራሱ በቂ እና ከበቂ በላይ ነው።


# አዲስ ዘመን

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

**የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስኪያጅ**

ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22

**ዋና አዘጋጅ**

አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

**አድራሻ**

ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ

ወረዳ 06

የቤት ቁጥር 319

ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et

ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

**የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር**

ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ

ስልክ:- 011 126 4240

Email:- wendweson.shimelis@press.et

wendwesonshimelis@gmail.com

**የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች**

- ወርቁ ማሩ
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- አልማዝ አያሌው
- እስማኤል አረቦ

**የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ**

ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com

ስልክ - 011-126-43-41

ፋክስ - 011-811-13-15

**የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል**

ስልክ ቁጥር - 011-156-98-73

ፋክስ - 011-126-58-12

**የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ**

ስልክ - 011-1-26-43-39

**ማከፋፈያ**

ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70


ነፃ ሃሳብ

# ትኩረት ለኑሮ ውድነት

ክብርት ፕሬዚዳንት የሁለቱ ምክር ቤቶች የጋራ መክፈቻ ስነ-ስርዓት ላይ ባደረጉት ንግግር፤ እንደ አምናውና ካች አምናው የተባባሰው የኑሮ ውድነት በዜጎች ላይ ከፍተኛ ጫና መፍጠሩን ፤ የዋጋ ግሽበት የማክሮ ኢኮኖሚው ማነቆ ሆኖ መታየቱን እና በሚቀጥለው አመት የዋጋ ንረትን የማረጋጋት ስራ ላይ ትኩረተ ይሰጣል ቢሉም መንግስት በተያዘው የበጀት አመት ከአምናው የተለየ መንገድ እንደሚከተል አልነገሩንም። ግልጽ ዕቅድ እንዳለውም አልጠቆሙንም።

ጎንደር ላይ በማክሮ ኢኮኖሚ አፈጻጸም ላይ የመከረው ካቢኔ፤ የአዲስ አበባ ከተማ ምክር ቤት ባደረገው ጉባኤ፤ የዋጋ ግሽበቱና የኑሮ ውድነቱ ላይ ወሳኝ መታጠፊያ ሊሆኑ የሚችሉ ውሳኔዎች ሊተላለፉ ይችላሉ ብዬ ብጠብቅም አንገብጋቢ ችግርነቱን የሚመጥን የተለየ ትኩረት አለማግኘቱና አቅጣጫ አለመቀመጡ ክፉኛ አሳስቦኛል። ብሔራዊ ባንክም በበጀት አመቱ የዋጋ ግሽበቱንና የኑሮ ውድነቱን የሚያስከኑ እርምጃዎችን ይወስዳል ብዬ ብጠብቅም አልሆነም።

የንግድና ቀጣናዊ ትስስር ሚኒስቴርም ታክቲካዊና ስትራቴጂካዊ መፍትሔ ይዞ ይመጣል ብዬ ባስብም ከ”ሰንበት ገበያ”ባሻገርና እሳት ከማጥፋት ውጭ ይሄነው የሚባል ነገር ይዞ አልመጣም። እነዚህን ሁሉ ተቋማት አስተባብሮ መፍትሔ ይዞ ሊመጣ ይችላል ብዬ የጠበቅሁት የፕላንና ልማት ሚኒስቴርም ይዞት የመጣ አዲስ ነገር የለም። ይሄ ይሄ ነገር ተደማምሮ የመንግስት ነገር ግራ አጋብቶኛል። አወዛግቦኛል።

እንደ አምናው ዘንድሮም መልስ የሚሹ ጥያቄዎች በአእምሮዬ ጓዳ እየተዥጎደጎዱ ነው። ምንድን ነው እየሆነ ያለው!? የኑሮ ውድነቱና የዋጋ ግሽበቱ የደቀነውን አደጋ በቅጡ አልተረዳነውም ማለት ነው፤ ዛሬ በየተቋማቱ የተንሰራፋው ብልሹ አሰራርና ሙስና በአንድም በሌላ መልኩ ከኑሮ ውድነቱ ጋር መያያዙና በዚሁ ከቀጠለ የህልውናችን ፣ የሰላማችን፣ የደህንነታችንና የጸጥታችን ስጋት መሆኑስ አልተገለጠልንም ማለት ነው!? ስንት ዋጋ የከፈልንለት እየከፈልንለት ላለው ለውጥ ፈተና እንደሆነ አልገባንም ማለት ነው !? የእንግሊዙ የግሎሪየስ፣ የፈረንሳይ ፣ የራሽያው የጥቅምት ፣ የ1966ቱ ፣ የጸደይ አብዮቶች የተቀሰቀሱት በኢኮኖሚያዊ ቀውስ መሆኑን ዘነጋን ማለት ነው። ነው አብዮት አማረን!? አሁን ባለንበት ተጨባጭ ሁኔታ ኢኮኖሚው ከሰንደቃችን ፣ ከዜግነታችን ፣ ከኢትዮጵያዊነታችን ባልተናነሰ እንዲያውም በበለጠ የጋራ አካፋያችን መሆኑ እንደ ስፔስ ሳይንስ ከብዶናል ማለት ነው!? ከሀገራዊ ምክክሩ ባልተናነሰ ለብሔራዊ እርቅና ሀገራዊ መግባባት መንገድ እንደሚያቀና አልታየንም ማለት ነው !? ምንድን ነው የነካን !?በዚህ ያልደነገጥን በምን ልንደነግጥ ነው !? ተሯሩጠንና እጅ ለእጅ ተያይዘን በአንድነት ለመነሳት ከዚህ ፈተና በላይ ምን ይምጣልን !?ነው ወይስ እኔን ያልገባኝ ነገር አለ !?

የኑሮ ውድነት ፣ የዋጋ ግሽበት ፣ ስራ አጥነት ፣ ድህነትና ሌሎች ኢኮኖሚያዊ ችግሮች ብሔርና ሃይማኖት የላቸውም። አማራ ፣ ኦሮሞ ፣ ሲዳማ ፣ ሱማሌ ፣ ትግሬ ፣ ወዘተረፈ አይደሉም። ኦርቶዶክስ፣ እስላም ፣ ክርስቲያን ፣ ዋቄ ፈና ፣ ወዘተረፈ አይደሉም። ኢትዮጵያዊ ከፍ ሲልም ሰው ናቸው። እነዚህ የኢኮኖሚ መሠረታዊ አላባውያን ጤናማ ከሆኑ ሕዝብን በአዎንታ ሳይነጋገር አንድ ያደርጋሉ።

ሕዝብን ለድጋፍ ለአንድነትና ለፍቅር ያነሳሳሉ። በተቃራኒው እነዚህ መሠረታውያን ጤናማ ካልሆኑ ሕዝብን በአሉታ ማለትም ለተቃውሞና ለአመጽ በአንድነት ያነሳሳሉ። ይህ ኢኮኖሚያዊ ስኬታችንም ሆነ ውድቀታችን ከፖለቲካው በላይ ጉልበት እንዳለው ያስረዳል። ከፖለቲካችን በላይ ለኢኮኖሚያችን ልዩ ትኩረት መስጠት ግድ የሚለው ለዚህ ነው።

በኢኮኖሚያዊ ችግሮች የተነሳ ሕልውናችን አደጋ ላይ እየደወደቀ ቢሆንም ለመፍታት የሚደረገው ጥረት የችግሩን ስፋትና ጥልቀት የሚመጥን ፣ አጥጋቢና ወጥ አለመሆኑን ስመለከት ፤ ለዘላቂ መፍትሔ ተጨባጭ፣ ግልጽና ተፈጻሚ የአጭርና የረጅም ጊዜ ዕቅድ ሳጣ፤ የተለያዩ ጥያቄዎች ወደ አእምሮዬ እየተመላለሱ ነው።

የኑሮ ውድነቱና የዋጋ ግሽበቱ በዚህ ከቀጠለ ከሕወሓትና ሸኔ በላይ የህልውናችን አደጋ ፤ የደህንነትና የጸጥታ ስጋት የመሆን አሉታዊ አቅሙን በቅጡ ተረድተነዋል !? የኑሮ ውድነት ወላፈኑስ ያለ ልዩነት እኩል እየተሰማን ነው !? የመንግስት ባለስልጣናትስ የኑሮ ውድነት እንደ ተራው ሕዝብ ይሰማቸዋል !? ካልተሰማቸው እንዴት የመፍትሔው አካል ይሆናሉ !? እንዴትስ ለመፍትሔው ፖለቲካዊ ቁርጠኝነት ሊኖራቸው ይችላል !? እያልሁ እብሰከሰካለሁ።

ሁለት አስር አመታትን ያስቆጠረው የዋጋ ግሽበትና የኑሮ ውድነት የዜጋውን ኑሮ በብርቱ እየፈተነው፤ ከኢኮኖሚያዊ ችግርነት ወደለየለት ማህበራዊና ፖለቲካዊ ቀውስነት እንዳይባባስ እያሰጋ ይገኛል። በእንቅርት ላይ ጀሮ ደግፍ እንዲሉ ኢኮኖሚው ለቀደሙት 27 አመታት የአንድ ቡድንና የጭፍራው መጠቀሚያ በመሆኑ በተከሰተው ኢፍትሐዊ ተጠቃሚነት ላይ አሻጥር ፣ ጦርነትና አለመረጋጋት ተጨምሮበት ኑሮው አልቀመስ ብሏል።

በአናቱ የውጭ ምንዛሬ እጥረት ፣ የተራዘመ የግብይት ሰንሰለት ፣ ከገበሬ ማሳና ከጉልት እስከ ጅምላ አከፋፋይ የተሰገሰገ ደላላ ፣ የገነገነ ሙስና ፣ በግብይት ሰንሰለቱ የተንሰራፋው ስርዓት አልበኝነት፣ ዋጋን በአድማ መወሰን ፣ ምርትን በመደበቅ ሰው ሰራሽ እጥረት መፍጠር ፣ የፍላጎትና የአቅርቦት አለመጣጣም፣ የኑሮ ውድነቱን ለመከላከል በመንግስት ዘንድ ወጥ የሆነ ፖለቲካዊ ቁርጠኝነት አለመኖር ፣ የሎጅስቲክስ አገልግሎቱ ቀልጣፋ አለመሆን ፣ ወደብ አልባ በመሆናችን በየአመቱ ቢሊዮኖችን የምናወጣ እና ስለሙብቱ የሚቆረቆርና የሚጠይቅ ጠንካራ ሸማች አለመፈጠሩ እንደ ዚምባብዌና ቬኒዞላ ባይሆንም በሰዓታት ልዩነት ለሚተኮስ ከፍተኛ የዋጋ ግሽበት እንዲዳረግ መግፍኤ ሆኗል።

በየፍጆታ ሸቀጦች ላይ የሚታየው የዋጋ ግሽበት በሌሎች ምርቶችና አገልግሎቶች ላይ ግሽበትንና የኑሮ ውድነቱን እያባባሰው ይገኛል። አምስት ሊትር የምግብ ዘይት 930_1050 መግባቱ ሳያንስ፤ ሲያሻው ከገበያ ይጠፋል። የስንዴ ዱቄት በኪሎ 52 ብር ተተኩሷል። ዳቦ 5 ብር ገብቷል። ጤፍ እንደዚሁ በኪሎ 58ና ከዚያ በላይ ገብቷል። ቡና በኪሎ ወደ 500 ብር አሻቅቧል። ሽንኩርት ፣ ቲማቲም አጠቃላይ አትክልትና ፍራፍሬ አልቀመስ ብሏል። ቲማቲም ከሰሞኑ በአንጻራዊነት ቀንሷል ቢባልም እንደለመደው ተመልሶ ማሻቀቡ አይቀርም። እህልና ጥራጥሬውም ብሶበታል።

በዚህ ሳቢያ በመዋቅራዊና በተቋማዊ ችግር የተነሳ ጽኑ ታማሚ ሆኖ ለኖረው ኢኮኖሚ ሌላ ራስ ምታት ሆኖበታል። የለውጡ መንግስት ባለፉት አራት አመታት የኑሮ ውድነቱንና የዋጋ ግሽበቱን ወደ ነጠላ አኃዝ ለማውረድ ያደረገው ጥረት ውጤት ሊያስገኝ አልቻለም። አልበርት አነስታይን፤” ችግሩን በፈጠረው አስተሳሰብ፤ ችግር መፍታት አይቻልም፡፡ “እንዳለው ከሳጥኑና ከተለመደው አተያይ ወጣ ብሎ መፍትሔን ማማተር ግድ የሚለን አሳሳቢ ወቅት ላይ ብንገኝም፤ በሚያሳዝን ሁኔታ የሚፈለገውን ያህል እየሰራን አይደለም። እንዲያውም ችግሩ ከዕለት ወደ ዕለት እየተባባሰ ይገኛል።

ትኩረት ለኑሮ ...ወደ ገጽ 6 ዞሯል

ፖለቲካ እና ልዩ ልዩ

# ነፃ ሃሳብ



በቀምላቸው አበበ ይማም (ሞሼ ዳያን)
fenote1971@gmail.com

ቀምላቸው አበበ በአማራ ባህል፣ ቱሪዝምና ማስታወቂያ ቢሮ፤ በኢትዮጵያ ዜና አገልግሎት፤ በደቡብ መገናኛ ብዙኃን፤ በጋዜጠኝነትና በታሪክ ባለሙያነት ያገለገሉ ሲሆን፤ የደቡብ ኤፍ ኤምን ከባልደረቦቻቸው ጋር በመሆንም አቋቁመዋል።በፌዴራል ውሃ ስራዎች ኮንስትራክሽን ድርጅትና በአለ በጅምላ በኮሙዩኒኬሽን ዳይሬክተርነት አገልግለዋል። ከአአዩ በቋንቋና ታሪክ የመጀመሪያ ዲግሪያቸውን የሰሩ ሲሆን፤ በዚሁ ዩኒቨርሲቲ በጋዜጠኝነትና ኮሙዩኒኬሽን ሁለተኛ ዲግሪያቸውን በማጠናቀቅ ሳይ እያሉ ባጋጠማቸው ድንገተኛ ህመም ተስተጓጉሏል። ጥልቅ ሀሳብ ያዘሉ ወቅታዊ ጉዳዮች ሳይ የሚያተኩሩ ፁሑፎችን በማህበራዊ ሚዲያና በተለያዩ ጋዜጦች በማውጣት ይታወቃሉ።

# ትኩረት ስኑሮ...

ከ5ኛው ገጽ የዞረ

ከዝቅተኛ እስከ ከፍተኛ አንዳንድ ስነ ምግባር የጎደላቸው የመንግስት አመራሮች በዚህ ሕገ ወጥ የግብይት ስርዓት ተሳታፊ ሆነው መገኘታቸው ችግሩን እንዳወሳሰበው በዚያ ሰሞን የጸረ ሙስና ኮሚሽን ባካሄደው መድረክ ይፋ ሆኗል። የኦሮሚያ ክልል ርዕሰ መስተዳድር አቦ ሽመልስ አብዲሳ ባለፈው በተካሄደው ጨፌ ኦሮሚያ ይሄን ሀቅ ደግመውታል።

ከዚህ ውይይት በፊት የብሔራዊ መረጃና ደህንነት አገልግሎት ከሕዝብ በደረሰው ጥቆማና ባደረገው ክትትል መሠረት በየመጋዘኑ ተከዝነውና ተደብቀው የሚገኙ የምግብ ዘይት ፣ የስንዴ ዱቄት ሌሎች መሠረታዊ ሸቀጦችን ለመያዝ ሲንቀሳቀስ በየአካባቢው ያለ አመራር ለመተባበር እንዴት እግሩን ይጎትትና ለማደናቀፍም ይጥር እንደነበር መግለጹ የኮሚሽኑን ግኝት ተጨባጭ ያደርገዋል። መንግስት መዋቅሩን ካላጣራ ችግሩ ተባብሶ ስርዓቱም ሀገሪቱም አደጋ መሆኑ አይቀርም።

ይሄን ስርዓት አልባ የግብይት አሰራር መንግስት በማያዳግም ሁኔታ በሕግ አግባብ ስርዓት ሊያስይዘው ካልቻለ፤ ከማሳና ከጉልት እስከ ጅምላ አከፋፋይ የተሰገሰገውን ደላላ ከግብይት ሰንሰለቱ ካላስወጣ ፤ በድጎማ ከውጭ የሚገባን ዘይትና ስንዴ ለነጋዴው 70 በመቶ ፤ ለሸማቹ 30 በመቶ የነበረውን የስርጭት ቀመር ቀይሮ የተገላቢጦሽ ካላደረገ ፤ በመሠረታዊ ሸቀጦች ላይ ተመንና የትርፍ ሕዳግ ካልተቀመጠ ፤ ገበያውን ለውጭ ኩባንያዎች ክፍት ካላደረገው ፤ የንግድ ውድድርና የሸማቾች ጥበቃ ባለስልጣን ከንግድና ቀጣናዊ ትስስር ሚኒስቴር ጉያ ወጥቶ ስልጣኑና አደረጃጀቱ ተሻሽሎና ተጠናክሮ እንደገና ካልተደራጀ ፤ በግብይት ሒደቱና ሰንሰለቱ የሚስተዋለው አጉራ ዘለልነትና ውንብድና በሕግ የበላይነት ስርዓት እንዲይዝ ካልተደረገ፤ ችግሩ ተባብሶ ተባብሶ ወደለየለት የጸጥታና የደህንነት ችግር እንዳይባባስ ያሰጋል።

የዋጋ ግሽበቱ ከ40 በመቶ በላይ ተተኩሶና በየቀኑ እየተባባሰ ባለበት፤ የኑሮ ውድነቱ ከእጅ ወደ አፍ የነበረውን ኑሮ የማይቀመስ ካደረገው ፤ የስራ አጡ ቁጥር ከዕለት ወደዕለት እየተባባሰ እንዴት ስለኢኮኖሚያዊ ስኬት ማውራት ይቻላል። እንዴት ስለብልጽግና ማለም እንችላለን። መንግስትስ ከዚህ በላይ ምን አንገብጋቢ ጉዳይ አለው።

ይሄን ችግር ለመፍታት ፖለቲካዊ ቁርጠኝነት የማያሳየው ሕዝብ ሰልፍ እስኪ ወጣ ፤ አመጽ እስኪቀሰቀስ እየጠበቀ ነው። ጽዋው ሲሞላ ማጣፊያው እንደሚያጥር አያውቅም። ለምንድን ነው ይሄን አጉራ ዘለል የግብይት ስርዓት አደብ የማያሲዘው። መቼ ነው ከዘመቻና እሳት ከማጥፋት አሰራር የሚወጣው።

ከፍ ብሎ ለመግለጽ እንደተሞከረው ይሄን ኢኮኖሚያዊ ትብታብ አሁን ላለው መንግስት በእዳ የተላለፈለት እንጂ ለብቻው የፈጠረው አይደለም። ሆኖም ይሄን ትብታብ የመፍታት ኃላፊነት ትከሻው ላይ ወድቋል። እንደ ሰበብ/excuse/ ሊጠቀምበትም አይችልም። የጦርነቱ ጫናም ቀላል አይደለም።

ኮቪድና የራሽያ ጦርነት የፈጠረው የዋጋ ግሽበትም ተጽዕኖው ከባድ ነው። በባህሪው ገበያ ድንጉጥ ነውና። አይደለም ጦርነትና የግጭት አዙሪት የተሳሳተ ፖሊሲና የገበያ ትንበያ /speculation/ ገበያን ያስበረግጋል ። ሰሞኑን በእንግሊዝ የሆነውን ያስታውሷል። ይሄን ችግር ይበልጥ አሳሳቢ ያደረገው ሸማቹ ሕዝብ የመንግስት ቁርጠኝነት በሙላት ሲገለጥ አለማየቱ ነው። በዚህ የተነሳ ከዛሬው ነገ እንዳይከፋ አስፈርቶታል። አስጨንቆታል።

መንግስት ችግሩን በዘላቂነት ለመፍታት ከብር ለውጥ ጀምሮ ምርትንና ምርታማነትን ለማሳደግ ኩታ ገጠም ግብርናን ፣ የቆላ ስንዴን ፣ የግብርና ሜካናይዜሽንን ለማስፋፋት ፤ የአረንጓዴ አሻራን ለማሳካት ጥረት እያደረገ ነው። ሆኖም ምርት ማሳደግ ብቻውን መፍትሔ አይሆንም። ብልሹው የግብይት ስርዓት ካልታረም ፤ ደላላው ከገበያው ካልወጣ ፤ የኢኮኖሚ አሻጥረኞችን በሕግ ስርዓት ማስያዝ ካልተቻለ ፤ ማህበራዊ ስብራታችን ካልታጀለ ምርታማነታችን የቱንም ያህል ቢያድግ ከዚህ አዙሪት መቼም ቢሆን ሰብረን መውጣት አንችልም።

ሆኖም ይሄ ችግር በመንግስት የተናጠል ጥረት ብቻ አይፈታም። ዩኒቨርሲቲዎች ፣ እንደ የኢኮኖሚክስ ባለሙያዎች ያሉ ማህበራት ፣ የንግድና የዘርፍ ማህበራት ምክር ቤት ፣ የሀይማኖት ተቋማት፣ እንደ የኢትዮጵያ ሸማቾች መብት ተቆርቋሪ ድርጅት ያሉ የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶችና ሌሎች ባለድርሻ አካላት ተቀናጅተውና ተናበው መስራት ይጠበቅባቸዋል።

በተለይ ዩኒቨርሲቲዎችና እንደ የኢኮኖሚክስ ባለሙያዎች ማህበር ያሉ ተቋማት ይሄን ችግር ለመፍታት ጥናትና ምርምር በማድረግ የፖሊሲ ሀሳብ ማመላከትና ማመንጨት ይጠበቅባቸዋል። ይሄን ሁሉ ተቋም ተሸክመን የዋጋ ግሽበትና የኑሮ ውድነት እንዴት እንደ ስፔስ ሳይንስ እስከ መቼ እንደተወሳሰበብን ይቀጥላል። በእርግጥ የዋጋ ግሽበቱና የኑሮ ውድነቱ የተፈጠረው በምርት እጥረት ነው ፣ በግብይት ስርዓት ችግር ፣ እሴት በማይጨምር ደላላ ፣ በውጭ ምንዛሬ እጥረት ፣ በአልጠግብ ባይ ነጋዴዎች ፣ በዩክሬንና በራሽያ ጦርነት ፣ በኮቪድ 19 የተነሳ ፤ ወዘተረፈ ነው !? መልሱን በጥናት ማግኘት የማያዳግም መፍትሔ ለማስቀመጥ ይረዳል። በተረፈ ችግሩንና ተጠያቂነቱን ያለአድራሻ ማስቀመጥና ጣት መቀሳሰር ከተዘፈቅንበት አረንቋ አያወጣንም።

የውጭ ንግዳችን ከሀገር ውስጥ ገበያው ይልቅ የውጭ ምንዛሬ ማሳደድ ላይ መጠመዱ የኑሮ ውድነቱን አባብሶታል። የቅባት እህል ወደ ውጭ ልኮ የፓልም ድፍድፍ ገቢ ያደርጋል። አትክልትና ፍራፍሬ ወደ ውጭ ልኮ መድሀኒት በውጭ ምንዛሬ ያስገባል። የውጭ ንግድ መሠረቱንና አይነቱን ማስፋት ሲገባው ከሸማቹ ጉሮሮ እየቀማ ወደ ውጭ ይልካል። ይሄ የተፋለሰና ወለፈንዲ የሆነ አሰራር በጥናት ተፈትሾ መስተካከል አለበት። የሀገር ውስጥ ገበያን እያራቆቱ ምርትን ወደ ውጭ መላክ ለዜጋው አለማሰብ ነውና።

መንግስት የግብይት ስርዓቱን ስድ መልቀቁ የኑሮ ውድነቱንና የዋጋ ግሽበቱን አባብሶታል። ስለሆነም በሕግና በአደረጃጀት ነገ ዛሬ ሳይል ስርዓት ሊያሲዘውና የቁጥጥርና የክትትል አሰራር ሊዘረጋ ይገባል። የመኖሪያና የንግድ ቤት ኪራይ የኑሮ ውድነቱን ከሚያባብሱ ችግሮች ዋናው ነውና ተመን ሊወጣለት ይገባል። በመሠረታዊ ሸቀጦች የትርፍ ሕዳግና የዋጋ ተመን ሊወጣ ግድ ይላል።

ለሸማቾች ሲል ዘይት ፣ ስንዴና ሌሎች መሠረታዊ የምግብ ሸቀጦች ከቀረጥ ነጻ እንዲገቡ ቢያደርግም የቁጥጥርና የክትትል ስርዓት ስለአልዘረጋ ገበያው ሊረጋጋ አልቻለም። መንግስት በዚህ ፖሊሲው ከ27 ቢሊየን ብር በላይ ቢያጣም ለሸማቹ ጠብ ያለ ነገር የለም። ይህ ከፍ ብሎ ለመግለጽ እንደተሞከረው የሕግ ክፍተት መኖሩን ያሳያል። ስለሆነም በማያዳግም ሁኔታ ስርዓት ሊበጅለት ይገባል።

ትኩረት በኑሮ ውድነት አለንጋ እየተገረፈ ላለው ሸማች !!!

> ስርዓት አልባ የግብይት አሰራር መንግስት በማያዳግም ሁኔታ በሕግ አግባብ ስርዓት ሊያስይዘው ካልቻለ፤ ከማሳና ከጉልት እስከ ጅምላ አከፋፋይ የተሰገሰገውን ደላላ ከግብይት ሰንሰለቱ ካላስወጣ፤ በድጎማ ከውጭ የሚገባን ዘይትና ስንዴ ለነጋዴው 70 በመቶ ፤ ለሸማቹ 30 በመቶ የነበረውን የስርጭት ቀመር ቀይሮ የተገላቢጦሽ ካላደረገ ፤ በመሠረታዊ ሸቀጦች ላይ ተመንና የትርፍ ሕዳግ ካልተቀመጠ ፤ ገበያውን ለውጭ ኩባንያዎች ክፍት ካላደረገው፤ የንግድ ውድድርና የሸማቾች ጥበቃ ባለስልጣን ከንግድና ቀጣናዊ ትስስር ሚኒስቴር ጉያ ወጥቶ ስልጣኑና አደረጃጀቱ ተሻሽሎና ተጠናክሮ እንደገና ካልተደራጀ ፤ በግብይት ሒደቱና ሰንሰለቱ የሚስተዋለው አጉራ ዘለልነትና ውንብድና በሕግ የበላይነት ስርዓት እንዲይዝ ካልተደረገ፤ ችግሩ ተባብሶ ተባብሶ ወደለየለት የጸጥታና የደህንነት ችግር እንዳይባባስ ያሰጋል

# «አሸባሪው ትህነግ በየትኛውም መስፈርት የትግራይን ህዝብ ስነ ልቦና የሚመጥን ተግባር የለውም»

- አቶ ኃይለማርያም ሕሉፍ
የትዴፓ ፓርቲ ማዕከላዊ ኮሚቴ የትግራይ ጽቤት ኃላፊ

አስቴር ኤልያስ

**«ጦርነት ባህላዊ ጨዋታዬ ነው» ያለው አሸባሪው ትህነግ አሁን ጭንቅ ጥብብ እያለው ይገኛል። በየትኛውም መመዘኛ ጦርነት ባህላዊም ዘመናዊም ጨዋታ ሊሆን አይችልም፤ ጦርነት እሳት ነው፤ እሳት ደግሞ ለሚፈለገው ዓላማ በጥበብ ጥቅም ላይ እንዲውል እስካልተደረገ ድረስ እርጥብ ከደረቅ ሳይል በአንድ ላይ የሚበላ ነው። ቡድኑ እርሱ በለኮሰው እሳት በተለይ የትግራይን ሕዝብ ለወላፈኑ እየዳረገው ይገኛል። ለተደጋጋሚ ጊዜ ለሰላም በሩን እንዲከፍት ቢጠየቅም ሰላም ፈላጊ መስሎ ይቀርብና መልሶ ሲያፈርሰው ይስተዋላል። የይስሙላ ሰላም ፈላጊ መሆኑን በተደጋጋሚ ጊዜ አረጋግጧል። መንግስት ግን ዛሬም ቢሆን ለሰላም ያለውን ቁርጠኝነት በአደባባይ እየገለጸ ይገኛል። ከትህነግ ባህሪና ሰላም ገፊነቱ ጋር በተያያዘ በአሸባሪው ትህነግ በርካታ ስቃይ ከደረሰባቸው፤ የለውጡ መንግስት ወደ ስልጣን ከመጣ በኋላ በአሸባሪው ቡድን ወደ 35 ጊዜ ለእስር ከተዳረጉት የትግራይ ዴሞክራሲያዊ ፓርቲ (ትዴፓ) ማዕከላዊ ኮሚቴ የትግራይ ፅህፈት ቤት ኃላፊ እንዲሁም በጊዜያዊ አስተዳደር የክልሉ የቤቶች ልማት ኤጀንሲ ምክትል ዳይሬክተር ከሆኑት ከአቶ ኃይለማርያም ሕሉፍ ጋር ያደረግነውን ቆይታ እንደሚከተለው አጠናቅረን አቅርበነዋል።**



**አዲስ ዘመን:- ትህነግ እስከዛሬ የመጣባቸው መንገዶች ሰላም አስመፈለጉን የሚያሳይ ነው፤ ከዚህ አኳያ ባሕሪውን እንዴት ይገለጻል ?**

**አቶ ኃይለማርያም:-** ትህነግ የሰውም የፓርቲም ባህሪ የለውም። ለምሳሌ በትግራይ ክልል ከሚንቀሳቀሱ ተፎካካሪ ፓርቲዎች ውስጥ አረና፣ ትዴፓ ተጠቃሾች ናቸው። ትህነግ በስልጣን እያለ ለፓርቲዎች የሰጠው እውቅና ነው። ነገር ግን የሚከራከረው እንዳይኖር የሚፈለግ ድርጅት ነው። ተፎካካሪ ፓርቲ እንዳይኖር የሚፈልግ ከነበረ በመጀመሪያ እውቅና መስጠት አልነበረበትም፤ ከሰጠው በኋላ ግን ለምንድን ነው የምትሞግተኝና የምትከራከረኝ በሚል ሰላምን የሚነሳ ነው። ገና ለገና በወቅቱ የነበረውን ስልጣን ላለመልቀቅ ይሽማቀቅ የነበረ ድርጅት ነው። ይህ አምባገነንነቱ ዛሬ ላይ ብቻ ሳይሆን አሸባሪ ሊያሰኘው የሚችለው ያኔም ነበር። አሁን አሸባሪነቱ በውጭ አገር ጭምር ለምሳሌ በካናዳም እየተነገረ ይገኛል። የሚያደርጋቸው ነገሮች ሁሉ ለራሱና የራሱን ጥቅም ሊያስከብሩለት የሚችሉትን ጉዳዮች ነው።

አሸባሪው ትህነግ በምንም አይነት ሁኔታ የትግራይን ሕዝብ ሊወክል የሚችል ድርጅት አይደለም። ምክንያት ያልሽኝ እንደሆነ በየትኛውም መስፈርት የትግራይን ህዝብ ስነ ልቦና የሚመጥን ተግባር የለውም። ለምሳሌ አሸባሪው ድርጅት አንዴ የካህናትን ልብስ ተክህኖ በመልበስ ቄስ ለመምሰል ሲጥር እና ሲያታልል ይታያል፤ ሌላ ጊዜ ደግሞ ሌላ አይነት ገጸ ባህሪ ይላበስና ሊያስት ይሞክራል። ይህ ባህሪው በዓለም ደረጃ ራሱ ተወዳዳሪ የሌለው የውሸት ባለቤት ሊያደርገው ይችላል፤ እንዲህ አይነቱ ስነ ምግባር የጎደለው አሰራር በትግራይ ሕዝብ ስነ ልቦና ውስጥ የሌለ ነው።

ሌላው የአሸባሪው ትህነግ በፈጣሪም በሰይጣንም አለማመኑ ባሕሪውን ለየት ያደርገዋል። ከሃዲዎች ናቸው። ለምሳሌ የአንድ የቡድኑ አባል እግዚአብሔር አለ ወይ? ብለሽ ብትጠይቂው የለም ይልሻል። ሰይጣንስ አለ ወይ? ብለሽ ብትጠይቂው የለም ይልሻል። ለዚህም ነው የአሸባሪው ትህነግ ባሕሪ በዓለም ደረጃ እንኳ የተለየ ነው ያልኩሽ። እነርሱ ራሳቸውን በገዥው ስፍራ አስቀምጠው ያንኑ ሕልማቸውን እውን ለማድረግና ለማስቀጠል ይፈልጋሉ።

አሸባሪው ትህነግ በጥቅሉ እኛ ከሌለን እናንተ አትኖሩም ብሎ የሚሰራ ድርጅት ነው። በመሆኑም በአሁኑ ወቅት የትግራይን ሕዝብ በማስፈጀት ላይ ናቸው። ከዚህ በፊት በርካታ ወጣት አስጨርሰዋል፤ አሁን በተደረገው ውጊያ ደግሞ ከሶስት እስከ አምስት መቶ የሚደርስ ወጣት ማለቁን ያለኝ መረጃ ያመለክታል። ትህነግ በዓለም አቀፍ ደረጃ ካሉ ሁሉ ይለያል የምለው ለዚህ ነው።

**አዲስ ዘመን:- አሸባሪው ትህነግ ከመንግስት በኩል ለሰላም ተደጋግመው የሚዘረጉ እጆችን ባለመቀበል እልቂትን መፈለጉ ኢትዮጵያ እንድትበታተን ያለውን ምኞት ያሳያልና እዚህ ላይ ያልዎት አስተያየት ምንድን ነው?**

**አቶ ኃይለማርያም:-** አሸባሪው ወያኔ የምዕራባውያን ወኪል ነው። ለዚህ በርካታ ማሳያን መጥቀስ ይቻላል፤ ለምሳሌ የኢትዮጵያን ተረጋግቶ መልማትን እንደማይፈልጉ ሁሉ አሸባሪው ትህነግም የእነርሱ ወኪል እንደመሆኑ ሕልሙ እሱ ነው። በመሰረቱ የትግራይ ሕዝብ ለኢትዮጵያ አገሩ በርካታ ዋጋ የከፈለ ነው። ለአገሩ ሲል ደሙን አፍስሷል፤ አጥንቱንም ከስክሷል። ይህን እውነታ በርካቶች ያውቁታል። የትግራይ ሕዝብ ብቻ ሳይሆን ኦሮሞም አማራም ሆነ ሌላው ኢትዮጵያዊ ሁሉ ከፍተኛ መስዋዕትነት ለአገሩ ከፍሏል። አሸባሪው ትህነግ ልክ ሁሉን ነገር የሰራ አድርጎና ዋጋ እንደከፈለ መሆኑ የሚያስኬደው አይደለም፤ ቡድኑ ሩጫው ሁሉ በትውልድ ደም ተረማምዶ ስልጣን መያዝ ነው። የትኛውም ሰው ይለቅ ማንም ምን ይበል እሱ ደህና ከሆነ የሌላው ደህንነት የሚያሳስበው አለመሆኑ ነው። ጦርነት ልማት እንደሚጎዳ ቢያውቅም እሱ ግን ከኢትዮጵያ የዘረፈውን በርካታ ሀብት ወደውጭ አገር በማሸሹ የሚደርስበት ጉዳት እንደማይኖር ያስባል። ቡድኑ ይህን ሀብት ያስቀመጠው ደግሞ በአፍሪካም በአውሮፓም ጭምር ነው። ይህ አሸባሪ የሚያስበው ስለራሱ ደህንነት ብቻ በመሆኑ የትግራይ ወኪል ሊሆን በፍጹም የማይችል ድርጅት ነው።

አሸባሪው ሕወሓት ሲለው ኮሚኒስት፣ ሲሻው ደግሞ ሊበራል ይሆናል። ነገ ደግሞ ሶሻል ነኝ ሲል ይደመጣል። በሌላ ጊዜ ደግሞ አብዮታዊ ዴሞክራሲ ነኝ ሲል ይሰማል። አብዮትና ዴሞክራሲ አብረው የሚሄዱ አይደለም። ይህን ሁሉ ማድረጉ ለማወዛገብ ነው። ሁለንተናው ሴራ የተሞላበት ነው። ውስጣቸው የምዕራባውያን ወኪል ነው። ስለዚህም ለሰላም የሚዘረጉ እጆችን የመቀበል ሞራል የላቸውም።

ቡድኑ በመሰረቱ የትግራይ ሕዝብ ወኪል ሆኖ አያውቅም። የትግራይ ሕዝብ ንጹህ የመጠጥ ውሃ ሳይኖረው እርሱ ግን ሲንደላቀቅ ይታያል። እነርሱ ለትግራይ ሕዝብ ማንነትም ባህልም ደንታ የሌላቸው ናቸው፤ ከሰሞኑ በአክሱም አካባቢ ምሽግ እየሰሩ እንደሆነ ይነገራል። ይህ ደግሞ ለቅርስም ያላቸው አመለካከት የወረደ መሆኑን አመላካች ነው። የትኛውም አይነት ቅርስ ይጥፋ አይጥፋ ለእነርሱ ምናቸውም እንዳልሆነ በአክሱም ሐውልት አካባቢ እየተቆፈረ ነው የተባለው ምሽግ አመላካች ነው። ይህ ዓላማቸው የሚያሳየው ቅርሱ እንዲመታ ከመፈለግ ነው። ከዚህም አልፈው ራሳቸው ቅርሱን ሊመቱ የሚችሉ ግፈኞች መሆናቸው ሊዘነጋ አይገባም።

**አዲስ ዘመን:- አሸባሪው ሕወሓት በሚሰራው የግፍ ስራ የሚያመሰግነው አካል ወይም ለእኔ ነው የሚለው አካል ያለ ይመስልዎታል?**

**አቶ ኃይለማርያም:-** አንድ ነገር ልግልጽልሽ፤ በተንቤን ውስጥ አንድ መልዕክት አዘል ዘፈን ተዘፍኗል፤ ከዘፈኑ ውስጥ ካሉ ስንኞች አንዱ፤ ‹የዐቢይ አሕመድ እርዳታ በሳምንት በሳምንት፤ የዶክተር ደብረጽዮን እርዳታ ደግሞ በስድስት ወር አንዴ› የሚል ነው። ስለዚህ ትህነግ ለሕዝብ የማያስብ ድርጅት መሆኑን ሕዝቡ በአግባቡ ተረድቷል። ምክንያቱም ሁለንተናዊ እንቅስቃሴው ለራሱና ለራሱ ብቻ ትኩረት ያደረገ ነው። ይህን አካሄዱን የሚቃወም ካለ ደግሞ ይመታል። ከዚህ በተጨማሪ መሪዎቹ የአንድ ቤተሰብ አባላት ስለመሆናቸው ሕዝቡ ያውቃቸዋል። የድሃው ልጅ እንጂ የእነርሱ ልጆች በአካባቢው የሉም። ገሚሱ አዲስ አበባ ሌላው በውጭ አገር ናቸው። በሕዝቡ ውስጥ ግን አባትም እናትም የሌለው ህጻን አለ። ከዚህ የተነሳ ቡድኑ የሚንቀሳቀስልኝ ለእኔ ነው የሚል የለም።

ስለሆነም በአሁኑ ወቅት የትግራይን ሕዝብ የሚያድነው ያስፈልገዋል። ምክንያቱም ሕዝቡ አሸባሪው ትህነግ እንደማይሆነው ተስፋ ከቆረጠ ቆይቷል። ሌላው ቀርቶ ከቀናት በፊት እንኳን በተንቤን ውስጥ ልጆቻችን የት አሉ? የሚል የእናቶች ሪቮሊሽን ተነስቷል። ‹ልጆቼን› የሚሉ እናቶች በየቦታው እያለቀሱ ነው። ከከተማ አምልጦ የሚሄድን ሁሉ ቡድኑ በጥይት እየመታቸው ይገኛል። አርሚ 31 በሚባለው ቡድን ነው የሚመታው፤ ይህ አርሚ 31 የሚባለው ቡድን የእነርሱ የቅርብ ቤተሰብ የሆነ ነው። የሚመራውም በወዲ ወረደ ነው።

በጥቅሉ የትግራይ ሕዝብ አማራጭ ያስፈልገዋል። በአሁኑ ወቅት ሕዝቡ ተርቧል። አሸባሪው ቡድን ደግሞ ለተራበው ሕዝብ አንዳች አያዝንለትም። ሕዝቡ በሆነ አማራጭ የምግብ አቅርቦት ቢደርስለት መልካም ነው። የትግራይ ሕዝብ ከደረሰበት መከራ የተነሳ አሸባሪውን በቃኝ ያለው ዛሬ አይደለም፤ የዛሬ ሰባት ዓመት አካባቢ ነው። ምክንያቱም ሕዝቡ ሴራቸውን አሳምሮ ያውቀዋል። ዋጋም እንደሌለው መቶ በመቶ አምኗል።

**አዲስ ዘመን:- መንግስት ለድርድር ሁኔታዎች እንዲመቻቹ እየጣረ ባለበት በዚህ ጊዜ አሸባሪው ትህነግ የክተት ጥሪ ማወጁ እየቀለደ ያለው እመራቸዋለሁ በሚለው ሕዝቡ ላይ እንደሆነ ይነገራል፤ እዚህ ላይ ምን ይላሉ?**

**አቶ ኃይለማርያም:-** ከአሁን በፊትም የክተት ጥሪን በተመለከተ ጌታቸው ረዳ አድርጓል። እኛ ወደ አዲስ አበባ ስንመጣ ምን ልትሰሩ መጣችሁ ያሉን የትግራይ ብልጽግና አባላት አሉ። የሰላም ሚኒስቴር አይዟችሁ ብሎ ሲያበረታታን በተለይ በወቅቱ የሰላም ሚኒስትር የነበሩት ወይዘሮ ሙፈሪያትን በዚህ አጋጣሚ ላመሰግናቸው እወዳለሁ። ሌሎቹ የትግራይ ብልጽግና ውስጥ ካሉት መካከል ምን ልትሰሩ መጣችሁ ብለውናል። እነዚህን አካላት እኛ የአሸባሪው ትህነግ አስተሳሰብ አራማጆች ናቸው አስብሎናል።

ስለዚህም የትግራይ ሕዝብ ቆራጥ አመራር

**ከአሁን በፊትም የክተት ጥሪን በተመለከተ ጌታቸው ረዳ አድርጓል። እኛ ወደ አዲስ አበባ ስንመጣ ምን ልትሰሩ መጣችሁ ያሉን የትግራይ ብልጽግና አባላት አሉ። የሰላም ሚኒስቴር አይዟችሁ ብሎ ሲያበረታታን በተለይ በወቅቱ የሰላም ሚኒስትር የነበሩት ወይዘሮ ሙፈሪያትን በዚህ አጋጣሚ ላመሰግናቸው እወዳለሁ።**

ፖለቲካና ወቅታዊ

# ወቅታዊ



ያስፈልገዋል። አብዮታዊ ዴሞክራሲ የሚለውን ጽንሰ ሐሳብ ከትግራይ ላይ የሚነጥል ፖለቲከኛ ያስፈልጋል ብዬ አምናለሁ። ቡድኑ ሁሉን ነገር በሰይፍ የሚል አስተሳሰብ ያለው ነው። ሕዝቡ በአሁኑ ወቅት አማራጭ አጥቷል፤ በምሬት የሆነ ነገር ሲናገር ቡድኑ ማታ ማታ አንቆ ይወስደዋል። የትግራይ ሕዝብ በኢትዮጵያዊነቱ የሚደራደር አይደለም። ሁሌም የሚለው ‹ኢትዮጵያውያን ነን፤ ነገም ዛሬም ቢሆን ኢትዮጵያውያን ነን› ነው። ይህን በማለታቸው በምሽት ውድቅት ላይ ትህነግ እንደሚበቀላቸው እያወቁ ነው። ይህን በማለታቸው ብቻ እስከ ሃያ ዓመት እየተፈረደበት የሚገኝ አለ።

አሸባሪው ትህነግ ወደስልጣን በምርጫ ወይም በፍቅር የመጣ ድርጅት አልነበረም። ወደኋላ ዞር ብለሽ ስራውን ስታዪ ሰውን አስፈጅቶ የመጣ ድርጅት ነው። የትግራይ ሕዝብ አንድ የሚለው ነገር አለው፤ ቡድኑ ገና ሲመጣም ሆኖ ከስልጣን ሲወርድ ሰውን አስፈጅቶ ነው የሚል ትንቢት ነበረው፤ አሁን እየታየ ያለ ጉዳይ ነው። ሕዝቡ ዘንድ ፍቅር እንደሌለ ያውቀዋል። ስለዚህ ትህነግ እንዲህ አይነት ስነ ልቦና ያለው እንደመሆኑ ለሕዝቡ ለደህንነቱና ለሰላሙ መፍትሔ ማምጣት ያስፈልጋል።

አሸባሪው ትህነግ ባለፉት 50 ዓመታት የመሰረተው ፖለቲካ ሁሉ የሴራ ፖለቲካ ነው። ስለዚህም ይህን የሴራ ፖለቲካ ለአንዴና ለመጨረሻ ድባቅ የሚመታ አመራር ያስፈልጋል። ይህ ካልሆነ ግን የትግራይን ሕዝብ ያላከተተ ለውጥ ይሆናልና እዚህ ላይም ቢታሰብበት መልካም ነው።

**አዲስ ዘመን፦ አሸባሪው ቡድን የአፍሪካን ችግር በአፍሪካውያን መፈታት አለበት የሚለውን ብሒል ወደጎን ያደረገ ይመስላልና በዚህ ላይ ምን አስተያየት አልዎት?**

**አቶ ኃይለማርያም፦** ይህ መርህ እሱ ራሱ ስልጣን ላይ ባለበት ጊዜ የወጣ ነው። ቀደም ሲል እነርሱ በስልጣን ላይ እያሉ እኔ ደግሞ በክልል ተቃዋሚ ነበርኩ። እኔ ያለሁበት የሕዝብ አገልግሎት መስጫ ቦታ ድረስ ካድሬዎቹ እየመጡ ችግር ሲያደርሱብኝ ነበር። ምንም እንኳ በተቃዋሚ ፓርቲ ጎራ ብንሆንም በሌላ በኩል ደግሞ የመንግስት ሰራተኛ ነበርንና በአንዳንድ ስብሰባዎች ላይ በመሳተፍ ሐሳብ አስተያየት በምንሰነዝርበት ጊዜ ብዙ መከራ ይደርስብን ነበር።

የአፍሪካ ችግር በአፍሪካውያን መዳኘት አለበት በሚል እነርሱ ራሳቸው የቀድሞው የሱዳኑ ፕሬዚዳንት አልበሽር ክሳቸው በዓለምአቀፉ ፍርድ ቤት ከሚሆን በአፍሪካ ውስጥ ቢሆን በሚል ለተነሳ ሐሳብ እነርሱም ነበሩበት። በአሁኑ ሰዓት ግን ይህ አይነቱ ሐሳብ ወደእነርሱ ሲመጣ አንዳኝም ማለት ከእኔ ወዲያ ላሳር የሚለውን ባህሪያቸውን የሚገልጽ ነው። ራሱ ባወጣሁት ሕግ አልገዛም እንደማለት ነው። ከእኔ በስተቀር የሚለው አስተሳሰባቸው የእነርሱ የውስጥ ሕጋቸው ነው። እንደልባቸው የሚሆኑት እነዚህ አካላት ደግሞ የሰባት ቤተሰብ አባላት ናቸው። በአሁኑ ወቅትም ራሳቸውን እንደመንግስት ቆጥረው የትግራይን ሕዝብ ካልመራሁት እያሉ ያሉት እነዚህ ሰባት ያህል ቤተሰብ ነን ባዮች ናቸው። እነዚህ አካላት ከጌታቸው ረዳ የሚኮናተሩት አፉን ነው። በአሁኑ ወቅት የትግራይን ሕዝብ እየለፈለፈ ያስጨረሰ ጌታቸው ረዳ ነው። በአሁኑ ወቅት ጌታቸው ረዳ ያኮናተረውን የአፉን ተግባር ወደማጠናቀቁ የገባ ይመስላል።

**አዲስ ዘመን፦ መንግስት ዛሬም ስለሰላም ይዘምራል፤ አሸባሪው ትህነግ ደግሞ ስለጦርነት ያንጎራጉራል። ለህዝቡ ሰላምን ለማስፈን መፍትሔው ምንድን ነው ይላሉ?**

**አቶ ኃይለማርያም፦** በመጀመሪያ ደረጃ የትግራይ ሕዝብ በማንም ጨቋኝ መተዳደር የለበትም። አሸባሪው ትህነግ የትግራይን ሕዝብ ባህል፣ ኃይማኖቱንና ስነ ልቦናውን በርዟል። አደረጃጀቱ በኦርቶዶክስ፣ በፕሮቴስታንት እንዲሁም በእስልምናው የእምነት ተቋማት ውስጥ አለ። በእነዚህ ተቋማት ውስጥ ፖለቲካ መግባት እንደሌለበት በሕጉ የተቀመጠ ቢሆንም ይህ ቡድን ግን ይህን ሲያደርግ ቆይቷል። አንድ ሰው ኃይማኖተኛ ነኝ ብሎ ካለ መሆን ያለበት ኃይማኖተኛ ነው እንጂ በቤተ እምነት ውስጥ ፖለቲካ ማራመድ አይኖርበትም።

እነርሱ ሰላም ፈላጊ ቢሆኑ ኖሮ ልማቱንም ጎን ለጎን ይሰሩ ነበር። በትግራይ ያለው ሪፈራል ሆስፒታል አይደር ብቻ ነው። በዛ ልክ አንድ ሆስፒታል መያዝ የሚገባውን የያዘ ሆስፒታል የለም። ታሽጎ የሚሸጥ መድኃኒት ነው ሲሸጥ የሚታየው። ስለዚህ ይህ ቡድን ስለሰላም ለልማትም አይኑን አልገለጥ ብሏል። በመሆኑም በመንግስት በኩል መደረግ ያለበት ብዬ የማስበው የትግራይን ሕዝብ በቡድኑ እጅ ላለመተው አማራጭ ሊሰጠው ይገባል።

መንግስት በሚመቸው መንገድ ለሕዝቡ እርዳታ መስጠት አለበት ባይ ነኝ። ከዚህ ጎን ለጎን መንግስት ለትግራይ ሕዝብ ለውጥ መስራት የሚችሉ አካላትን ከጎኑ ማሰለፍ መቻል አለበት። ዋናው ነገር በፖለቲካው ላይ መንግስት ጠንክሮ መስራት ይጠበቅበታል፤ ሌላው ቀርቶ አሸባሪው ቡድን በውጊያ ቢያሸንፍ እንኳ በፖለቲካው ከተሸነፈ ዜሮ ነው ማለት ነውና መንግስት ለሰላም ሲል በፖለቲካው ላይ ጠንክሮ መስራትና ማሸነፍ አለበት።

ስለትግራይ የሚያስቡ የትግራይ ተወላጆች ደግሞ በአደባባይ ወጥተው ስለሕዝቡ መናገር አለባቸው። በእርግጥ የተጀመረ ነገር አለ። ይህ መልካም ጅማሮ ነው። የአሸባሪው ትህነግ ታሪኩ አብቅቷል ማለት ይቻላል። በአፍሪካ፣ በምስራቅ አፍሪካ፣ ብሎም በኢትዮጵያ ከዚያም ወርዶ በመቀሌ ከዚያም አልፎ ቆላ ተንቤን ገብቷል፤ እናም በዓለም ላይ ወድቆ ተመልሶ የገዛ መንግስት የለም። ደርግም ወድቆ ነበር፤ አልተመለሰም፤ ነገ ደግሞ ሌላ ተረኛ ሊውድቅ ይችላል፤ ግን አይመለስም። ምክንያቱም ላለመመለሱ የሰላም ጠንቅ በመሆኑ አሊያ በሌላ ችግሩ ሊሆን ይችላልና ሕዝብ ያንን መልሶ መንግስት ሊያደርገው አይችልም።

አሁንም ይህ ቡድን ምንም እንኳን መመለስ ባይችልም አስተዳድረዋለሁ እያለ ያለው ሕዝብ ግን እያለቀ ስለሆነ አማራጭ በመንግስት በኩል ሊቀርብለት ይገባል። ከክልሉ አማራጭ አጥቶ ሰላምን ፍለጋ ሲሰደድ ድጋፍ ማድረግ ያስፈልጋል። በዚህ መሃል ደግሞ አስቸጋሪ በሆኑ ሰዎች ላይ እርምጃ መውሰድ መቻል አለበት። ወደሕግ ማቅረቡ የግድ ይላል።

ለሰላም መረጋገጥ ሌላው መፈተሽ ያለበት መንግስት ወደራሱ ያቀረባቸውን ሰዎች ጭምር ነው። ጨው ለራሱ ሲል ካልጣፈጠ ድንጋይ ነህ ተብሎ ሊወረወር እንደሚችል መታወቅ አለበት። የትግራይ ብልጽግናም ራሱን በአግባቡ መፈተሽ አለበት። ማን ትክክል፤ ማን ደግሞ ስህተት ፈጻሚ ተብሎ መለየት መቻል አለበት። መንግስት ስህተት እንደሌለበት አሳምረን እናውቃለን፤ በትግራይ ብልጽግና አካባቢ ግን አንዳንድ ሁኔታ ቢፈተሽና ቢታይ ለሰላሙ የበለጠ ጉልበት ይኖረዋል ብዬ አስባለሁ።

ሌላው ደግሞ የትግራይ ሕዝብ ባለቤት ያስፈልገዋል። በተለይ የሚቆረቆርለት ባለቤት በፓርላማው ውስጥም ያስፈልገዋል። የትግራይ ሕዝብ ወኪልን መንግስት

**እንደስታሊን ገብረስላሴ የመሳሰሉ የትግራይን ሕዝብ ባህል የሚያጠለሹ አይነቶችን መቃወም ይኖርባቸዋል። ስታሊን በንግግሩም የትግራይ እናቶችን የሚያንቋሽሽ መልዕክት አስተላልፏል። ይህንን ሰው የትግራይ ዳያስፖራ ብቻ ሳይሆን መንግስትም ሊጠይቀው ይገባል ባይ ነኝ። እንደፓርቲዬም ይህ ሰው መከሰስ ይጠበቅብናል እላለሁ።**

እውቅና ሊሰጣቸው ይገባል። በፓርላማ ውስጥ አቤቱታ የሚያቀርብለት አካል ያሻዋል። ሕዝቡ እንደዜጋ ታይቶ ብዙ መከራ እንደከፈለ ኢትዮጵያዊ ታይቶ ይህ ሊደረግለት ይገባል። የተወሰኑ አሸባሪ ቡድኖች ሰሜን እዝን ላይ ባደረሱት ጥቃት የትግራይን ሕዝብ ከዚህ ግፈኛ ቡድን ጋር እኩል ማየቱ ከበድ የሚል ነው። በለውጡ መንግስት የተፈጠሩ ልጆች ዳቦና ውሃ ሊከለከሉ አይገባም።

የቡድኑ አባላት ማዕድን ያለበትን ስፍራ በገመድ እየመተሩ ሲከፋፈሉ አይተናል። ሕዝቡ በወቅቱ ግራ ገብቶት ነበር። የለውጡ መንግስት በመምጣቱ እንደማንኛውም ኢትዮጵያዊ የትግራይ ሕዝብ ተደስቷል። ነገር ግን አሸባሪው ትህነግ የፖለቲካውን ሁኔታ ወደ ራሱ ገለበጠው። ሕልሙ ሕዝቡን አደንቁሮ መግዛት ነው። ከእሱ ቤተሰብ ውጪ ማንም እንዲገባ አይፈልግም፤ መማርም ሆነ ሀብታም መሆንም የሚፈቀድለት የቡድኑ ቤተሰብ የሆነ አካል ነው። ለምሳሌ ሰሞኑን የተሰጠውን የሁለተኛ ደረጃ መልቀቂያ ፈተና የትግራይ ሕዝብ የሚፈልገው አይነት አሰራር ነው፤ ምክንያቱም የትግራይ ሕዝብ ልጁ በትክክለኛው መንገድ ተፈትኖ የተሻለ ቦታ እንዲደርስለት ምኞቱ ነው።

የአሸባሪው ትህነግ ካድሬ ከዚህ በኋላ በሕዝቡ ኑሮ ሊቀልዱ አይገባም፤ ሕዝቡንም ማስጨረስ የለባቸው፤ በሕዝቡ ዘንድ በከፍተኛ ሁኔታ ተጠልተዋል። ዛሬ ለ12 ኪሎ እህል የትግራይ ሕዝብ ተሰልፎ ወረፋውን በመጠባበቅ ላይ ነው።

በአዲስ አበባ ያሉ ለውጥ ፈላጊዎችን መንግስት ማደራጀት አለበት፤ ይህ አሁን ተጀምሯል። ለሁሉም ጥሪ አድርጎ ማደራጀቱን ማጠናከር አለበት። አሜሪካ የትግራይን ሕዝብ እያስፈጀችው ነውና ተይ ልትባልም ይገባል።

**አዲስ ዘመን፦ ዲያስፖራዎች እና የፖለቲካ ፓርቲዎች በዚህ ጉዳይ ድርሻቸው ምን መሆን አለበት ይላሉ?**

**አቶ ኃይለማርያም፦** በውጭ አገር ያሉ የትግራይ ተወላጆች በመጀመሪያ የዲፕሎማሲ ስራውን ከእነርሱ ጋር መስራት ተገቢ ነው እላለሁ። ምክንያቱም አሸባሪው ትህነግ ውድቅ መሆኑን እያዩት ነው። እስከ ሶስተኛው ድረስ ጦርነት አውጆ ሕዝቡን ሲያስጨርስ የነበረው በአሁኑ ሰዓት አክትሞለታል። በቅርቡ እንኳ ከቆቦ ሲወጣ አብቅቶለት ነው። በተለያየ አገር ውስጥ የሚገኙ የቡድኑ አክቲቪስቶች በሚጽፉት ፕሮፓጋንዳ ሰው መሸውድ የለበትም። ይህ አካሄዳቸው ግን የሚያዋጣቸው አይደለም።

ከዚህ በተጨማሪ እንደስታሊን ገብረስላሴ የመሳሰሉ የትግራይን ሕዝብ ባህል የሚያጠለሹ አይነቶችን መቃወም ይኖርባቸዋል። ስታሊን በንግግሩም የትግራይ እናቶችን የሚያንቋሽሽ መልዕክት አስተላልፏል። ይህንን ሰው የትግራይ ዳያስፖራ ብቻ ሳይሆን መንግስትም ሊጠይቀው ይገባል ባይ ነኝ። እንደፓርቲዬም ይህ ሰው መከሰስ ይጠበቅብናል እላለሁ። በተለይ ደግሞ በአገር ውስጥ በየትኛውም ክልል ያሉ ሴቶች ይህን ሰውዬ በሕግ መጠየቅ አለባችሁ። ከሚኖርበትም አካባቢ ተጎትቶ መጥቶ በኢትዮጵያ ሕግ እንዲዳኝ ዳያስፖራው ጩኸቱን ማሰማት አለበት። በጥቅሉ በውጭ አገር ያሉ ሰውዬውን ወደሕግ እንዲቀርብ የበኩላቸውን ሊወጡ ይገባል። ይህ ሰው ያዋረደው ትግራይን ብሎም ኢትዮጵያንም ጭምር ነው።

ጦርነት ባህላዊ ጨዋታ ነው ካሉት ግድየለሾች ጀምሮ ሁሉም ተጠያቂ ሊሆኑ ይገባል። በየትኛውም አገር ጦርነት አጥፊ፣ አወዳሚ፣ አፍራሽ እንጂ ከባህላዊ ጨዋታዎች እንደ አንዱ ሊታይ አይገባም። እኛ የትግራይ ተወላጆች ውጊያ አያስፈልገንም። በውጊያ የሚያድግም ያደገም አገር የለም። የቡድኑ አባላት በየበለጸገው አገር ተቀምጦ ዲያመንድ ሲያማርጥ የትግራይ ሕዝብ እናት የሆነች ግን የሚቆረስ ዳቦ አጥታ በረሃብ ትማቅቃለች።

**አዲስ ዘመን፦ በጦርነቱ እየተሳተፉ ላሉ ወጣቶች እና ለትግራይ ሕዝብ ምን መልዕክት ማስተላለፍ ይሻሉ?**

**አቶ ኃይለማርያም፦** የትግራይ ወጣትም ሆነ ሕዝብ ለአንድ ቤተሰብ የስልጣን ጥማት ሲል መሞት የለበትም። ቡድን የትግራይ ሕዝብ ወኪል ሳይሆን የምዕራባውያኑ ወኪል ነው። ኢትዮጵያ ማለት ታላቅ አገር እንደሆነች የተቀረው ዓለም ጠንቅቆ ያውቀዋል፤ ስለዚህ ይህን ሕዝብ መቼም ቢሆን ከፋፍሎ መግዛት አይቻልም። ይህ ሕልም መቼም ቢሆን እውን እንደማይሆን እነዚህ አካላት ሊገነዘቡት ይገባል። ደግሞም የውጭ አካላት ኢትዮጵያውያን በምንም መንገድ እንደማይከፋፈሉ በተለያየ መንገድ አይተዋል። ስለሆነም ለሰላም እየተንቀሳቀሰ ያለውን የኢትዮጵያን መንግስት መደገፍ ይጠበቅባቸዋል። ሲያጫርሱ የነበሩት የአንድ ቤተሰብ አባላት የሆኑት አሸባሪዎች ግን ተገቢውን ቅጣት ማግኘት አለባቸው። ወደውጭ ለመውጣት ይጣጣሩ ይሆናልና ይህ እንዳይሳካላቸው ማድረግ ነው።

እኔ በአዲስ አበባ ያየሁት መንግስት አወቃቀሩን የፈጠረ ቢሆንም ታች ላለው የለውጥ ኃይል የሚደርሰው ነገር የለም። በጊዜያዊ መንግስት የበኩላቸውን ነገር ላደረጉ እውቅና መስጠት አለበት። ከመከላከያ ጎን ከመቆም ጀምሮ ለለውጡ የታገሉትን እውቅና መስጠት ያስፈልጋል። እየተሰሩ ያሉትንም ሊሰማቸው ይገባል።

**አዲስ ዘመን፦ ስለሰጡን ማብራሪያ አመሰግናለሁ?**

**አቶ ኃይለማርያም፦** እኔም አመሰግናለሁ።

ኢኮኖሚ

# ኢንቨስትመንት

## የሕክምና ዘርፍ ምርቶችን በአገር ውስጥ የማምረት ጥረት

አንተነህ ቸሬ

መንግሥት መዋቅራዊ የምጣኔ ሀብት ሽግግርን እውን ለማድረግ አስተዋፅኦ ይኖራቸዋል ብሎ ትኩረት ከሰጣቸው ተግባራት መካከል የኢንዱስትሪ ፓርኮች ልማት አንዱ ነው። በእርግጥም ፓርኮቹ በሚገነቡባቸው አካባቢዎች ለሚኖረው የኅብረተሰብ ክፍል የስራ እድል በመፍጠርና ከአካባቢ ጋር ተስማሚ የሆነ የሥራ ከባቢ እውን በማድረግ ለአገራዊ የምጣኔ ሀብት እድገት ትልቅ አስተዋፅኦ ይኖራቸዋል።

የኢንዱስትሪ ፓርኮችን ተመራጭ ከሚያደርጓቸው ነገሮች መካከል በርካታ አገልግሎቶችን አንድ ሥፍራ ላይ ሰብሰብ አድርገው የሚያቀርቡ መሆናቸው፣ ተገቢ መሰረተ ልማት የሚገነባላቸው እንዲሁም ከሌሎች አምራቾች ጋርም ትስስር የሚፈጠርባቸው መሆናቸው ይጠቀሳሉ። ከዚህ አንፃር በኢትዮጵያም ብዙ የኢንዱስትሪ ፓርኮችን በማቋቋም እንዲሁም ሰፊ የሰው ኃይል ያለ መሆኑና በቂ የኤሌክትሪክ ኃይል አቅርቦት መኖሩ፣ ማሽኖችን ከቀረጥ ነፃ ማስገባትን፣ የብድር አቅርቦትን፣ የአንድ ማዕከል አገልግሎትን እና የመሰረተ ልማት ግንባታዎችን እንደማበረታቻ በማቅረብ ትልልቅ ዓለም አቀፍ ኩባንያዎች ፋብሪካዎቻቸውን ኢትዮጵያ ውስጥ ተክለው እንዲሰሩ ጥረቶች ተደርገዋል።

የኢንዱስትሪ ፓርኮች ሦስት ዋና ዋና መሰረታዊ ተልዕኮዎች አሏቸው። እነዚህ ተልዕኮዎቻቸው የውጭ ቀጥታ ኢንቨስትመንት መሳብ፣ የሥራ እድል ፈጠራን ማስፋት እና የቴክኖሎጂ ሽግግርን ማከናወን ናቸው። በአሁኑ ወቅት በመላ አገሪቱ 13 የኢንዱስትሪ ፓርኮች የሚገኙ ሲሆን በስራ እድል ፈጠራ፣ በውጭ ቀጥታ ኢንቨስትመንትና በቴክኖሎጂ ሽግግር ለአገራዊ ምጣኔ ሀብት እድገት አስተዋፅኦ እያበረከቱ ይገኛሉ።

እስከ ሰኔ 30 ቀን 2014 ዓ.ም በተጠናቀረ የኢንዱስትሪ ፓርኮች ልማት ኮርፖሬሽን መረጃ መሰረት በኢንዱስትሪ ፓርኮች ውስጥ በቀጥታ በምርት ተግባራት ላይ 81ሺ ሰራተኞች ተሰማርተዋል። ይህ ቁጥር ከፓርኮቹ ውጭ ያሉና ተዘዋዋሪ በሆነ መንገድ የሥራ እድል የተፈጠረላቸውን ሰዎች አይጨምርም። በኢንዱስትሪ ፓርኮቹ ውስጥ የሚገኙ አምራቾች ከፓርኮቹ ውጭ ካሉ ግለሰቦችና ድርጅቶች ጋር የስራ ትስስር ስላላቸው በዚህ ሂደትም በርካታ የሥራ እድሎች ተፈጥረዋል። ከዚህ በተጨማሪም ፓርኮቹ ስራ ከጀመሩበት ጊዜ አንስቶ፣ እስከ ሰኔ 30 ቀን 2014 ዓ.ም ድረስ፣ ለውጭ ገበያ የቀረበውና በተኪ ምርቶች የተገኘው ገቢ አንድ ነጥብ አንድ ቢሊዮን ዶላር ሆኗል። ከዚህ ገቢ ውስጥ፣ 930 ሚሊዮን ዶላር የሚሆነው ገንዘብ ለውጭ ገበያ ከቀረቡ ምርቶች የተገኘ ነው።

በእርግጥም ኢትዮጵያ የአፍሪካ የማምረቻ መናኸሪያ እንድትሆን የሚደረገውን ጥረት ለማቀላጠፍ እንዲሁም የሥራ አጥነት ችግርን ለመቅረፍ ላቅ ያለ ሚና ይኖረዋል ተብሎ ተስፋ የተጣለበት የኢንዱስትሪ ፓርኮች ልማት ውጤቶች ተገኝተውበታል። በተለይም እንደ አገር የውጭ ምንዛሬ በእጅጉ በሚያስፈልግበት በእዚህ ወቅት እንደ አንድ የውጭ ምንዛሬ ምንጭ በመሆን እንዲሁም ለበርካታ ዜጎች የስራ እድሎችን በመፍጠር አስተዋፅኦ አበርክተዋል።

ከእነዚህ ፓርኮች መካከል አንዱ በአዲስ አበባ ከተማ የሚገኘው የቂሊንጦ ኢንዱስትሪ ፓርክ ነው። በ279 ሄክታር መሬት ላይ ያረፈው ፓርኩ፣ የፋርማሲዩቲካል ምርቶችን የሚያመርቱ ባለሀብቶች እንዲሰማሩበት የተገነባ ነው። በአሁኑ ወቅት 17 ባለሀብቶች ወደ ፓርኩ ገብተው በተለያዩ ደረጃዎች በኢንቨስትመንት ተግባራት ላይ ተሰማርተዋል። ወደ ፓርኩ የገቡት አምራቾች ኢትዮጵያን በየዓመቱ ለከፍተኛ የውጭ ምንዛሬ ወጪ ከሚዳርጓት ዘርፎች መካከል አንዱ የሆነውን የመድኃኒትና የሕክምና መገልገያዎች ግዢ ፍላጎት በአገር ውስጥ ለማምረት የሚደረገውን ጥረት እያገዙ ይገኛሉ።

የቂሊንጦ ኢንዱስትሪ ፓርክ ሥራ አስኪያጅ አቶ መንግሥቱ ረጋሳ፣ ፓርኩ ለአምራች ኩባንያዎች አስፈላጊ የሆኑ መሰረተ ልማቶችን አሟልቶ አምራቾችን እየተቀበለና ሌሎች አምራቾችንም እየተጠባበቀ እንደሚገኝ ይገልፃሉ። እርሳቸው እንደሚሉት፣ ወደ ፓርኩ የገቡት ባለሀብቶች በማምረት ላይ፣ በግንባታ ላይ እና በዲዛይን/ጥናት ላይ የሚገኙ ሲሆኑ፤ አብዛኞቹ አምራቾች የአገር ውስጥ ባለሀብቶች ናቸው። በቀጣይ ወራትም ወደ ምርት




ቂሊንጦ ኢንዱስትሪ ፓርክ

የሚገቡ አምራቾች አሉ። ካለፈው ሐምሌ ወር ጀምሮ ወደ ፓርኩ ገብተው ለመስራት ፍላጎት ያሳዩ ባለሀብቶች ቁጥር እየጨመረ መምጣቱን ጠቁመው፤ ሌሎች ባለሀብቶችም ወደ ፓርኩ ገብተው እንዲያለሙ ጥሪ አቅርበዋል።

የኢንዱስትሪ ፓርኮች ልማት ኮርፖሬሽን የማርኬቲንግና የሕዝብ ግንኙነት ዳይሬክተር አቶ ሄኖክ አስራት እንደሚሉት፣ ባለሀብቶቹ በዘርፉ ኢንቨስት ሲያደርጉ የታክስ ክፍያ የእፎይታ ጊዜ፣ ከውጭ ለሚያስገቧቸው ግብአቶች የቀረጥ ነፃ ድጋፍና ሌሎች ማበረታቻዎች ይደረጉላቸዋል። ወደ ፓርኮቹ ገብተው ለሚሰማሩ ባለሀብቶች፣ በተለይም ተኪ ምርቶችን በማምረት ላይ ላተኮሩ አምራቾች፣ የመሬትና የማምረቻ ሼድ ኪራይ ክፍያን በብር እንዲከፍሉ የሚያስችሉ ሁኔታዎች እየተመቻቹ ነው። ባለብቶቹ ወደ ፓርኩ ገብተው በፈለጉት ዲዛይን ገንብተው እየሰሩ እንደሚገኙና በግልም ሆነ በጋራ በመሆን የሚያለሙበት መንገድ እንደሚመቻችላቸው ገልፀዋል።

ባለሀብቶችን ወደ ኢንዱስትሪ ፓርኮች ለመሳብ በሚደረገው ጥረት ለዘላቂ የአገር ልማትና እድገት አስተማማኝ ዋስትና መሆን የሚችሉትን የአገር ውስጥ ባለሀብቶችን መደገፍ ትኩረት ሊሰጠው የሚገባ ዐቢይ ጉዳይ መሆኑ ይታወቃል። የአገር ውስጥ ባለሀብቶች ወደ ቂሊንጦ ኢንዱስትሪ ፓርክ እንዲገቡ በማድረግ ረገድ የሚከናወኑ ተግባራትን በተመለከተም «የአገር ውስጥ አቅም ለመፍጠር የሚያግዙ ሥራዎች እየተሰሩ ነው። ከምቹ ሁኔታዎቹም መካከል የታክስ ክፍያ እፎይታ፣ አምራቾች ከውጭ ለሚያስገቧቸው የምርት ግብዓቶች የሚደረጉ ድጋፎችና ሌሎች ማበረታቻዎችም አሉ። ባለሀብቶች የመሬት ሊዝ ክፍያው በዶላር መሆኑ አሁን ባለው የምንዛሬ ዋጋ አስቸጋሪ ስለሚሆን የሊዝ ዋጋው በኢትዮጵያ ብር ቢሆን የተሻለ እንደሚሆን ያቀረቡትን ጥያቄ መነሻ በማድረግ የሊዝ ዋጋው በዶላር ስሌት በብር የሚከፈልበት መንገድ እየተመቻቸ ይገኛል» በማለት ያስረዳሉ።

የኢትዮጵያ የመድኃኒትና ሕክምና መገልገያዎች አስመጪዎች እና አከፋፋዮች ማኅበር ስራ አስኪያጅ አቶ ለማ ገብረየስ በበኩላቸው፤ ፓርኩ የመብራትና ውሃን ጨምሮ ሌሎች መሰረተ ልማቶች የተሟሉለት በመሆኑ ለኢንቨስትመንት ተግባራት ምቹ እንደሆነ ይገልፃሉ። «ፓርኩ የውሃ፣ የመብራት፣ የደህንነትና ሌሎች አግልግሎቶች አሉት። ከኢንቨስትመንት ኮሚሽን፣ ከባንኮች፣ ከኢንዱስትሪ ፓርኮች ልማት ኮርፖሬሽንና ከሌሎች ተቋማት ጋር በመተባበር ባለሀብቶች ከውጭ ኢንቨስተሮች ጋር በሽርክና እንዲሰሩና ወደ ፓርኩ እንዲገቡ ማድረግ ያስፈልጋል። ጥሬ እቃዎችን አምጥቶ መሰረተ ልማቶች የተሟሉለት ፓርክ ውስጥ በማምረት የውጭ ምንዛሬ እጥረትን መቀነስ ይቻላል። ለባለሀብቶቹ የሚደረጉት ማበረታቻዎችም ትልቅ ፋይዳ አላቸው» ይላሉ።

**ወደ ቂሊንጦ ኢንዱስትሪ ፓርክ የገቡት ባለሀብቶች በማምረት ላይ፣ በግንባታ ላይ እና በዲዛይን/ጥናት ላይ የሚገኙ ሲሆኑ፤ አብዛኞቹ አምራቾች የአገር ውስጥ ባለሀብቶች ናቸው። በቀጣይ ወራትም ወደ ምርት የሚገቡ አምራቾች አሉ። ካለፈው ሐምሌ ወር ጀምሮ ወደ ፓርኩ ገብተው ለመስራት ፍላጎት ያሳዩ ባለሀብቶች ቁጥር እየጨመረ መጥቷል።**

የአገሪቱን የምጣኔ ሀብት መዋቅር ከእርሻ መር ወደ ኢንዱስትሪ መር ኢኮኖሚ ለማሸጋገር የሚያግዙ በርካታ መልካም አጋጣሚዎችና እድሎች አሉ። ይሁን እንጂ እነዚህን መልካም አጋጣሚዎች በመጠቀም የኢኮኖሚውን መዋቅራዊ ሽግግር ለማሳካት የተከናወኑ ተግባራት አገሪቱ ካላት አቅምና ፍላጎት ጋር ተመጣጣኝ አይደሉም። ኢትዮጵያ በኢንዱስትሪ ያላትን አቅም በመጠቀምና ከዚሁ ዘርፍ የሚገኘውን ገቢ በማሳደግ ወደ ኢንዱስትሪ መር ኢኮኖሚ የምታደርገውን መዋቅራዊ የምጣኔ ሀብት ሽግግር ለማሳካት አምራች ዘርፉ አሁን ካለው አፈፃፀም በብዙ እጥፍ እንዲጨምርና እንዲሻሻል ማድረግ ያስፈልጋል።

የአምራች ዘርፉ እድገት ሊሻሻል የሚችለው ከኢንቨስትመንት መስፋፋት ጋር ተያይዞ ነው። የኢንዱስትሪ ፓርኮች ደግሞ የአንድ ማዕከል አገልግሎትን ተግባራዊ በማድረግ ለኢንቨስትመንት መስፋፋት ምቹ ሁኔታዎችን የሚፈጥሩ ናቸው። ስለሆነም መዋቅራዊ የምጣኔ ሀብት ሽግግሩን ለማሳካት የኢንዱስትሪ ፓርኮችን አፈፃፀም ማሻሻል ይገባል። ይህም ባለሀብቶች ወደ ፓርኮቹ ገብተው ለማምረት የሚያስችሏቸውን የሰለጠነ የሰው ኃይልና የፋይናንስ አቅርቦት ማሟላትን እንደሚያካትት ሊታወቅ ይገባል።

የኢንዱስትሪ ፓርኮችን ለባለሀብቶቹ ምቹ ከማድረግ በተጨማሪ ትኩረት የሚሻው ሌላው ጉዳይ የአገር ውስጥ ባለሀብቶች ወደ ፓርኮቹ ገብተው በኢንቨስትመንት ተግባራት ላይ እንዲሰማሩ ማበረታታት ነው። የአገር ውስጥ ባለሀብቶች ለዘላቂ የአገር ልማትና እድገት አስተማማኝ ዋስትና መሆን የሚችሉ የልማት አንቀሳቃሾች ናቸው። በአሁኑ ወቅት በምጣኔ ሀብታቸውና በፖለቲካ ተፅዕኗቸው የዓለም ኃያላን የሆኑት አገራት የአገር ውስጥ ባለሀብቶቻቸውን በመደገፍ ረገድ በርካታ ተግባራትን አከናውነዋል። እነዚህ አገራት ባለሀብቶቻቸውን በማገዝና በመጠበቅ የሰሩት ስራ የአምራችነት አቅማቸውን አሳድጎ የምጣኔ ሀብት እድገታቸው ዘላቂ እንዲሆን አስችሏቸዋል።

የበለፀጉት የዓለም አገራት የአገር ውስጥ ባለሀብቶቻቸውን ቀደም ባሉት ጊዜያት ብቻም ሳይሆን አሁንም ከፍተኛ ድጋፍና ጥበቃ ያደርጉላቸዋል። አገራቱ በፋይናንስ አቅርቦትም ሆነ በሌሎች ዘርፎች ለባለሀብቶቻቸው የተለየ የድጋፍ መርሃ ግብር አላቸው። የበለጸጉት አገራት ለአገር ውስጥ ባለሀብቶቻቸው የሚያደርጉት ድጋፍ፣ ገና በማደግ ላይ ያሉ አገራት ከሚያደርጉት ድጋፍ ቢበልጥ እንጂ አያንስም። ለአሁኑ የምጣኔ ሀብት ኃያልነታቸው መሰረት የሆናቸው ከውጭ ጥገኝነት ያላቀቃቸው የውስጥ አምራችነት አቅማቸው ማደግ እንደሆነ ይታወቃል።

የአገር ውስጥ ባለሀብቶችን የመደገፍ ጥረት በብዙ መልኮች ሊገለፅ ይችላል። የአገር ውስጥ ባለሀብቶችን የሚያበረታቱ ምቹ የኢንቨስትመንት ፖሊሲዎችን በመቅረፅ፣ ፋይናንስን ጨምሮ ግብዓቶችን በማቅረብ፣ የመሰረተ ልማት አቅርቦትን በማሟላት እንዲሁም ቢሮክራሲያዊ የአሰራር ውጣ ውረዶችን በማቃለል ለባለሀብቶቹ ድጋፍ ማድረግ ይገባል። ባለሀብቶቹ ምርቶችንና አገልግሎቶችን በማቅረብ ከሚኖራቸው ሚና ባሻገር ለዜጎች የሥራ እድል በመፍጠር፣ ገቢ ምርቶችን በመተካት እና የወጪ ንግድን በመጨመር ትልቅ አስተዋፅኦ ስለሚኖራቸው ይህን ሚናቸውን የበለጠ እንዲያሳድጉ በመንግሥት ድጋፍ ሊደረግላቸው ያስፈልጋል።

በተለይ ኢትዮጵያ በስራ አጥነትና በዋጋ ንረት እየተፈተነች ባለችበት በአሁኑ ወቅት የአገር ውስጥ ባለሀብቶችን መደገፍ እጅግ አስፈላጊ ተግባር ነው። መንግሥት ለባለሀብቶቹ የሚያደርገው ድጋፍ ምጣኔ ሀብቱን በማነቃቃት፣ የሥራ እድል በመፍጠር፣ የገቢ ንግድ እቃዎችን በመተካት፣ የወጪ ንግድን በማሳደግ ጥቅል አገራዊ ምጣኔ ሀብት እንቅስቃሴው ዘርፈ ብዙ ለውጥ እንዲኖረው ያደርጋል። የአገር ውስጥ ባለሀብቶችን መደገፍ አገር በራሷ አምራቾች ላይ እንድትተማመን ያስችላል። ተለዋዋጭ በሆነው የዓለም ፖለቲካ ምክንያት በሚፈጠሩ ችግሮች ከሚከሰት አደጋ ለመዳንም ይረዳል።

ኢትዮጵያውያን የአገር ውስጥ ባለሀብቶች በኢንዱስትሪ ፓርኮች ውስጥ ያላቸው ተሳትፎና ድርሻ በየጊዜው እየተሻሻለ እንደመጣ ባይካድም በቂ የሚባል ግን አይደለም። አገሪቱን በየዓመቱ ለከፍተኛ የውጭ ምንዛሬ ወጪ ከሚዳርጓት ዘርፎች መካከል አንዱ የመድኃኒት ግዢ በመሆኑ የሕክምና መገልገያዎችን በአገር ውስጥ በማምረት ዘርፍ የተሰማሩ ባለሀብቶችን በመደገፍ የውጭ ምንዛሬን ማዳን እንዲሁም የአገሪቱን የጤና ዘርፍ ማሻሻል ያስፈልጋል።

ፖለቲካ እና ልዩ ልዩ

# ጎሜ

# ‹‹ጤፍ አጋደለ›› ቢለው ‹‹ገብስ እንዳይሰማ››

ምሕረት ሞገስ

‹‹ በእኔ እምነት ምንጊዜም ቢሆን እውነት ያሸንፋል። ፈጣሪ ከበጎ ሰሪዎች፣ ከንጹሀን ጎን ነው። ክፉ ሰሪ ቀኑን ይጠብቃል እንጂ የገዛ ሥራው ጠልፎ እንደሚጥለው ማረጋገጫው ትህነግ ነው።...››

እነ ዘውዴ መታፈሪያ፣ ተሰማ መንግስቴ እና ገብረየስ ገብረማሪያም ደስታ በደስታ ሆነዋል። በተለይ የገብረየስ መሳጭ ንግግር የተሰማን እና የዘውዴን አንጀት እያራሰ እርስ በእርስ በስሜት እያስተሳሰራቸው ይገኛል። ገብረየስ በበኩሉ ተሰማ እና ዘውዴ እርሱን ከማዳመጥ አልፈው ቃላቱን እያመኑበት መስማማታቸውና ቆመው በጭብጨባ መግለፃቸው አየር ላይ እየተንሳፈፈ ያለ እንዲመስለው አደረገ። በዓይኑ እምባ ሞላ።

‹‹ የትግራይ ሕዝብ እኮ ዛሬ ጉልቻ የራቀው አመድ ያጠለቀው የተበደለ ችግር ያንገላታው፤ ድጋፍ ያጣ ነው። ለእዚህ ደግሞ ዋነኛ ምክንያቱ የእነ ደብረፂዎን ሴራ እና እብሪት ነው። የትግራይ ሕዝብ ከለውጥ በኋላም ያርስ ነበር፤ ተማሪው ይማር ነበር። ነጋዴው ይነግድ ነበር። ባንክ፣ ቴሌ መብራት ነበረው። ጥጋበኛው ትህነግ ሰሜን ዕዝን ከጀርባወ በመውጋት ጦርነት ጀምሮ ወደ ሌሎች ክልሎች አስፋፋ። ዶሮ ብታልም ጥሬዋን ነውና የትግራይ ሕዝብም የአሸባሪውን ቡድን የሀሰት ፕሮፓጋንዳ ሰምቶ እና ተታሎ ‹አሸባሪው ሕወሃትና የፌዴራል መንግስት ጠበኞች ናቸው ፊት አዟዙረዋል፤ ተጣልተዋል› ብሎ በማመን ነገሩን በስፋትና በጥልቀት ሳይመረምር የቅርቡ ላይ ብቻ በማተኮር ተታለለ። ›› በማለት ገብረየስ ስለትግራይ ሕዝብ እያሰበ እንባው ፈሰሰ። ሁሉም ፀጥ ብለው ፈዘዙ። ተሰማ አይዞህ በሚል ስሜት የገብረየስን ጀርባ አሻሽቶ ቸብ ቸብ አደረገው።

ዘውዴም በበኩሉ ለገብረየስ ‹‹አይዞህ ያለፈው አልፏል። ያለውን መቀበል ነው። ወንድም በወንድሙ ላይ አይጨክንም፤ ሁሉም ኢትዮጵያዊ ነው። ከዚም ከዚያም ሁሉም ተጎድቷል። ብዙ ኢትዮጵያውያን ሞተዋል። ከሥልጣን በፊት አገርና ሕዝብ ማስቀደም ያቃታቸው በገሃዱ ዓለም ሲቃዡ የኖሩ ትህነጎች ኢትዮጵያ ላይ ፈልተው ኢትዮጵያን ነቀዝ ሆነው ቦርቡረዋታል። በድህነትና በኋላቀርነት በምትማቅቅ አገር ላይ ጦርነት በማወጅ ተጨማሪ ውድቀት እንዲኖር ምክንያት ሆነዋል። ልክ ከ30 ዓመት በፊት ሥልጣን በአጋጣሚ እጃቸው ሲገባ ኢትዮጵያውያንን በጠላትነት እየፈረጁ ሲያስሩ፣ ሲያሰቃይ፣ ሲያሳድዱና ሲገድሉ እንደኖሩት ሁሉ አሁን ደግሞ የትግራይ ሕዝብን ምሽግ አድርገው ተጫወተውበታል።

መደበቃቸው እና ሕዝብ ውስጥ ተሸሽገው ጦርነት መክፈታቸው በ27 ዓመት በስልጣን ዘመናቸው ከመንግሥታዊ ተቋማት በቢሊዮን የሚቆጠር ሃብትን የመዝረፍ ተግባራቸውን ለማስቀጠል ነበር። ያም አልሆን፤ ካልሆነላቸው ደግሞ ከገደሉትና ከዘረፉት ሕዝብ ተጠያቂነት ለማምለጥ በማሰብ ነበር። ሆኖም እንዳሰቡት አልሆነም። እንደውም ሥራቸው በጥፋት ላይ ጥፋት ሆነ። ያለፈውን ጥፋት ሕግ ፊት ቀርበው ፍርዳቸውን መቀበል ሲገባቸው በበለጠ መልኩ እጃቸው በንፁኃን ደም አጨማለቁት። ከሕግ ለማምለጥ ሲሉ የትግራይ ሕዝብ ውስጥ ተደብቀው ጦርነት ከፈቱ። የአገር አለኝታ የሆነውን መከላከያን አጠቁ።

መንግስት ሕዝብ ከሚያልቅ ሕግ ማስከበር ይዘግይ ሲል፤ በአገር ውስጥ በሌሎች አካባቢዎች ሕገወጥነትና ሥርዓተ አልበኝነት እንዲሰፍን የተቻላቸውን ሁሉ ሰሩ። ያም አልሳካ ቢላቸው፤ ሌላ አካል ያወደማቸው ያጠቃቸው የከበባቸው አስመስለው ተበዳይ መስለው የትግራይነትን ጭምብል በማጥለቅ በደም መነገዳቸውን ቀጠሉ። ወረራቸውን አጧጧፉ። የትግራይን ሕዝብ አታለው ከገዛ ወንድሙ ጋር አጋደሉት።›› በማለት ዘውዴ ትህነግ ምን ያህል በትግራይ ሕዝብ እየነገደ እና ከገዛ ወንድሞቹ ጋር እያናከሰው እንደሆነ ገለፀ።

ተሰማ የፌዝ ሳቅ እየሳቀና ፈገግ እያለ፡ ‹‹አሸባሪው ትህነግ መሠረቱ ውሸት ነው። ውሸቱን ለማሳመን የማይቆፍረው ጉድጓድ የለም። ዓላማውን ለማስፈጸም የሚጠቀመውን ውሸት በእውነትን በመተካት ትግራይም ሆነች መላው ኢትዮጵያ የሴረኛው የትሕነግ መጫወቻ እና መፈንጫ እንዳንሆን ጥረት ማድረግ አለብን። መሸወድ የሌለብን አሁን ላይ ትህነግ መሀረብ ዘርግቶ እያለቀሰ ነው። ምንም ነገር ለመፈፀም ጥንካሬ የለውም።

ነገር ግን የትግራይን የድሃ ልጅ እየማገደ የራሱን ቤተሰብ አውሮፖና አሜሪካ አስቀምጦ ዛሬም የትግራይን ሕዝብን መደበቂያ በማድረግ እንደተራ የብረት መሳሪያ እንደባሪያ እየተጠቀመበት ነው። ጥንታዊ የጦርነት ዘይቤ በመከተል በሠው ማዕበል በመዋጋት ሕዝብ እያስጨረሰ ትውልድ እንዲነጥፍ ምክንያት በመሆን ላይ ያገኛል። የተለያዩ የመረጃ ተቋማት እንደሚያሳዩት አሸባሪው ትህነግ ጦርነቱን እንዲገፋበት ከአንድ አገር ሁለት ሚሊዮን ዶላር እንደተበረከተለትና በየ 45 ቀኑም 500 ሺ ዶላር ድጋፍ ሲደርግለት እንደቆየ ምስጢራዊ ሰነዶች እያረጋገጡ ነው።

ይህ ከውጪ ጠላት ጋር አብሮ ኢትዮጵያን ለመጣል እየተጋ ያለ ምስጥ በሕዝብ መሸነፉ እና በድጋሚ ላይነሳ መቀመቅ መውረዱ አይቀርም።›› በማለት የሽብር ቡድኑ አቅም እንደሌለው ሳይወድ በግድ ሽንፈቱን እያረጋገጠ መምጣቱን አይተነዋል። እሱ ግን በኢትዮጵያ ጠላቶች እየታገዘ መሆኑን ተናግሮ በረዥሙ ተነፈሰ።

ዘውዴ ከተሰማ ቀጠል አድርጎ ‹‹ ይህንን የኢትዮጵያ ጠላት ‹ጤፍ አጋደለ› ቢለው ‹ገብስ እንዳይሰማ› እንደተባለው የእርሱ መጥፎ አርአያነት ወደ ሌላው እንዳይዛመት ቀጥቅጦ ሕግ ፊት ማቅረብ እና የማያዳግም እርምጃ መውሰድ ያስፈልጋል። አገር ውስጥ ሲፈፀም የነበረው ግፍ በሙሉ ለማመን ቢያስቸግርም ብዙሃኑ በእርሱ ሴራ በተጠረገ የክፋት መንገድ የተካሔደ ስለመሆኑ አያጠራጥርም። ዜጎች ማንነታቸው እየተለየ ሲጨፈጨፉና የተረፉት ሲፈናቀሉ የነበረው እርሱ ከውጪ ጠላት ጋር በነበረው ትስስር እና ባገኘው ድጋፍ ተመስርቶ እንዲሁም በስልጣን ዘመኑ የነበረ ኔትወርኩን ተጠቅሞ ነበር።

በዛ ጭፍጨፋ፣ በዛ መፈናቀልና ዘረፋ የትግራይ ሕዝብ በምንም መልኩ ተጠቃሚ የሚሆንበት ዕድል የለም። እንደውም ከተጠቃሚነቱ ይልቅ ተጎጂነቱ እንደሚያመዝን አያጠራጥርም። በሴራ ፖለቲካ የተካኑ፤ የሚፈልጉትን ዓላማ ለማሳካትና አገር እስከማፍረስ የወጠኑት የአሸባሪው ትህነግ አባላት በማንነት ላይ ያነጣጠሩ ጥቃቶችንና ጭፍጨፋዎች እንዲፈፀሙ በተለያዩ ቦታዎች ላይ ሲጭሩ የነበረው እሳት ወላፈኑ ቢያንስ በስነልቦና ደረጃ የትግራይ ተወላጅን ሲያስጨንቅ ነበር።

እነዚህ በትግራይ ሕዝብ ላይ፣ በአማራ ሕዝብ ላይ፣ በአፋር ሕዝብ ላይ፣ በኦሮሞ ሕዝብ ላይና በሌላውም ሕዝብ ላይ በአጠቃላይ በኢትዮጵያውያን ላይ መከራን እንደዝናብ ያዘነበው የእፉኝት ልጆች የእነርሱ ክህደት ወደሌላው እንዳይጋባ መቀጣጫ እንዲሆኑ እስከጫፍ ድረስ መቀጣት አለባቸው።›› ሲል በምሬት ትህነጎች ሲሰሩ የነበረውንና ክፋታቸውን በመዘርዘር ቅጣት ይገባቸዋል ሲል ደመደመ።

ገብረየስ ተሰማ እስኪናገር አልጠበቀም። ይልቁኑ እርሱም የሚያምንበትን ለመናገር ጉሮሮውን ጠራረገ። ‹‹ በእኔ እምነት ምንጊዜም ቢሆን እውነት ያሸንፋል። ፈጣሪ ከበጎ ሰሪዎች ጎን ነው። ክፉ ሰሪ ቀኑን ይጠብቃል እንጂ የገዛ ሥራው ጠልፎ እንደሚጥለው ማረጋገጫው አሸባሪው ትህነግ ነው። አሁን ‹ገዳይ ሲያረፋፍድ ሟች ይገሰግሳል› ሆኗል። ሕዝብ ተደግፎ በዛው ሕዝብ ላይ መጫወት በራስ ላይ አደጋ መጋበዝ ነው። አሸባሪው ትህነግ እያደረገ ያለው ይህንኑ ነው። ሕዝብ ተደግፈው በዛው ሕዝብ ላይ መቀለዳቸውን አላቆሙም። አሁንም ድረስ ቁማራቸውን እንደቆመሩ ነው። በነፍስ ላይ ቁማር በመጫወት ሃሳብ ናውዘዋል። ተበላን ብለው አያስቡም። ንብረቱን ጨርሶ ሚስቱን ለቁማር ሲል ለመሸጥ እንደተዘጋጀ ነፈዝ ሱሰኛ አባወራ በደመነፍስ በሱስ ውስጥ ሆነው እየገሰገሱ ነው።›› አለ።

ተሰማ በመገረም መንፈስ፤ ‹‹ አንዳንድ ሰው በራሱ በቀላሉ ከችግር ማምለጥ ሲችል ራሱን እና ሌላውንም ችግር ውስጥ በመክተት የባሰ ከችግር የመውጫ መንገዱን የበለጠ ያወሳስበዋል። በራሱ ላይ ይቆልፋል። መውጫ በሚያሳጣ መልኩ በራሱ ላይ ቁልፉን ያጠብቀዋል። ሌሎች ደግሞ ይህ እንዳይፈጠር ከመምከር ይልቅ አብረው መሳሪያ ይሆናሉ። ከዚያም አብረው ይታሰራሉ። እነርሱም ራሳቸው ላይ በተመሳሳይ መልኩ ይቆልፋሉ። የትህነጎች ላቅ ይላል። ጥቂቶች ቢሆኑም ብዙሃኑ ሕዝብ ላይ ቆልፈዋል።

የአሸባሪው ትህነግ ቡድን ሕዝቡ እንዲሰቃይ የተቻላቸውን ሁሉ አድርገዋል። ህዝቡ በሌላው ኢትዮጵያዊ እንዲጠላ ብዙ ሰርተዋል። በግጭት አድገው ከግጭት ውጪ ማሰብ የተሳናቸው መሆኑን በግልፅ አሳይተዋል። ሰው እያፈሱ ጦርነት ውስጥ መማገድ መደበኛ ሥራቸው ሆኗል። በጦርነቱ ከተገደለው በላይ በትህነግ አፈሣ በማስገደድ የታጠቀውን የራሳቸውን ሠራዊት ሸሽተሃል በሚል ራሳቸው እየረሸኑ በብዙ ሺህ ጨርሷል።›› ሲል የገብረየስን ሃሳብ በመደገፍ ትህነጎች በራሳቸውም ሆነ በተለይ በትግራይ ሕዝብ ላይ ምን ያህል ነገሮችን እንዳወሳሰቡ ለመግለፅ ሞከረ።

ዘውዴ በበኩሉ፤ ‹‹ጥንቃቄን ከዕድለ ቢሱ ይማሩታል፤ በእርግጥም ከእነዚህ በደንብ መማር ያስፈልጋል። በአንዱ ላይ የታየው መጥፎ ነገር ለሌላው ትምህርት ይሆናል። በስልጣን ላይ ሆኖ መንደላቀቅ ሕዝብ እስከፈቀደበት ቀን ብቻ ነው። ከስልጣን ከወረዱ በኋላ ደግሞ ቢያንስ እንደማንኛውም ተራ ሕዝብ ለመኖር ራስን ማዘጋጀት እና ላጠፉት ጥፋትም ሃላፊነት ወስዶ ቅጣትን መቀበል ይሻላል። በእኛ ውብ ባህልም የቅርታም እኮ ነበር። እሱንም ለመቀበል ዝግጁ አይደሉም እንጂ። ከዛ ውጪ ከሕዝብ አመልጣለሁ ብሎ ሴራ መጎንጎንም ሆነ ከውጪ ጠላት ጋር እስከ ማበር የደረሰ የአገር ክህደት መፈፀም፤ ከምንም አያስመልጥም። ይልቁኑ የመኖሪያ እና ምህረት የማግኛ ጊዜን ሙሉ ለሙሉ ማጣት ነው።

ትህነጎች እስከ አሁን ያጠፉት ለመቁጠር ያዳግታል። የኢትዮጵያን ህልውና በመፈታተን እስከሚችሉት ድረስ ሞክረዋል። በኢትዮጵያ ሰላም እንዳይሰፍን ሰማይ እስከመቧጠጥ ለመድረስ ከአቅማቸው በላይ ተንጠራርተዋል። ነገር ግን አልሆነላቸውም። ይህ ህልማቸው ቅዠት መሆኑን የኢትዮጵያ ሕዝብ አረጋግጦታል። ገሚሶቹ በዛው በበረሃ ሲሸሹ እንደሞቱት ሁሉ፤ አሁንም ሆነ ወደፊት ቀን ሲደርስ እያንዳንዳቸው የአሸባሪው ትህነግ አባላት የትም ሜዳ እንደሚበተኑ አልጠራጠርም።›› ብሎ በንግግራቸው መሃል ረስተውት የቆዩትን ከተቀዳ የቆየው ድራፍት ተጎነጩ።

ገብረየስ ‹‹በዋናነት እንድትዘነጉት የማልፈልገው ግን›› አለ። ቀጠለና ‹‹ገመድ ቢበጠስ መቀጠል፤ አባይ መስካሪን ወደ ገደል ነው። የትግራይ ሕዝብ ብዙሃኑ በተለይ አሁን ትህነግን ተቀብሎ ሳይሆን አማራጭ አጥቶ ነው። አማራጭ ያጣ ሕዝብ መሆኑን፤ በትህነግ ተገዶ ለጦርነት መሰለፉን፣ ማወቅ ተገቢ ነው። እኔ አሁን የሚያሳስበኝ የትግራይ ሕዝብ ጉዳይ ነው። ትህነጎች የተሸነፉት በሕዝብ ተደግፈው ሕዝብን በሸጡበት ቀን ነው። አሁን ጫፍ ላይ ደርሰዋል። በእርግጥም እነርሱ እንዲሞቱ አይደለም፤ መቀጣጫ እንዲሆኑ ለፍርድ እንዲቀርቡ መንግሥትም ሆነ አገር ወዳድ ማንኛውም ኢትዮጵያዊ ምኞቱ መሆኑ ትክክል እና ተገቢ ነው። እንኳን እንደ አሸባሪው ትህነግ አይነቱን አገር ከጂ ቀርቶ ማንኛውንም የጥፋት ፀባይ ተጠቂ በህግ መቅጣት ተገቢ ነው። ባለ ክፉ ፀባይ አሸባሪው ትህነግን ማስተማር ይገባል።

ነገር ግን ድህነት ያመሳቀላቸው ለግል ሥልጣንና ጥቅማ ጥቅም ሲል አሸባሪው ትህነግ የተጫወተባቸው የትግራይ ተወላጆችን ላይ ጨፌ ተቃጠለ እንደሚል ወሬኛ ያልሆነ የሆነውን በማውራት ከገበታ ከማራቅ ይልቅ ተጠግቶ፤ እነርሱም ከማንኛውም የኢትዮጵያ ሕዝብ የተለዩ አለመሆናቸውን፤ ሌላው ህዝብ አሸባሪው ትህነግን እንጂ ከትግራይ ህዝብ ጋር ምንም ዓይነት የጠላትነት ስሜት የሌለው ስለመሆኑ መግለፅ ያስፈልጋል። ምክንያቱም አሸባሪው ትህነግ ቢጠፋ እንኳ ዘርቶት የሚሔደው ክፋት እና እስከ አሁንም በትግራይ ሕዝብ አዕምሮ ውስጥ ክፋትን ለማተም ሲል ሲሰራ የነበረው ፕሮፖጋንዳ ቀላል ባለመሆኑ በዚህ ላይ ከወዲሁ ማሰብ ያስፈልጋል።›› አለ።

ዘውዴ ‹‹ ትክክል ነው። ከዚህ በኋላ ሁሉም አንድ ሕዝብ ነው። ለኢትዮጵያ አንዱ ባለቤት እየሆነ ሌላው ባይተዋር የሚሆንበት ጊዜ ያበቃል። ሕዝብ ለዛውም የኢትዮጵያ ሕዝብ ገራገር ነው። እርስ በእርሱ ይቅር ተባብሎ፤ ተጫውቶ ተስማምቶ መኖሩ አይቀርም። ዋናው ነገር ከዚህም በኋላ ማንም ቢሆን ቂምና ተንኮልን በማስወገድ ደግ ሆኖ ቤተሰቡን እና አገሩን መምራት አለበት። የትግራይ ሕዝብማ የት ይሔዳል ያው ወንድማችን ነው። ቀን ሲያልፍ አብረን ተቃቅፈን ማዕድ መጋራታችን አይቀርም። ይህ ቀን ሩቅ እንደማይሆን እርግጠኛ ነኝ።›› ሲል የዕለቱን ጨዋታቸውን አብቅተው። ሁሉም ከመጠጥ ቤቱ ለመውጣት አኮበኮቡ። ዘውዴ ሰውነቱን እያንጠራራ በመጨረሻ ‹‹ የአሸባሪው ትህነግ መዋረጃው ተቃርቧል›› ሲል ተናገረ።

ስፖርትና መዝናኛ

# የዘመን ጥበብ

## ሕይወቱም ሥራውም ቅኔ የሆነው ጥበበኛ

ዋለልኝ አየለ

ሙሉጌታ ተስፋዬ የሚታወቀው በግጥም መድብሎቹ እና በዘፈን ግጥሞች ነው። ይህን ሰው በቅርብ የሚያውቁትን ሰዎች ጨምሮ ታሪኩ የሚናገረው ግን ሥራዎቹ ብቻ ሳይሆን ሕይወቱ ራሱ ቅኔ ነው። የጽሑፋችን ዓላማ የሕይወት ታሪኩ ላይ ስላልሆነ እንጂ ገጠመኞቹ ሁሉ አስቂኝና አሳዛኝ ናቸው። በአጠቃላይ ከተለመደው ወጣ ያለ ሕይወት የነበረው ነው።

ስለሙሉጌታ ተስፋዬ ብዙ ቢባልም ለዛሬው ስለእርሱ ሥራዎች ለማውራት የተነሳነው ግን ባለፈው ቅዳሜ ጥቅምት 5 ቀን 2015 ዓ.ም ‹‹አያ ሙሌን በነቢያት ጉባኤ›› በሚል ውይይት ተደርጎ ስለነበር ነው። መድረኩን ያዘጋጁት የኢትዮጵያ ብሔራዊ ቤተ መዛግብትና ቤተ መጻፍት ኤጀንሲ (ወመዘክር)፣ ኢጋ ሚዲያና ኮምኒኬሽን እና ጎተ ኢንስቲትዩት ናቸው።

አርክቴክትና የስነ ጽሑፍ ባለሙያው ሚካኤል ሽፈራው ለውይይት መነሻ ሀሳብ አቅርበዋል፤ ከታዳሚዎች ሀሳቦች ተነስተዋል። በተለያዩ ገጣሚያን የተገጠሙ ግጥሞች እና የሙሉጌታ ተስፋዬ (አያ ሙሌ) ግጥሞች ቀርበዋል።

የውይይት መነሻ ሀሳቡን፣ ከታዳሚዎች የተነሱትን እና አጠቃላይ ስለባለቅኔው ሙሉጌታ ተስፋዬ የተባሉትን ጠቅለል አድርገን እናቀርባለን።

ሙሉጌታ ተስፋዬ የኖረበትም ሆነ የግጥም ሥራዎችን የጀመረበት ዘመን የፈተና ጊዜያት ነበሩ። በተለይም ታዋቂ ገጣሚ የሆነው ኢህአዴግ በመጣባቸው የመጀመሪያዎቹ ዓመታት (1980ዎቹ) ነው። የመጨረሻው ግጥሙ ደግሞ በ1996 ዓ.ም ነው። አንዳንዶቹ ግን ቀን የሌላቸው ናቸው።

ኢህአዴግ ደርግን አስወግዶ አገሪቱን ሲቆጣጠር መደማመጥ አልነበረም፤ በዚያን ጊዜ ትንሽ ማስተዋል የነበራቸው ባለቅኔዎች ነበሩ። ጸጋዬ ገብረመድኅን የዚያን ጊዜ ነው ‹‹ሀ ሁ ወይም ቀ ቁ›› የተሰኘውን ሥራውን የጻፈው። ወይ አዲስ ታሪክ እንጀምራለን ወይም የነበረውን እናስቀጥላለን ለማለት ነው። እነዚህ ሰዎች የግላቸውን ጉዳይ ሳይሆን አገራዊ የሆኑ ሁኔታዎች ላይ ያስቡ ነበር።

ሙሉጌታ ተስፋዬ ግጥሞቹን የሚጽፈው አጠገቡ ካሉ ነገሮች ነው፤ አይቷቸው ስሜቱን የነኩትን ነገሮች ነው። ኃላፊነትን ሌሎች ሰዎች ላይ መጣል ሳይሆን ራስን መታዘብን ይናገራል።

የሙሉጌታ ግጥሞች የክርስትና ኃይማኖት መንፈስ ያላቸው ናቸው። በሕይወቱም የዓለም በቃኝ አይነት የምናኔ ሕይወት ያለው ነው። መቆዘም እና ብቻውን መሄድ ያበዛል። ራሱን ሁሉ እስከመጣል ደርሷል፤ በእነዚህ ፍልስፍናዎቹ ነው ሀሳቦችንም እያረቀቀ የሚጽፋቸው። በመንፈስ የሰመጠ ሰው ስለሆነ ሥራዎቹም ከዚያ የሚቀዱ ናቸው።

ሙሉጌታ ግጥም ሲጽፍ ከቃል ውስጥ ቃል ይፈጥራል። ለምሳሌ መስከረም የሚለውን ቃል መሰከረ፣ መስከ.. የሚሉ ቃላት ሊያወጣለት ይችላል።

አሁን በመድብል የሚታወቁት የሙሉጌታ ተስፋዬ ግጥሞች አንዳንዶቹ በስንዱ አበበ አማካኝነት ተሰብስበው የታተሙ ናቸው። በቅርበት የሚያውቁት ሰዎች እንደሚሉት ሙሉጌታ ግጥም ጽፎ የሆነ ቦታ ጥሎት ሊሄድ ይችላል። ስለዚህ ለህትመት ያልበቁ ወድቀው የቀሩም ሊኖሩ ይችላሉ።

ገጣሚ መንግሥቱ ዘገየ የሙሉጌታ ተስፋዬ ግጥሞች ወደ ተረትነት እንዳይቀየሩ ስጋት እንዳለው ተናግሯል። ስለዚህ ሙሉጌታ ማነው የሚለው መነገር አለበት። ብዙ ጊዜ በመገናኛ ብዙኃን ቃለ መጠይቅ አያደርግም፤ ግን የቅርብ ጊዜ ታሪክ እና በሕይወት ያሉ ሰዎች የሚያውቁት ነው።

መንግሥቱ ዘገየ ላሊበላ ለሥራ ጉዳይ ሄዶ፤ ‹‹ከሙሉጌታ ተስፋዬ በዕድሜ ሊያንስ የሚችል ሰው አግኝቼ ‹ሙሉጌታ ተስፋዬን ታውቀዋለህ?› ብየ ጠይቄው ‹ጓደኛዬ ነው!› አለኝ›› ብሏል። የሚያውቁት ሰዎች ሁሉ ‹‹ጓደኛዬ ነው›› ብለው ነው የሚናገሩ።

ባለሙያዎቹ እንደሚሉት፤ የሙሉጌታ ግጥሞች የሕዝብ የቃል ግጥሞችን አይነት ለዛ ያላቸው ናቸው። በዚህም ምክንያት እነርሱ የገጠማቸው መሆናቸው ካልተገለጸ ምናልባትም የሕዝብ ስነ ቃል ሊመስሉ ይችላሉ። ምክንያቱም ሀሳቦቹ ሁሉ ከአገር ቤቱ ባህልና ወግ የሚቀዳ ነው። ለምሳሌ፤ ‹‹ደስ ይላል መስከረም›› የሚለው ግጥም የገጠሩን አርሶ አደር ሕይወትና ሊጋስነት የሚገልጽ ነው። ግጥሞቹ ፎክሎራዊ ባህሪ ያላቸው ናቸው።

በውይይቱ ላይ ከተነሱት ሀሳቦች አንዱ፤ የሙሉጌታ ግጥሞች ጠጠር ያሉ ቃላት የያዙ ናቸው። ስለዚህ አዘጋጁ (የነብያት ጉባኤን መድብል) የግርጌ መግለጫ ቢያስቀምጥባቸው የሚል ነው። በነገራችን ላይ በዕውቀቱ ሥዩም በአንዳንድ ግጥሞቹ ሥር አዲስ ይሆናሉ ብሎ ያሰባቸውን ቃላት የግርጌ መግለጫ ያስቀምጥባቸዋል።

የሙሉጌታ ግጥሞች እንደተባለውም ጠጠር ያሉ ቃላት የያዙ ናቸው። የግዕዝ ቃላት አሉት፤ አንዳንድ ቦታ ደግሞ የአገር ቤቱን ለዛ ላለመልቀቅ ሲል ማህበረሰቡ በሚጠቀማቸው ቃላት የጻፋቸው አሉ። እነዚህ ቃላት ለከተሜው ነዋሪ አዲስ እንደሚሆኑ ግልጽ ነው። ስለዚህ አዘጋጆች መግለጫ ቢያደርጉባቸው ያስፈልግ ነበር።

ሙሉጌታ ተስፋዬ በግጥም መድብሎች ላይ ባሉት ግጥሞች መጽሐፉን ያነበበ ያውቀዋል። አብዛኛው ሰው ግን የሙሉጌታ ተስፋዬ ግጥሞች ባሉባቸው ዘፈኖች ተመስጧል፣ ተክዟል፣ ተደስቷል፣ አልቅሷል።

ለምሳሌ፤ የታምራት ደስታ ‹‹ሐኪሜ ነሽ›› የተሰኘው ዘፈን ግጥም የሙሉጌታ ተስፋዬ ነው። ይህን ዘፈን ብዙ ወጣቶች ፍቅራቸውን ገልጸውበታል።

የብፅዓት ሥዩም ‹‹አደራ ልጄን አደራ›› ዘፈን በብዙዎች ዘንድ ይታወቃል፤ ይወደዳል። የዚህ ዘፈን ግጥም የባለቅኔው ሙሉጌታ ተስፋዬ ነው። በሌሎች የብጽዓት ሥዩም ዘፈኖች ውስጥም የሙሉጌታ ግጥሞች አሉ።

ሙሉጌታ ለብዙ ዘፋኞች ግጥም ሰጥቷል። ለዘፋኞች በጣም ቅርብ ነበር። ፍቅርአዲስ ነቃዐጥበብ በአንድ ቃለ መጠይቅ ላይ ሙሉጌታ ብዙ ዘፋኞችን እንዳበረታና ትልቅ ደረጃ እንዳደረሰ ረዘም ያለ አስተያየት ስትሰጥ ሰምቻለሁ።

ከሙሉጌታ የዘፈን ግጥሞች ውስጥ በብዙዎች ዘንድ የታወቀውና የተለመደው የአበበ ተካ ‹‹ወፍዬ›› ነው። በዚህ ዘፈን ግጥሞች ከወጣት እስከ አዛውንት ያልተመሰጠ፣ ያልተከዘ፣ በምናብ ያልተዋጠ የለም። ሙሉጌታ ተስፋዬ በዚያ ዘፈን ውስጥ ባሉ ግጥሞች፤ ተፈጥሮን ከምናብ፣ እንስሳትን ከሰው፣ አካባቢን ከጠፈር፣ የቅርብ ያለን ነገር ከሩቅ ያቆራኘበት ነው። የሰውን ልጅ የማሰብ ህሊና የሚታዘብ ግጥም ነው። የዚህን ዘፈን ግጥሞች እናስቀምጣቸው።

ጭራ ጭራ የምታድረው
ጭራ ለቅማ የምታድረው

**ከሙሉጌታ የዘፈን ግጥሞች ውስጥ በብዙዎች ዘንድ የታወቀውና የተለመደው የአበበ ተካ ‹‹ወፍዬ›› ነው። በዚህ ዘፈን ግጥሞች ከወጣት እስከ አዛውንት ያልተመሰጠ፣ ያልተከዘ፣ በምናብ ያልተዋጠ የለም። ሙሉጌታ ተስፋዬ በዚያ ዘፈን ውስጥ ባሉ ግጥሞች፤ ተፈጥሮን ከምናብ፣ እንስሳትን ከሰው፣ አካባቢን ከጠፈር፣ የቅርብ ያለን ነገር ከሩቅ ያቆራኘበት ነው።**

ጭራ ጭራ የምታድረው
ጭራ ለቅማ የምታድረው
እንዲህ አስናቀችኝ...
ቀድማኝ ጎጆ ወጥታ ጎጆ አስተማረችኝ
ጎጆ ...አቤት ጎጆን... ወፍዬ አስቀናችኝ፤
እህህ... ምነው ባደረገኝ
እህህ... የሷ ጋሻ ጃግሬ
እንደምንም ብዬ እኔም ጥሬ ግሬ
ያገዳ ጎጆዬን ባቆምኳት ማግሬ፤
እህህ... አጉል በቃኝ ላ'ይል
እህህ... አይን አይቶ ገምቶ
ወይ ሞልቶ ላይሞላ ጆሮ አይችሉ ሰምቶ
እንዴት ጎጆ ይቅር አርሶና ሸምቶ
ገመና ከታቹ የሣር ቤት ያማረሽ
ሚስጥረ መለኮት ማነው ያስተማረሽ
ካፈር ከዳን ጎጆ መሬቱን ፈልፍሎ
ከሰማይ ቤት እጣሽ ማን በሰጠኝ ከፍሎ
እኔን እኔን እኔን ይብላኝ
እኔን አይኔን እኔን ይብላኝ...
እኔን እኔን እኔን ይብላኝ
እኔን አይኔን እኔን ይብላኝ...
የቀን ሰው ሌጣ አፈር
ልቤ ሩቅ አሳቢው ቅርብ አድሮ ሲደፈር
ምን ነበር ቢቆጨው ጎጆ አጥቶ ከማፈር፤
እህህ... ፈጣሪዋን አምና
ያፏን ጥሬ ሰጥታ
ለጭሮ አዳር ውሎ በዝማሬ ወጥታ
አዳኝ እንዴት ያጥቃት ፍርድና ዳኛ አጥታ
እህህ... አጣሁ፣ ነጣሁ ብላ
እንደሰው ባይከፋት
ምፅዋት ባትለምን ተርፎን ባንደግፋት
ጎጆዋ ለቻላት ምን ነበር ባንገፋት
ታማ ትንፋሽ አጥሯት ደክማ ስታጣጥር
ማን ያቃናት ይሆን፥ ውለታ ሳይቆጥር
ወልዶ ማሳደጉን ብዙ ሰው ቢያውቅበት
ያፉን ማን ይሰጣል የእጁ ሲርቅበት
እህህ... ወፊቱ
ኡሁሁ... ወፍዬ

በእነዚህ ስንኞችና እንጉርጉሮዎች ውስጥ የራሱ የሙሉጌታ ተስፋዬ ሕይወት ይታያል። ‹‹ታማ ትንፋሽ አጥሯት፣ ደክማ ስታጣጥር፤ ማን ያቃናት ይሆን ውለታ ሳይቆጥር›› የምትል ስንኝ አለች። አንድ የሙሉጌታን ድርጊት ብቻ እንጥቀስ።

መቼም ብዙ ጊዜ ብቻውን መሄድ ይወዳል ነው የሚባለው። አንድ ዕለት አንድ በባዶ እግራቸው የሚሄዱ ሰውየ ያገኛል። ያስቆማቸውና ትንሽ ካወራቸው በኋላ ‹‹እስኪ ይሄን ጫማ ይለኩት›› ብሎ ጫማውን አውልቆ ይሰጣቸዋል። ሰውየው ጫማውን ሲለኩት ልክክ አለ። ‹‹አሁን መሄድ ይችላሉ›› ብሎ በባዶ እግሩ ጉዞውን ቀጠለ።

የሙሉጌታ ግጥሞች አብዛኞቹ ረጃጅም ናቸው። ከቃል ላይ ቃል እየፈጠረ፣ ከአንድ ሀሳብ ላይ ሀሳብ እያወጣ አንባቢን ጭምር ሌላ የራሱን ሀሳብ እንዲያስብ ያደርጋል። ሲፈልግም አንባቢው የራሱን የሕይወት ውጣ ውረድ በገጠመኞቹና ሙሉጌታ ባስተዋላቸው ዕይታዎች ውስጥ እያስገባ ይመሰጣል።

እንዲህ አይነት ፈላስፋዎች ብዙ ጊዜ የራሳቸውን ሕይወት በምቾት አይኖሩም ይባላል። የሙሉጌታ ተስፋዬ ሕይወትም እንደዚያ ነው፤ ብዙ የምቾት አጋጣሚዎችን ጥሎ ይሄዳል ይባላል። መሽቀርቀር የሚያስችል አቅም እያለው የተጎሳቆለ ሕይወት ሲኖር ቆይቷል። በዚህ ሕይወቱ ውስጥ የጎስቋሎችን ሕይወት የሚያሳዩ ሥራዎችን አስቀምጣል።

እነሆ ከጎስቋላ ሕይወቱ ይልቅ በሥራዎቹ ሲታወስ ይኖራል!






ማህበራዊ

# ልዩ ልዩ

## ሴቶች በአስከፊው የጎዳና ህይወት

መልካምሥራ አፈወርቅ

ከዋናው ጎዳና አለፍ ብሎ ከሚገኝ የሆቴል ቤት በረንዳ አንዳቸው በአንዳቸው ላይ ተደራርበው ተኝተዋል። በወጉ ያልተሸፈነው የአብዛኞቹ እግር ውሀ አይቶ የሚያውቅ አይመስልም። የጎዳና አቧራ፤ ጭቃ፤ ዝናብና ጸሃይ ስለተፈራረቀባቸው ወጣቶች ቢሆኑም በለጋ ዕድሜያቸው ወይበዋል።

ሁሉም በሚባል መልኩ በከባድ ዕንቅልፍ ውስጥ ናቸው። እንዲህ መሆኑ አዲስ የሚባል አይደለም። ምናልባት አንዳንዶች ርሀብ ቀስቅሷቸው ሊነሱ ይችሉ ይሆናል። በርካቶቹ ግን ወፍ ተንጫጭቶ እግረኞች መንገድ እስኪጀምሩ ከአስፓልቱ ጥግ ተዘርረው ማርፈዳቸው ተለምዷል።

ወደቀደመው መነሻዬ ልመለስ፣ ከመንገዱ ዳርቻ ወዳስተዋልኩት የሆቴል ቤት በረንዳ። በዚህ ምሽት አስቀድመው ጥግ የያዙ የጎዳና ልጆች ጎናቸውን አሳርፈው ዕንቅልፋቸውን እየተለማመጡ ነው። በእንዲህ አይነቱ ስፍራ ከዕንቅልፍ ጋር በዋዛ መገናኘት ዘበት ይሆናል። ባልተመቸው መኝታ መሀል እራፊን ተጋፈው ከሚጋሩት ትንፋሽ በምትገኝ ስስ ሙቀት ራስን እያታለሉ ብርድን ማሸነፍ የግድ ይላል። አጋጣሚው አግዞ በድካም መረታት ከተቻለ ደግሞ ዕድለኛነት ነው። ይህን አልፈው ባልተመቸ ጎናቸው ህልም የሚያዩና ቅዠት ጭምር የሚጎበኛቸው አይጠፉም። ይህም ዕድል ነው ከተባለ ‹‹እሰዬው›› ነው።

ምሽቱ ተገባዷል። ምናልባትም እኩለሊቱ እየተጋመሰ ነው። አሁንም ርዕሰ ጉዳዬ ከሆቴሉ በረንዳ ነው። ተደራርበው ከተኙት የጎዳና ልጆች መሀል በአይኗ ዕንቅልፍ ይሉት ያልዞረባት ወጣት በንቃት ተቀምጣ አካባቢዋን ትቃኛለች። ወጣቷ በዙሪያዋ ተኝተው ዕንቅልፍ በጣላቸው ባልንጀሮቿ የቀናች አትመስልም። አሁንም ትኩረቷ ዙሪያ ገባውን መቃኘት ብቻ ነው። ለአፍታ እረፍት ይሉት የላትም። ኮሽታ እያዳመጠች፣ ዓይኖቿ እዚህም እዚያም ይቃብዛሉ።

ለሊቱ እየገፋ ቅዝቃዜው እየከፋ ነው። እንዲያም



ሆኖ ወጣቷ ጎኗን ከጓደኞቿ አስጠግታ ሙቀት መጋራት አላሻትም። እንዲህ ላድርግ ብትል የሚሆነውን አሳምራ ታውቃለች። ቢደክማትና ቢያማት እንደሌሎች መኝታን አያምራትም። ድካም ህመሟን ዋጥ አድርጋ እንደሁሌው ዙሪያ ገባዋን ትቃኛለች። በንቃትና በተለየ ጥንቃቄ።

የጎዳናዋ ወጣት ምሽቱን ተቀምጣ ስታሳልፍ ብቻዋን አይደለችም። በሁለቱ እጇ አጥብቃ የያዘችውን ማስቲሽ የተሞላበትን የሃይላንድ ላስቲክ ደጋግማ ትስባለች። በዚህ ሰአት ማንም ምንም ቢላት ጉዳይዋ አይደለም። ለእሷ የማስቲሹ መኖር ዋስትናዋ ነው። እሱን ከያዘች ዕንቅልፍ አይወስዳትም። ዕንቅልፍ ካልጣላት ደግሞ ራሷን አታስደፍርም። ሌቱን ቀን አድርጋ ማንነቷን ከዕንቅፋት የምትጠብቀው ወጣት ስጋትና ፍራቻ ቢኖራትም የጎዳናውን ህይወት እንዲህ መጋፈጧ ግዴታዋ ሆኗል።

ይህ አይነቱን እውነት በርካቶቹ የጎዳና ላይ ሴት ልጆች ማድረግ የሚሹት ቢሆን ይወዳሉ። አይቻላቸውም እንጂ ቢቻላቸው ኖሮ ሁለም ይህን ዘዴ እንደ አማራጭ ተጠቅመው ከሚመጣባቸው ችግር በሙሉ ባመለጡ ነበር።

የጎዳና ህይወት ለማንም ቢሆን ፈታኝና አስቸጋሪ ነው። ይበልጥ ግን በህጻናትና ሴቶች ላይ የሚያሳርፈው ጠባሳ ከሁሉም ይለያል። ሴቶች ከቤት ከወጡባት ዕለት ጀምሮ ፈተናቸው የበዛ ነው። ‹‹መሬት የወደቀች እርጥብ ስጋ አፈር ይዛ ትነሳለች›› እንዲሉ ከጎዳና የተገኘች ሴትም የምትሸከመው ግፍና መከራ የበረከተ ይሆናል።

ማንም ቢሆን ከተመቸ መኖሪያው ወጥቶ የጎዳና ህይወትን ምርጫው ሲያደርግ የራሱ መነሻ ምክንያት ይኖረዋል። አንዳንዱ በዕለት ቅያሜ ከቤተሰቡ ተጋጭቶ እንደወጣ ይቀራል። ሌላው የራሱና፣ የቤተሰቡ ድህነት ገፍቶት ጎዳና ‹‹ይሻለኝ›› ሲል ይወስናል። በርካታው ደግሞ ተወልዶ ካደገበት ቀዬ እንደዋዛ ወጥቶ ዕድሜውን ከጎዳና ጥግ ያገምሳል። ከነዚህ ነፍሶች መሀል የሚገኙት ሴቶች ደግሞ ክብር ይሉትን እውነት ፈጽሞ አያውቁትም። በእንዲህ አይነቱ ህይወት አንቀጥል ካሉም ሴትነታቸውን አሳልፈው ሊሰጡ ይገዳዳሉ።

ብዙ ጊዜ ይህን ዋጋ የሚከፍሉ ሴቶች ለኔ የሚሉትን አቻ እስካልመረጡ ማንም እንዳሻው ሲጎትታቸው መዋል ማደሩ የተለመደ ነው ። ጉዳዩ በዚህ ብቻ አይቋጭም። በልጅነታቸው የልጅ እናት በሆኑ ጊዜ ኃላፊነቱን የሚጋራላቸው አያገኙምና ችግራቸውን ለብቻቻው ይጋፈጣሉ።

ሁኔታዎችን ለመሸሽ አቻ ይሉትን አጋር በመረጡ ጊዜም አብዛኞቹ ወንዶች አብረዋቸው ሊዘልቁ አይፈቅዱም። የልጅ እናቶች በሆኑበት አጋጣሚ አካባቢውን ጥለው ከሌሎች መላመዳቸው የተለመደ ነው። ሴቶቹ ራሳቸውን ለመርሳትና ችግሮችን ለማለፍ ሲሉ በሱስ መጠመድን ምርጫቸው ያደርጉታል። በልመና የሰው አይንን ከማየት ባለፈ በጫትና ሲጋራ፣ በመጠጥና ሀሺሽ ሱስ ናውዘው ራሳቸውን ለችግር ያጋልጣሉ። ‹‹የወደቀ ዛፍ ምሳር ይበዛበታል›› እንዲሉ ሆኖም ለተደራራቢ ችግሮች ለመጋፈጥ ያመቹ፣ የተመቹ ይሆናሉ። ለሴቶች በጎዳና ራስን ከችግር ጠብቆ፣ ከክፉ ሁኔታዎች ተጠብቆ ለመዝለቅ መሞከር ምናልባትም ፌዝ ሊባል ይችላል ። ይህን እንሞክር የሚሉ ቢኖሩ እንኳን መንገዳቸው ከእርምጃ ጉዞ አያልፍም። ብዙዎች በሚፈተኑበት ጥልፍልፍ ወጥመድ ተጠልፈው ሊወድቁ ግድ ይላል።

በጎዳና ላይ የሚወለዱ ህጻናት ዕጣ ፈንታም ቢሆን ከእናቶቻቸው ማንነት የተለየ አይሆንም። በተለይ ሴቶች ከሆኑ ከህጻንነታቸው ጀምሮ በጾታዊ ትንኮሳ መፈተናቸው አይቀሬ ይሆናል። ለሴቶች በጎዳና ላይ የሚኖረው የህይወት መልክ በእጅጉ ይለያል። ለእነሱ መኖር ማለት እንደሌሎች ተኝቶ መነሳት ብቻ አይደለም። ብዘዎች ከተለያዩ አባቶች የሚወልዷቸውን ልጆች አብልቶ ለማሳደር እንደመፍትሄ የሚወስዱት ራስን ለችግር አሳልፎ መስጠትን ነው። የያዙት የችግር ቋጠሮ በወጉ ሳይላላ ለተመሳሳይ ችግር መጋፈጣቸውም የተለመደ ነው።

ሁሌም ቢሆን የጎዳና ላይ ህይወት በሴቶች ላይ የከፋ በትሩን እንዳሳረፈ ነው። እናትነት ከሚያሳድረው ኃላፊነት በዘለለ በሌሎች ዘንድ የሚኖረው ያልተገባ አመለካከትም ከማንነታቸው አፈንግጠው እንዲታዩ ተጽዕኖውን የጎላ ያደርገዋል።

ጥናቶች እንደሚያመለክቱት በአዲስ አበባ ከተማ ብቻ ከሀምሳ ሺህ በላይ የጎዳና ተዳዳሪዎች ይገኛሉ። አሳሳቢውን የጎዳና ላይ ህይወት ለመታደግም የማህበራዊ ህይወት ተሞክሮዎችን ባህል ከማድረግ ባለፈ እስከዛሬ በመንግስት በኩል የተለያዩ ጥረቶች ሲደረጉ ቆይተዋል። ክረምት ከበጋ ፈተናዎችን ተጋፍጠው ህይወታቸውን ለሚመሩ ነፍሶች ዘለቄታዊ መፍትሄ በማፈላለግም ወደ ትውልድ ቦታቸው እንዲመለሱ የማጓጓዙ ስራ እንደ አማራጭ ሲተገበር ቆይቷል። አንዳንዴ በደጋግ ልቦች አነሳሽነት ለነዚህ ወገኖች ማዕድ የማጋራት ሂደቱ የተለመደ ቢሆንም አሁንም ግን ከዳር ሊያደርሳቸው የሚያስችል ዘላቂ መፍትሄ ሊፈጠር የግድ ይላል።

ቀደም ሲል የጎዳና ነዋሪዎችን ህይወት ለማሻሻል ሲባል በዕቅድ የተያዙ ፕሮጀክቶች በስፋት መተረጎማቸው ደግሞ ይበልጥ ወሳኝነት ይኖረዋል። ለዓመታት በጎዳና ላይ ህይወትን በፈተና የኖሩ ጥቂት የማይባሉ እናቶች የቤት ባለቤቶች የመሆናቸውን ተሞክሮ በማስፋት በርካታ ወገኖች ከአስከፊው የጎዳና ላይ ኑሮ እንዲላቀቁ የማድረግ ኃላፊነት የሁሉም ኢትዮጵያዊ ማህበራዊ ግዴታ ሊሆን ይገባል። መልዕክታችን ነው።

# ዓለም አቀፍ

## ለቻድ መረጋጋት ብቸኛው መፍትሔ አንድነትን ማጠናከር ነው

የሰሜናዊ ማዕከላዊ አፍሪካዊቷ ቻድ ከዘመናት ቀውስ ተላቅቃ የተረጋጋች አገር እንድትሆን ሁሉም ልዩነቱን ወደ ጎን በመተው ወደ አንድ መምጣት ጊዜው አሁን ነው ሲሉ አዲሱ የቻድ ጠቅላይ ሚኒስትር ሳልሕ ከብዛቦ ጥሪ ማቅረባቸውን ዘጋርዲያን ዘግቧል።

ጠቅላይ ሚኒስትር ሳልሕ ከብዛቦ በቅርቡ በአገሪቱ በተቋቋመ ጊዜያዊ የብሔራዊ አንድነት አስተዳደርን ይመሩ ዘንድ በአገሪቱ ፕሬዚዳንት ተሹመዋል። በተደረገው አዲሱ ሹመት በርካታ የቀድሞ አማጺያን በሚኒስቴር ማዕረግ መሾማቸውም ተገልጿል።

“ዓላማዬ የቻድ ሕዝብ አንድ እንዲሆን መሥራት ነው። በእርግጥ ሀይለኛ መናወጥና ቀውስ ውስጥ ያላቸውን አገር አንድ ማድረግ ፈታኝ ቢሆንም ከአንድነት ውጪ ሌላ አማራጭ ስለሌለ አንድነት ላይ መሥራት ምርጫ ሳይሆን ግዴታ ነው” ይላሉ ጠቅላይ ሚኒስትር ሳልሕ ከብዛቦ።

ጠቅላይ ሚኒስትሩ በጠብ መንጃ ጉልበት ለሦስት አስርተ ዓመታት አገሪቱን ያስተዳደሩና እ.ኤ.አ በ2021 በአማጺያን ላይ በተወሰደው የተቀናጀ እርምጃ የተገደሉት ፕሬዚዳንት ኢድሪስ ዴቢ ኢቶን በምርጫ ለማሸነፍ አራት ጊዜ ለፕሬዚዳንትነት ተወዳድረው አልተሳካላቸውም።

ወጣቱ ዴቢ የስልጣን ዘመኑን ከ18 ወራት የስልጣን ቆይታ በኋላ ወደነበረበት ለመመለስ እና በሚመጣው ምርጫ እንደማይሳተፍ ቃል በመግባት ስልጣኑን ተረከበ። ነገር ግን የ18 ወራት ቀነ-ገደብ ሲቃረብ፣ በዴቢ የተካሄደ ሀገር አቀፍ መድረክ ሰዓቱን ዳግም አስጀምሯል።

የአባቱን ሞት ተከትሎ ወደ ሥልጣን የመጣው ወጣቱ ዴቢ፣ ከ18 ወራት የስልጣን ቆይታ በኋላ በአገሪቱ የሲቪል መንግስት በምርጫ እንዲመሰረትና በምርጫው እንደማይሳተፍ ቃል ቢገባም የምርጫው ቀነ-ገደብ ሲቃረብ ግን በቃሉ መሰረት አልተገኘም ተብሏል።

ይሁን እንጂ በጥቅምት ወር መጀመሪያ ላይ ፎረሙ እንደገና ምርጫ ለማካሄድ የሁለት አመት የጊዜ ገደብ



ጠቅላይ ሚኒስትር ሳልሕ ከብዛቦ

አጽድቆ፣ ዴቢ በጊዜያዊነት “የሽግግር ፕሬዚዳንት” በማለት የሰየመው እና በምርጫው እጩ መሆን እንደሚችል አስታውቋል።

ወደ 30 የሚሆኑ አማጺያንና ተፎካካሪ የፖለቲካ ፓርቲ መሪዎች የዘመናት ቀውስ ለመግታት ከአገሪቱ የሽግግር ባለሥልጣናት ጋር ለመሥራት ቢስማሙም፣ ነገር ግን ግንባር ለለውጥ እና ኮንኮርድ በቻድ (ፋክት) የተባለው ኃይለኛው የአገሪቱ አማፂ ቡድን ከባለሥልጣናቱ ጋር ለመሥራት ፈቃደኛ አለመሆኑን ገልጿል።

ሆኖም ግን ጠቅላይ ሚኒስትር ሳልሕ ከብዛቦ ቡድኑ እንዲሳተፍና ለአንዳንዶቻቸው የሚኒስቴር ሹመት ለመስጠት ማቀዳቸውንና ያለሰለሰ ጥረት ለማድረግ ቁርጠኛ መሆናቸውን ይናገራሉ። የቡድኑ ቁልፍ ጥያቄ የሆነው ከፕሬዚዳንቱ ግድያ ጋር ተያይዞ የታሰሩት የቡድኑ አባላት ያለምንም ቅድመ ሁኔታ እንዲለቀቁ ሲሆን ጠቅላይ ሚኒስትሩ ግን “ጉዳዩ ጊዜ ይፈልጋል” ሲሉ አስተያየታቸውን ሰጥተዋል።

በሊቢያ በሚገኝ የፋክት አማጺ መሪ ማሃማት ማህዲ አሊ፣ ቡድናቸው ወደ ውይይት ለመግባት ያለው ሁኔታ ምንም አይነት ወታደራዊ ተሳትፎ ሳይኖረው “ነጻ እና ፍትሃዊ ምርጫ” ከሆነ ብቻ መሆኑን አስታውቀዋል።

## 579 ሚሊዮን አፍሪካውያን አሳሳቢ ድህነት ውስጥ መሆናቸውን አንድ ጥናት አመለከተ

ከሰሃራ በታች ከሚኖሩት አፍሪካውያን ወደ 579 ሚሊዮን የሚጠጉት አስቸጋሪና አሳሳቢ ድህነት ውስጥ መሆናቸው የአለም ሁለገብ የድህነት መረጃ ጥናት አመለከተ። ጥናቱን በጥምረት ያካሄዱት የተባበሩት መንግስታት ኤጀንሲና ኦክስፎርድ ዩኒቨርሲቲ ሲሆኑ፤ በጥናቱ መሰረት በዘንድሮው ዓመት የሰሃራ በታች አገሮች የአስከፊ ድህነት ጽዋ ከደቡብ እስያ አገራት መረከባቸውን ኦልአፍሪካን ኒውስ ዘግቧል።

ቀደም ሲል 385 ሚሊዮን የሚሆኑ ደቡብ እስያውያን በሁለገብ አስከፊ ድህነት ውስጥ በመሆናቸው በድህነት ይጠቀሱ ነበር። ነገር ግን በተለይ ህንድ በድህነት ቅነሳ ስትራቴጂ ላይ በትኩረት በመሥራት ገጽታውን በተወሰነ መልኩ መቀየር ችላለች። ሆኖም ግን ህንድ አሁንም 229 ሚሊዮን ድሆች ያሉባት አገር በመሆኗ በድሆች ብዛት እንደምሳሌ መጠቀሷ አልቀረም።

ጥናቱ የተካሄደው በ111 የአለም አገሮች ላይ ሲሆን፤ እንደከዚህ በፊቱ በቀን ገቢ ብቻ ላይ ሳይሆን የትምህርት ተደራሽነት ፣የጤና አገልግሎት፣መኖሪያ ቤት፣የመጠጥ ውሃ አቅርቦት፣የኤሌክትሪክ ሀይል አቅርቦትና የንጽሕና አጠባበቅን መሰረት ያደረገ በመሆኑ ሁለገብ ጥናት መሆኑ ተመስክሮለታል።

በእነዚህ መመዘኛዎች፣ የዓለም ድሆች ቁጥር በቀን ከ1 ነጥብ 9 የአሜሪካን ዶላር በማግኘት ከዓለም አቀፍ የድህነት ወለል በታች ከሚኖሩት የሰዎች ቁጥር በእጥፍ እንደሚበልጥ ጥናቱን ያካሄዱ ተመራማሪዎች ይፋ አድርገዋል።

በጥናቱ ግኝትም መሰረት ናይጀሪያ 97 ሚሊዮን ድሆች በመያዝ ከቀጣናው ቀዳሚ ተርታ ላይ ተሰልፋለች። እንዲሁም ኒጀር፣ደቡብ ሱዳንና ቡርኪናፋሶ በድምሩ የ50 ሚሊዮን ድሃ ሕዝብ ባለቤት በመሆናቸው በአለም የመጨረሻ ድሃ አገራት ተብለዋል።

ከሰሃራ በታች በሚኖሩት አገሮች ውስጥ የኤሌክትሪክ



ሀይል ተደራሽነት 48 ነጥብ 4 በመቶ ሲሆን፤ በተለይ በስምንት የሆኑ አገሮች ውስጥ 80 በመቶ የሚሆን ሕዝብ በጨለማ ውስጥ ሲሆን የኤሌክትሪክ ተጠቃሚው ቁጥር 20 በመቶ ብቻ መሆኑ በጥናቱ ተረጋግጧል።

የአገሮቹ የድህነት ደረጃ ያለበት ሁኔታ ለመገምገም በተቀመጡት መስፈርቶች ሁሉ በቀጣናው “የድሃ ድሃ” የሚባሉ ሰዎች 3 ነጥብ 8 ሚሊዮን ሲሆኑ፤ ከእነዚህም 910ሺህ የሚሆኑት በናይጄሪያ፣ 685 ሺህ የሚሆኑት በኒጀር እንዲሁም 615ሺህ የሚሆኑት ደግሞ በኢትዮጵያ ውስጥ ይኖራሉ ተብሏል።

የኮቪድ-19 ወረርሽኝ ከመከሰቱ በፊት ድህነትን በከፍተኛ ፍጥነት ከቀነሱት 20 የቀጣናው አገራት መካከል 12 የአፍሪካ ሀገራት ኮንጎ፣ ኮትዲቯር ፣ ኢትዮጵያ፣ ጋምቢያ፣ ጊኒ፣ ላይቤሪያ፣ ማላዊ፣ ማሊ፣ ሞዛምቢክ፣ ሳኦቶሜ እና ፕሪንሲፔ፣ ሴራሊዮን እና ቶጎ በአርአያነት የሚጠቀሱ ቢሆንም ድሃ ከመባል ግን አላዳናቸውም።




አዲስ ዘመን

ሐሙስ ስፖርት

ይህ ቦታ
ለማስታወቂያ ክፍት ነው!

# ኢትዮጵያውያን አትሌቶች በቫሌንሲያ ግማሽ ማራቶን ለአሸናፊነት ይጠበቃሉ

ብርሃን ፈይሳ

በስፔን ከሚካሄዱ የጎዳና ላይ የሩጫ ውድድሮች መካከል የቫሌንሲያ ግማሽ ማራቶን በቀዳሚነት ተጠቃሽ ነው። የዓለም አትሌቲክስ ለዚህ የጎዳና ላይ ውድድር እአአ በ2016 የወርቅ ደረጃ የሰጠው ሲሆን፤ በዓለም ላይ «ሱፐር ሃፍስ» ከሚባሉት መሰል ታላላቅ የግማሽ ማራቶን ውድድሮች(ሊዝበን፣ ፕራግ፣ ኮፐንሃገን እና ካርዲፍ የግማሽ ማራቶን ሩጫዎች) ጎን የሚሰለፍም ነው። በዚህም ምክንያት የዓለም የግማሽ ማራቶን ቻምፒዮናን ለማካሄድም ቫሌንሲያ ተመራጭ ሊሆን ችሏል።

በውብና በበርካታ ስነህንጻ ባማረችው ቫሌንሲያ ከተማ የሚካሄደው ይህ ውድድር በታላላቅና ዝነኛ የጎዳና ላይ ሯጮችም ተመራጭ ነው። ተመራጭ የሆነበት ዋናው ምክንያት ደግሞ ፈጣን ሰአት የሚመዘገብበት ውድድር በመሆኑ ነው። ለዚህ ማሳያ የሚሆነው ደግሞ በሴቶች የዓለም ግማሽ ማራቶን ክብረወሰን የተመዘገበው በዚህ ውድድር በመሆኑ ነው። ይህም በኢትዮጵያዊቷ ጠንካራ አትሌት ለተሰንበት ግደይ የተመዘገበ ሲሆን፤ አትሌቷ ባለፈው ዓመት ርቀቱን ስታሸንፍ 1:02:52 ሰዓት ማስመዝገቧ ይታወሳል። ኬንያዊው ኪቢዎት ካንዳይ ደግሞ ከሁለት ዓመት በፊት 57፡32 የሆነ ሰዓት በማስመዝገብ የአለምን ክብረወሰን መስበር ችሎ ነበር። በዘንድሮው ውድድርም በሁለቱም ጾታዎች ፈጣን ሰዓት እንደሚመዘገብ ይጠበቃል።

የዚህ ዓመቱ የቫሌንሲያ ግማሽ ማራቶንም በመጪው እሁድ የሚካሄድ ሲሆን፤ እንደተለመደው በርቀቱ ጠንካራ የሆኑና ፈጣን ሰዓት ያላቸው አትሌቶች ተሳታፊዎች ይሆናሉ። ከእነዚህ አትሌቶች መካከል ኢትዮጵያዊያን አትሌቶችም በሁለቱም ጾታ ተሳታፊዎች መሆናቸው ተረጋግጧል። ይሁንና በወንዶች በኩል የቦታው ባለፈጣን ሰዓት ባለቤቱ ካንዳይ ዘንድሮም የውድድሩ ተሳታፊ መሆኑ እንዲሁም ሌሎች ፈጣን ሰዓት ያላቸው የሃገሩ ልጆችም የሩጫው ተካፋይነታቸውን ማረጋገጣቸው ውድድሩን ከባድ ሊያደርገው እንደሚችል ይጠበቃል።




አትሌት ሚልኬሳ መንገሻ በቫሌንሲያ ማራቶን የአሸናፊነት ግምት ከተሰጣቸው ኢትዮጵያውያን ዋነኛው ነው፤

ጠንካራ ኢትዮጵያዊያን አትሌቶችም ከተፎካካሪነት በዘለለ ከፍተኛ የአሸናፊነት ቅድመ ግምት የተሰጣቸው ሆነዋል። አትሌት ሚልኬሳ መንገሻ በርቀቱ ባለው ፈጣን ሰዓት ቀዳሚው የአሸናፊነት ግምት ከተሰጣቸው ኢትዮጵያውያን አትሌቶች አንዱ ነው። የ22 ዓመቱ ወጣት በዓመቱ በርካታ ውድድሮች ላይ የተሳተፈ ሲሆን፤ በሂውስተን እና ኮፐንሃገን ግማሽ ማራቶኖች ላይም ሮጧል። ባለፈው ወር በተካሄደው የኮፐንሃገን ግማሽ ማራቶን ተወዳድሮም 58:58 የሆነ የግሉን ፈጣን ሰዓት ሊያስመዘግብ ችሏል።

ሌላኛው በመም የረጅም ርቀት ውድድሮች በተለይ የሚታወቀው ኢትዮጵያዊ አትሌት ዮሚፍ ቀጀልቻም በውድድሩ ጠንካራ ተፎካካሪ ይሆናሉ ተብሎ ከሚጠበቁት አትሌቶች መካከል ነው። ዮሚፍ በቅርቡ በጎዳና ላይ ሩጫ አይታይ እንጂ እአአ በ2019 የቫሌንሲያ ማራቶንን በመሮጥ አሸናፊ መሆኑ የሚታወስ ነው። በወቅቱ የገባበት 59፡05 የሆነ ሰዓት ደግሞ አትሌቱ በርቀቱ ያለው ፈጣን ሰዓት ነው። በመሆኑም አትሌቱ ጠንካራ ተፎካካሪ ብቻም ሳይሆን አሸናፊ የመሆን እድሉ የሰፋ እንደሚሆንም ተገምቷል። ታደሰ ወርቁም በዚህ ውድድር የሚካፈል ኢትዮጵያዊ አትሌት መሆኑ ታውቋል።

በሴቶች በኩል ኢትዮጵያዊያኑ አትሌቶች ያለፉትን አራት ዓመታት በተከታታይ አሸናፊዎች ነበሩ። ዘንድሮ የውድድሩ ተሳታፊነታቸውን ያረጋገጡ ኢትዮጵያዊያን አትሌቶች እንደተለመደው አሸናፊዎች ሊሆኑ እንደሚችሉም ተገምቷል። ከእነዚህም መካከል ቀዳሚዋ አትሌት ሃዊ ፈይሳ ናት። በኮፐንሃገን፣ ባህሬን እና በቫሌንሲያ ግማሽ ማራቶን በመሮጥ ልምድ ያላት ይህች አትሌት፤ ባለፈው ዓመት በኮፐንሃገን ግማሽ ማራቶን ያስመዘገበችው 1ሰዓት ከ05ደቂቃ ከ41 ሰከንድ የግሏ ፈጣን ሰዓት ነው። ይህ ሰዓት አብረዋት በውድድሩ ላይ ከሚሳተፉት አትሌቶች በሰከንዶች ብቻ የዘገየ ቢሆንም ጠንካራ የአሸናፊነት ፉክክር እንደምታደርግ ይጠበቃል።

በአምስት ሰከንዶች ብቻ ከሃዊ የዘገየ ሰዓት ያላት ኢትዮጵያዊቷ አትሌት ቦሰና ሙላቴም የዚህ ውድድር ተካፋይ ናት። በዚህ ዓመት የኮፐንሃገን ግማሽ ማራቶን ሁለተኛ ደረጃን በመያዝ ያጠናቀቀችው ሌላኛዋ አትሌት ጽጌ ገብረሰላማም የቫሌንሲያ ግማሽ ማራቶን ተካፋይ ናት። አትሌት እታገኝ ወርቁም በተመሳሳይ የውድድሩ ተፎካካሪ ይሆናሉ በሚል ግምት ከተሰጣቸው አትሌቶች መካከል አንዷ ሆናለች።



## የጨረታ ማስታወቂያ

በደ/ብ/ብ/ሕ/መንግሥት በጌዴኦ ዞን የዲ/ዙ/ወ/ፋ/ጽ/ቤት በ2015 በጀት ዓመት ለወረዳው ሴክተር መ/ቤቶች አገልግሎት የሚውሉ ቋሚና አላቂ የቢሮ ዕቃዎችን ማለትም ሎት 1 የጽህፈት መሣሪያ፣ ሎት 2 ኤሌክትሮኒክስ፣ ሎት 3 ሞተር ሳይክል፣ ሎት 4 የደንብ ልብስ፣ በአካባቢው ማቴሪያል የሚሰሩ ለቢሮ አገልግሎት የሚውሉ ፈርኒቸሮችን በግልጽ ጨረታ አወዳድሮ ለመግዛት ይፈልጋል።

ስለዚህ በጨረታው ለመሳተፍ የምትፈልጉ ተጫራቾች

- በዘመኑ የታደሰ የንግድ ፈቃድ ማቅረብ የሚችል
- የንግድ ምዝገባ የምስክር ወረቀት ማቅረብ የሚችል
- የአቅራቢነት ምዝገባ የምስክር ወረቀት ማቅረብ የሚችል
- የግብር ከፋይነት መለያ ቁጥር ያለው
- የተጨማሪ እሴት ታክስ ምዝገባ የምስክር ወረቀት ማቅረብ የሚችል

ከላይ በዝርዝር የተቀመጡትን መስፈርቶች የሚያሟሉ ተጫራቾች ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ ለተከታታይት 15 ቀናት የጨረታ ሰነዱን ዘወትር በሥራ ሰዓት ለእያንዳንዱ የማይመለስ ብር 100 በመክፈል ሰነዱን ከዲላ ዙ/ወ/ፋይ/ጽ/ቤት ግዥና ን/አስ/ዋና የሥራ ሂደት በመቅረብ መግዛት ትችላላችሁ።

**ተጫራቾች**

- ሎት 1 የጽሕፈት መሣሪያ ብር 5000 /አምስት ሺ ብር/
- ሎት 2 ኤሌክትሮኒክ ብር 5000 /አምስት ሺ ብር/
- ሎት 3 ሞተር ሳይክል ብር 5000 /አምስት ሺ ብር/
- ሎት 4 የሠራተኞች የደንብ ልብስ ብር 5000/ አምስት ሺ ብር/
- ሎት 5 በአካባቢው ማቴሪያል የሚሠሩ ለቢሮ አገልግሎት የሚውሉ ፈርኒቸሮች ብር 5000/ አምስት ሺ ብር/ በባንክ በተረጋገጠ ሲፒኦ ከታወቀ ባንክ በሚሰጥ የክፍያ ማዘዣ ቼክ ሆኖ በጥሬ ገንዘብ ብቻ ዋስትና ማቅረብ አይቻልም።
- ተጫራቾች ዕቃዎች የሚሸጡበትን ዋጋ በተዘጋጀው ዝርዝር ሰነድ ላይ ዋጋ ሞልተው አንድ ኦሪጅናል ሰነድና ሁለት ኮፒ ሰነድ በተለያየ ፖስታ ካሸጉ በኋላ ከሲፒኦ ጋር በአንድ ትልቅ ፖስታ በሰም በማሸግ ማቅረብ ይገባቸዋል።
- ኦሪጅናል ኮፒ ሰነድ በላይ ማንኛውም አይነት ስርዝ ድልዝ /ፍሉድ/ የተስተካከለ ካለ በሚታይ መልኩ በድጋሚ ተጽፎ በተጫራች/በሕጋዊ ተወካይ ፊርማ መፈረም የለበትም።
- እያንዳንዱ የጨረታ ሰነድ ላይ ሕጋዊ የድርጅት ማህተምና ፊርማ ማረፍ አለበት።
- ጨረታው የሚከፈተው ይህ ማስታወቂያ በአዲስ ዘመን ጋዜጣ ወጥቶ በአየር ላይ ከዋለበት ቀን አንስቶ በተከታታይ 15 ቀናት ቆይቶ በ16ኛው ቀን ጠዋት የጨረታ ሳጥን በ4፡00 ሰዓት ታሽጎ በ4፡30 ተጫራቾች ወይም ህጋዊ ወኪሎቻቸው በተገኙበት ይከፈታል። ስለሆነም 16ተኛው ቀን የሥራ ቀን ካልሆነ በሚቀጥለው የሥራ ቀን በተመሳሳይ ሰዓት ጨረታው የሚከፈት ይሆናል።
- የጨረታ ሳጥኑ የሚገኘው በዲላ/ዙ/ወ/ፋይናንስ ጽ/ቤት ቅጥር ግቢ ግዥና ንብ/አስ/ዋና/የስራ ሂደት ነው።
- ተጫራቾች በጨረታው ተወዳድረው ያሸነፉባቸውን ዕቃዎች በዲላ/ዙ/ወ/ፋይናንስ ጽ/ቤት እቃ ግምጃ ቤት ድረስ የማጓጓዝ እና የማውረጃ ወጭ ችለው ማቅረብ ይኖርባቸዋል።
- መ/ቤቱ የተሻለ ዘዴ ካገኘ ጨረታውን ሙሉ በሙሉ ወይም በከፊል የመሰረዝ መብቱ የተጠበቀ ነው።

ለበለጠ መረጃ ስልክ ቁጥር 0986058964/0916629023

**በደ/ብ/ብ/ሕ/መንግሥት በጌዴኦ ዞን የዲ/ዙ/ወ/ፋ/ጽ/ቤት**

## የንግድ ምልክት የባለቤትነት ለውጥ ማስታወቂያ

ከድጃ ቡሴር ሻፊ አድራሻው ክልል አዲስ አበባ፣ ክ/ከተማ ኮ/ቀራንዮ፣ ወረዳ 07፣ የቤት.ቁ አዲስ, ኢትዮጵያ የሆነ ከዚህ በታች የሰፈረው የንግድ ምልክት በኢትዮጵያ ብቸኛ ባለቤትና ተጠቃሚ መሆኑ በዚህ ማስታወቂያ ተገልጿል።

**በኢትዮጵያ የተመዘገበው የንግድ ምልክት ዝርዝር**

| ንግድ ምልክት | የማመልከቻ ቁጥር | የማስታወቂያዎቹ ቁጥርና ቀን |
|---|---|---|
|  | LTM/12340/2014 | ቁጥር: LXXXI -332<br>ቀን: 02/12/2014 |

የንግድ ምልክቱ የሚውለው ከፍ ብለው በተዘረዘሩት ማስታወቂያዎች ላይ ለተጠቀሱት ዕቃዎች ሲሆን ንግድ ምልክቱ በማስታወቂያዎቹ ላይ ይገኛል። ባለቤቱ በዚህ የንግድ ምልክት ላይ ያለውን የባለቤትነት መብት አምርሩ ሱሩር አንዳሮ አድራሻው, ወረዳ 05, የቤት.ቁ 748, ልደታ, አዲስ አበባ, ኢትዮጵያ ለሆነ ድርጅት ያስተላለፈ ሲሆን ይህም በኢትዮጵያ አዕምሯዊ ንብረት ባለሥልጣን በተመዘገበ የባለቤትነት ለውጥ ሰርተፊኬት ተረጋግጧል። ስለሆነም ማንኛውም ግለሰብ ወይም የሕግ ሰውነት ያለው ተቋም ከባለቤቱ ፈቃድ ውጪ በዚህ ምልክት በሚጠቀም ወይም አስመስሎ በሚሰራ ላይ በሕግ ክስ ይመሰረትበታል።

**የኢትዮጵያ አዕምሯዊ ንብረት ባለሥልጣን**

**ADDIS ZEMEN VOl-LXXXII No-040 10/2/2015 (20/10/2022)**

## የሐራጅ ሽያጭ ማስታወቂያ

በፍ/ባለመብት ወ/ሮ ፋጡማ ኑሪ እና በፍ/ባለዕዳ እነ አቶ ኪያር ሻፊ መካከል ስላለው የፍርድ አፈጻጸም ጉዳይ የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁጥር/92842 በጥቅምት 8 ቀን 2014 ዓ/ም እና በኮ/መ/ቁ/98107 በ14/04/2014 ዓ.ም በዋለው ችሎት በሰጠው ትዕዛዝ መሠረት 1ኛ በአዲስ ከተማ ክ/ከተማ ወረዳ 04 የቤት ቁጥር 803 የሆነው ቤት በይዞታ መለያ ኮድ AA000020400279 የቦታው ስፋት 160 ካ/ሜ ካርታ ያለው በግራቀኙ እግድ ያለበት የባንክ ዕዳ 1,899,167 ያለበት የሆነ የሐራጅ ሽያጭ መነሻ ዋጋ ብር 347,600 (ሦስት መቶ አርባ ሰባት ሺ ስድስት መቶ ብር) የትራንዛክሽን ታክስ ገዥ የሚከፍል መሆኑ ታውቆ ኅዳር 12 ቀን 2015 ዓ.ም በሐራጅ ይሸጣል። የተጫራቾች ምዝገባ 8፡30 ሰዓት ተጀምሮ የቀረቡ ተጫራቾች ተመዝግበው እንደተጠናቀቀ ወዲያዉኑ ጨረታው የሚካሄድ ይሆናል። 2ኛ በአዲስ ከተማ ክ/ከተማ ወረዳ 1 የቤት ቁጥር 298 የሆነው የንግድ ድርጅት የሐራጅ ሽያጭ መነሻ ዋጋ ብር 36,145(ሠላሳ ስድስት ሺ አንድ መቶ አራባ አምስት ብር) ድርጅቱ የመንግስት በመሆኑ ተጫራቾች የሚገዙት ድርጅቱን ሳይሆን ከመንግስት ተከራይቶ ውል ተፈራርሞ በቤቱ ውስጥ የንግድ ሥራ ለመስራት ያለው መብት ብቻ ሆኖ የትራንዛክሽን ታክስ ገዥ የሚከፍል መሆኑ ታውቆ ኅዳር 12 ቀን 2015 ዓ/ም በሐራጅ ይሸጣል። የተጫራቾች ምዝገባ 9:00 ሰዓት ተጀምሮ የቀረቡ ተጫራቾች ተመዝግበው እንደተጠናቀቀ ወዲያዉኑ ጨረታው የሚካሄድ ይሆናል።

የሐራጁ ሽያጭ የሚካሄደው በፌዴራል ፍርድ ቤቶች የፍርድ አፈጻጸም ዳይሬክቶሬት የጨረታ አዳራሽ ውስጥ ሲሆን፣ ንብረቱን ተጫርተው ለመግዛት የሚፈልጉ ተጫራቾች ከጨረታው ቀደም ብሎ ባሉት አራት የሥራ ቀናቶች ውስጥ ባለመብቱ ለማስጎብኘት በሚመርጧቸው ሦስት የሥራ ቀናት በፌ/ፍ/ቤቶች ፍርድ አፈጻጸም ዳይሬክቶሬት ሐራጅ ክፍል ድረስ ከጠዋቱ በ3፡30 ብቻ በመገኘትና ባለመብቱ በሚያቀርበው ትራንስፖርት ንብረቱን ለመጐብኘት የሚችሉ ሲሆን እያንዳንዱ ተጫራች በሚጫረትበት ወቅት የንብረቱን ግምት 1/4 ኛውን በባንክ በተረጋገጠ CPO ማስያዝ ይኖርበታል። ከ1/4ኛ አስበልጦም ሆነ አሳንሶ የሚመጣ ተጫራች በጨረታው አይካፈልም። በጨረታው አሸናፊ የሆነው ግለሰብ አሸናፊ የሆነበትን ገንዘብ በአጠቃላይ ጨረታውን ከአሸነፈበት ቀን ጀምሮ በ15 ቀናት ውስጥ ገቢ ማድረግ አለበት።

በተጨማሪ ተጫራቾች ካፒታል ጌይን እና ታክስ ስምን ይዛወርልኝ የሚልን ጥያቄ፣ ሐራጁ ጐድቶኛል የሚሉ ጥያቄዎችን ዳይሬክቶሬቱ የማያስተናግድና በችሎት የሚጠየቅ መሆኑን እንገልፃለን።

**በኢ.ፌ.ዴ.ሪ ጠቅላይ ፍ/ቤት የፌዴራል ፍ/ቤቶች የፍርድ አፈጻጸም ዳይሬክቶሬት**